# በኢየሱስ እናምናለን

## ትምህርት ሁለት

# ክርስቶስ

# We Believe in Jesus

## Lesson Two

## The Christ

## ተርጓሚ፡ እሸቴ በለጠ

THIRD MILLENNIUM MINISTRIES

Biblical Education. For the World. For Free.

## ማውጫ


1. **መግቢያ**
2. **ውልደትና ዝግጅት**

    ትስጉት

        ከድንግል መወለድ

        የዳዊት ዘር

        ጣምራ አንድነት

    ጥምቀት

        ክርስቶስ መሆኑ መረጋገጡ

        ለአገልግሎት መቀባቱ

        ጽድቅን መፈፀሙ

    መከራ

        መታዘዝ

        ድካምን መረዳት

        እንከን አልባነት

3. **የአደባባይ አገልግሎት**

    ወንጌል

        መንግሥት

        ንስሓ

    ሥልጣን/ኃይል

        የተረጋገጠ ማንነት

        ጥርጥር የሌለበት ስኬት

    ማረጋገጫ

        ሐዋርያዊ መግለጫ

        ልውጠት

4. **ህማማትና ሞት**

    ሆሳዕና

    የጌታ እራት

ስርየት

አዲስ ኪዳን

ስቅለት

ልውውጥ

ፍርድ

## 5. ከፍታ/ከበሬታ

ትንሣኤ

የማዳን ዕቅድ

የድነት በረከቶች

ዕርገት

ሐዋርያዊ ሥልጣን

መንበረ-ንግሥና

አገዛዝ/ግዛት

ቃልና መንፈስ

ምልጃ

ግዛት

መመለስ/ምፅአት

ፍርድ

ኀዳሴ

## 6. መደምደሚያ

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጎሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. In 2009 ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሊ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡፡

# መግቢያ

በእኛ ዘመን በአብዛኛው የዓለም ክፍል፣ ሰዎች ቢያንስ ሁለት ስሞች አሉዋቸው፡፡ ለምሳሌ፣ ዝርያቸውን የሚያመለክት የአባት ስም እና በቀጥታ እነርሱ የሚጠሩበት የራሳቸው ስም፡፡ እንግዲያው ልጆችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስናስተምራቸው፣ ብዙውን ጊዜ የሚገምቱት "ኢየሱስ" የራሱ ስም "ክርስቶስ" ደግሞ የአባቱ ስም እንደሆነ ነው፡፡ እንዲያውም አዋቂዎችም እንኳን ይህንን የመሰለው የተሳሳተ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡ ይህ ግን ሊያስገርመን አይገባም፡፡ አንዳንድ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ እንኳን "ክርስቶስ" የሚለውን ቃል የኢየሱስ ስም እንደሆነ ዓይነት ይጠቀምበታል፡፡ እውነታው ግን፣ "ክርስቶስ" የሚለው ቃል በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የኢየሱስን አገልግሎትና ከበሬታ የሚያመለክት መጠሪያ ነው፡፡

ይህ ትምህርት *በኢየሱስ እናምናለን* የሚለው ተከታታይ ትምህርታችን ሁለተኛው ትምህርት ነው፡፡ "ክርስቶስ" የሚል ርዕስም ሰጥተነዋል፡፡ በዚህ ትምህርት የምንከተለው ስልት ክርስቶስ መሆን ማለት ለእርሱ ምን ማለት እንደሆነ ማብራራት በምንችልበት መንገድ በክርስቶስ ሕይወት የተለያዩ ሁነቶችና ባሕርያት ላይ ትኩረት ማድረግ ነው፡፡

በቀላሉ "ክርስቶስ" የሚለው ቃል የተቀባ ማለት ነው፡፡ "*Christos*" የተሰኘው የአዲስ ኪዳኑ የግሪክ ቃል አቻ ፍቺ ሲሆን፣ ይኸው ቃል ራሱ የብሉይ ኪዳኑ የዕብራይስጥ ቃል " *Mashiach* or Messiah." የሚለውም ቃል ፍቺ ነው፡፡

ብዙ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ በቀጥታ "ክርስቶስ" ወይም "የተቀባ" የሚለውን ቃል ለክርስቶስ ነጥሎ ያለመጠቀሙን ምክንያት በአድናቆት የማወቅ ጉጉት አላቸው፡፡ በብሉይ ኪዳን ዘመን ለእግዚአብሔር ለየት ያለ አገልግሎት ዘይት በመቀባት የተለዩ ሰዎችን ለማመልከት አገልግሎት ላይ የሚውል የተለመደ ቃል ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ታሪክ በአንድ የተወሰነ እርከን ላይ፣ ሁሉም ነቢያት፣ ካህናት፣ ቀሳውስት እና ነገሥታት በጥቅሉ "የተቀቡ" ተብለው ይጠሩ ነበር፡፡

ለምሳሌ፣ በብሉይ ኪዳን ዘመን "ክርስቶስ" ወይንም "የተቀባ" የሚለው ቃል ከሚፈታባቸው ወሳኝ ፍቺዎች መካከል አንዱ በእስራኤልና በይሁዳ ላይ ይነግሡ የነበሩትን የዳዊት ዝርያዎች ለማመልከት ጥቅም ላይ ይውል የነበረው ነው፡፡ ይህንንም እንደ 2ዜና ምዕራፍ 6ቁጥር 42፤ መዝ 89 ቁጥር 38 እና 39፣51፤ መዝ 132 ቁጥር 10 እና 17 በመሳሰሉት ስፍራዎች እናገኛቸዋለን፡፡ ሆኖም ግን በርካታ የብሉይ ኪዳን ክፍሎች አንድ ልዩ የተቀባ ወደፊት እንደሚመጣ በማመልከት ሕዝቡ እንዲጠብቅ ያደርጉ ነበር፡፡ እርሱም ለየት ባለ መንገድ፣ ሦስቱንም በአንድነት አጣምሮ እንደሚይዝ፣ የእግዚአብሔርንም የማዳን ዕቅድ በዚህ ዓለም ተፈፃሚ እንደሚያደርግ ያሳዩ ነበር፡፡ ይህም ሰው በአይሁድ መካከል እንደ መሲሕ ወይንም

ክርስቶስ ይታወቃል፡፡ በእርግጥም፣ በመላው ዓለም የሚገኙ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ታላቁ መሲሕ፣ የመጨረሻው የተቀባው ክርስቶስ መሆኑን ያውቃሉ፡፡

ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የምናደርገው ውይይት በአራት ክፍሎች ይከፈላል፡፡ በመጀመሪያ፣ ከልደቱ አንስቶ እንደ ክርስቶስ ኃላፊነቱን ለመወጣት ዝግጅት እስካደረገባቸው ጊዜያት ያሉትን ሁነቶች ነገረ-መለኮታዊ ፋይዳ እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ እንደ ክርስቶስ የነበረውን የአደባባይ አገልግሎት እንዳስሳለን፡፡ ሦስተኛ፣ ህማማቱንና ሞቱን እንመረምራለን፡፡ አራተኛ ደግሞ፣ እንደ ክርስቶስ ከበሬታውን የሚያካትቱ ሁነቶችን እንመረምራለን፡፡ አስቀድመን በኢየሱስ ውልደትና ዝግጅት እንጀምር፡፡

## 2. ውልደትና ዝግጅት

በዚህ ትምህርት፣ መወለዱ አስቀድሞ ከተነገረበት ጊዜ አንስቶ በምድረ በዳ ከፈተናው በድል እስከተመለሰበት ጊዜ ድረስ ያለውን የኢየሱስን ልደትና ለመሲሐዊ አገልግሎቱ ያደረገውን ዝግጅት እናብራራለን፡፡ የዚህን የሕይወቱን ክፍል እያንዳንዳቸውን ዝርዝር ጉዳዮች በጥልቀት እንመለከታለን፣ ሆኖም ለአሁኑ ጠቅላላውን ዘመን በፍጥነት ጠቅለል አድርገን እንመለከታለን፡፡

ኢየሱስ ከመወለዱ አስቀድሞ፣ ለድንግሏ እናቱ ለማርያምና ለእጮኛዋ ለዮሴፍ መላእክት የመወለዱን የምሥራች አብስረዋቸው ነበር፡፡ በሉቃስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 26 እስከ 38 መላኩ ገብርኤል የኢየሱስን መወለድ ለማርያም አስቀድሞ እንደነገራት ተጽፏል፡፡ በማቴዎስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 20 እስከ 21 ባለው ክፍል ደግሞ የእግዚአብሔር መልአክ ተመሳሳይ የሆነ መልእክት ለእጮኛዋ ለዮሴፍ ማድረሱን እናነባለን፡፡ ዮሴፍና ማርያም የሮማውያን ግዛት አካል በሆነችው በእስራኤል ውስጥ ይኖሩ ነበር፡፡ በማርያም መጨረሻዎች የእርግዝናዋ ወራት፣ አውጉስጦስ ቄሳር ዮሴፍና ማርያም በቤተልሔም ከተማ ለግብር ከፋይነት እንዲመዘገቡ ትዕዛዝ አወጣ፡፡ ይህንንም በሉቃስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 1 እስከ 5 ተጽፎ እናነባለን፡፡

በሉቃስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 6 እስከ 20 መሠረት፣ ኢየሱስ በዚህ ቆይታ ወቅት ተወለደ፡፡ ልደቱም በአካባቢው ለነበሩ በኋላም ሊያዩት ለመጡና የሰሙትን ሄደው ላወሩ እረኞች በመላእክት ሠራዊት አማካይነት ተበሰረ፡፡ ሉቃስ በጠቀሳቸው ገዢዎችና በዘመኑ የተከናወኑ ኩነቶች፣ እና በተጨማሪም በሌሎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮች መሠረት ላይ ቆመው የታሪክ ምሁራን እንደሚያሰሉት ኢየሱስ የተወለደው በ4 ኛው ዓ.ም. አካባቢ ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ  በኢየሱስ የልጅነት ሕይወት ስለ ተከናወኑ ሁነቶች ብዙ የሚያወራው ነገር የለም፣ ነገር ግን ሉቃስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 21  በተወለደ በስምንተኛ ቀኑ ስም እንደ ወጣለትና እንደ ተገረዘ ይናገራል፡፡ በሉቃስ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 22 እስከ 40 እንደምናነብበው ኢየሱስ ወደ ቤተመቅደስ በተወሰደ ጊዜም ሁለት የጌታ ታማኝ አገልጋዮች ስምዖንና ሐና ለረጅም ዘመን

ሲጠበቅ የነበረው ክርስቶስ መሆኑን አወቁ፡፡ በማቴዎስ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 1 እስከ 12 እንደምናነብበው ልደቱ በልዕለ ተፈጥሮአዊ የከዋክብት እንቅስቃሴ የታጀበ ነበርና የምሥራቅ ጠቢባን እንደ አይሁድ ንጉሥ ተቀበሉት፡፡

ቢሆንም፣ ኢየሱስ በእስራኤል ውስጥ ረጅም ጊዜ አልቆየም፡፡ የወቅቱ የአይሁድ ንጉሥ ታላቁ ሄሮድስ አዲሱ የአይሁድ ንጉሥ እንደተወለደ ከሰብዓ-ሰገል ሲረዳ፣ አዲስ የተወለደውን መሲህ ሊገድለው ፈለገ፡፡ ስለዚህም፣ በኢየሩሳሌምና በአካባቢዋ የሚኖሩ ሁለት ዓመትና ከዚያም በታች ዕድሜ ያላቸው ወንዶች ሕፃናት እንዲታረዱ አዘዘ፡፡ ጌታ ግን ሕፃኑንና ቤተሰቡን ይዞ ወደ ግብፅ እንዲሸሽ አስጠነቀቀው፡፡ ሄሮድስም ሲሞት ቤተሰቡ ወደ እስራኤል ተመለሰ፡፡ ሆኖም ግን ከጌታ በድጋሚ በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት፣ ከአዲሱ የአይሁድ ንጉሥ ከሄሮድስ ልጅ ከአርኬላዎስ ራቅ ብሎ በትንሿ ከተማ በናዝሬት ተቀመጠ፡፡ ይህም በማቴዎስ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 13 እስከ 23 ተመዝግቦ ይገኛል፡፡

ኢየሱስም ሲያድግ፣ ቤተሰቦቹ በኢየሩሳሌም የሚከበረውን የአይሁድን ዓመታዊ በዓል ለመካፈል ወጡ፡፡ በሉቃስ 2 ከቁጥር 41 እስከ 52 ተመዝግቦ እንደምናነብበው፣ ከእነዚህ ጉዞዎች በአንዱ እና ኢየሱስም ዐሥራ ሁለት ዓመት ሲሞላው፣ የሃይማኖት መሪዎችንና አስተማሪዎችን በጥበቡና በእውቀቱ እንዳስገረማቸው እንረዳለን፡፡

ኢየሱስ ሠላሳ ዓመት ሲሞላው፣ ራሱን ለአደባባይ አገልግሎት ማዘጋጀት ጀመረ፡፡ በመጀመሪያ፣ በማቴዎስ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 13 እስከ 17፤ በማርቆስ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 9 እስከ 11 እና በሉቃስ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 21 እስከ 23 እንደተጻፈ በመጥምቁ ዮሐንስ ተጠመቀ፡፡

ከዚያም፣ ከጥምቀቱ በኋላ ወዲያውኑ፣ ኢየሱስ ለአርባ ቀናት በምድረበዳ ፆመ፡፡ ይህንንም በማቴዎስ ምዕራፍ 4 ከቁጥር1 እስከ 11፤ በማርቆስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 12 እና 13 እና በሉቃስ ምዕራፍ 4 ከቁጥር 1 እስከ 13 ተመዝግቦ እናገኛለን፡፡ በዚህም ወቅት፣ የአደባባይ አገልግሎቱን ከመጀመሩ አስቀድሞ፣ የሰይጣንን ፈተና ተቋቋመ፡፡

ስለ ኢየሱስ የውልደትና የዝግጅት ጊዜያት ልንናገር የምንችላቸው ብዙ ነገሮች ቢኖሩም፣ በሦስቱ ሁነቶች ላይ ብቻ እናተኩራለን፡፡ እነርሱም ትስጉቱ፣ ጥምቀቱ እና ፈተናው ናቸው፡፡ አስቀድመን ስለ ትስጉቱ እንነጋገር፡፡

## ትስጉት

ትስጉት የሚለው ነገረ-መለኮታዊ ቃል የኢየሱስን ሰዋዊ ተፈጥሮ፣ ማለትም የሰውን አካልና የሰውን ነፍስ መያዙን የሚያመለክት ነው፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት በበርካታ ስፍራዎች ማለትም

እንደ ዮሐንስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እና 14፤ ፊሊጵስዩስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 6 እና 7 እና ዕብራውያን ምዕራፍ 2 ከቁጥር 14 እስከ 17 ያሉት ክፍሎች ስለ ትስጉት ይናገራሉ፡፡

በዚህ ትምህርት፣ ከድንግል ስለመወለዱ፣ የዳዊት ዘር ስለመሆኑ፣ መለኮትም ሰውም ስለመሆኑ በመመልከት በኢየሱስ ትስጉት ነገረ-መለኮታዊ ፋይዳ ላይ እናተኩራለን፡፡ ከድንግል ስለ መወለዱ በመመልከት እንጀምር፡፡

## ከድንግል መወለድ

የኢየሱስ እናት ማርያም፣ ኢየሱስን ስትፀንስ፣ ስትሸከምና ስትወልድ ድንግል ነበረች፡፡ እርሱን የፀነሰችው በመንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ጣልቃ ገብነት ሲሆን፣ ኢየሱስን እስከ ወለደችበት ዕለት ድረስም በድንግልና ኖራለች፡፡ እነዚህ እውነታዎች በማቴዎስ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 18 እስከ 25 እና በሉቃስ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 26 እስከ 38 በግልጽ ተቀምጠዋል፡፡

የኢየሱስ ከድንግል መወለድ ቢያንስ ሦስት እንድምታዎች አሉት፡፡ አንደኛው፣ ኢየሱስ ከሴት በመወለዱ፣ እርሱ በእውነት ሰው ነው፡፡

ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ከቁጥር 21 እስከ 28 ባለው ምንባብ መሠረት፣ የእርሱ ፍጥረታት በየወገናቸው እንዲባዙ የእግዚአብሔር መሠረታዊ ስርዓቱ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ የዚህም እውነታ ግልጥ ውጤት ሆኖ የምናገኘው ሰብዓዊ ሴት ዘወትር የምትወልደው ሰብዓዊ ሕፃናትን መሆኑን ነው፡፡ ይህም ማለት ሌሎቹ ሰብዓዊ ሕፃናት እንደሚያድጉት ሁሉ ኢያሱስም በእናቱ ማሕፀን ውስጥ አድጓል፣ ስለዚህም ተክክለኛውን ሰብዓዊ ተፈጥሮ አካልንም ነፍስንም በአንድነት ይዟል፡፡

ከ325 እስከ 389 ዓ.ም. ባለው ጊዜ የኖረው የቁስጥንጥኒያው ጳጳስ ናዚያንሲሳዊው ግሪጎሪ፣ ስለ ኢየሱስ እውነተኛ ሰውነት አስፈላጊነት በ51 ኛው ደብዳቤው እንዲህ ፅፏል፡፡ እስኪ እናድምጠው፡

> *እርሱ የህማም ሰው እንዳልነበረ ሊቆጠር አይገባም... ግማሽ አዳም ብቻ በላዩ ከተገኘ፣ የክርስቶስ ማዳንም ግማሽ ሊሆን ይገባዋል፤ ሆኖም ምሉዕ (አዳማዊ) ተፈጥሮ ከተገኘበት፣ መላው ተፈጥሮው ከአንድያ ልጅነቱ ጋር አንድ ይሆናል እናም ምሉዕ ማዳንንም ያስገኛል፡፡ እንግዲያው፣ በምሉዕ መዳናችን አይቀኑብን አሊያም አጥንት፣ ነርቭና ምሉዕ ሰብዕና የተላበሰውን አዳኝ ይልበሱት፡፡*

ግሪጎሪ የዕብራውያን ምዕራፍ 2 ቁጥር 17 ን ሃሳብ በማስተጋባት፣ የሰው ዘር መዳን ምሉዕ የሰው ዘር ያለው አዳኝ እንደሚፈልግ እውቅና ሰጥቷል፡፡

ሁለተኛ፣ ኢየሱስ በተዓምራት ከመንፈስ ቅዱስ በመፀነሱ ምክንያት፣ ሰብዓዊ ማንነቱ ከኃጢአት የነፃ ነው፡፡ በሮሜ ምዕራፍ 5 ከቁጥር 12 እስከ 19 መሠረት የሰው ዘር በጠቅላላ የመጀመሪያውን የአዳም ኃጢአት ፍሬ ተሸክሟል፡፡ በሮሜ ምዕራፍ 7 ከቁጥር 5 እስከ 24 መሠረት ደግሞ፣ እኛም በዚያ ኃጢአት ረክሰናል ተወርሰናልም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደሚያስቀምጥልን ኢየሱስ ግን ያለ ኃጢአት ተወልዷል፡፡ ይህንንም በ2 ቆሮንቶስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 21 እና 1 ዮሐንስ ምዕራፍ3 ቁጥር 5 ውስጥ የምናገኘው ሲሆን በሉቃስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 35 በመወለዱ ብሥራት ላይም ተመልክቷል፡፡ የነገረ መለኮት ምሁራኑ ኢየሱስ ከሰብዓዊ እናት ተወልዶ ሳለ ከኃጢአት እርኩሰትና ዕዳ ነጻ መሆኑን አስመልክቶ አንድ ምስጢር እንዳለ ቢረዱም፣ ከድንግል መወለዱ ግን ያለ አንዳች እንከን ይህንን ተግባር የፈፀመ መለኮታዊ የእግዚአብሔር ጥበቃና የማጽናት ህላዌ መኖሩን እውቅና ይሰጣሉ፡፡

> *ኢየሱስ የመጣው ኀጢአተኞችን ሊያድን ስለሆነ ከኀጢአት ነፃ ሊሆን ይገባዋል እናም የእውነተኛው አምሳል ጥላዎች፣ ለምሳሌ የብሉይ ኪዳን የመስዋዕቶች ስርዓት፣ ለመስዋዕት የሚቀርቡት እንስሳት በጠቅላላ እንከን አልባ፣ ስህተት የሌለባቸው መሆናቸው ኢየሱስ በእኛ ምትክ ለመሆን ሲመጣ ያለ ኀጢአት መሆኑና እንከን አልባ የመሆኑን አስፈላጊነት ያመለክታሉ፡፡ ኀጢአተኞችን ሊያነፃ የሚመጣ ራሱ ከኀጢአት የነፃ ሊሆን ይገባዋል፡፡ [ዶ/ር ሮበርት ሊስተር]*

> *የብሉይ ኪዳኑን የምትካዊ መስዋዕት አምሳል ለማሳካት፣ መስዋዕቱ ያለ ኀጢአት ፣ ወይንም እንከን አልባ መስዋዕት ሊሆን ይገባል፡፡ እንግዲያው ክርስቶስ በየትኛውም መንገድ የእኛ ኀጢአታዊ ተፈጥሮ ተካፋይ ከሆነ እና ለኀጢአታዊ ባህርይ ተጋልጦ ከተገኘ፣ እርሱ ራሱ ያለምንም ጥርጥር በቅዱሱ በእግዚአብሔር ፊት ምትክ የሚሆንለት አንድ ሰው ያስፈልገው እንደነበር እንደምንገምት አስባለሁ፡፡ ነገር ግን ለብዙዎች አዳኝ ለሚያሻቸው ሰዎች ጠበቃ ሆኖ ለመቆም ያስቻለው አንዳችም በደል ያልተገኘበት መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ ተቃራኒ ያልሆነውና እንዲያውም ደጋፊ የሆነው ሌላ አመለካከት ኢየሱስ የመጀመሪያው አዳም የተሸነፈበትን ሁሉ  በትክክል የፈጸመው ሁለተኛው አዳም እንደሆነ የመረዳቱ ነገር ነው፡፡ አዳም ተሸንፎበት የነበረውን የፍፁም ታዛዥነት ሕይወት፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በትክክል ፈፀመው፡፡ ስለዚህም እርሱን እንደ ሁለተኛው አዳም፣ አሊያም እንደ እንከን አልባና ተገቢ የሆነ የኀጢአት መስዋዕት አድርጋችሁ ተመልከቱት፣ የክርስቶስ ኀጢአት አልባነት የማያወላውል ወሳኝና ስለ መሲሁ የተነገረው መልካም የምሥራች አጅግ አስፈላጊ ውቅረ ነገር ነው፡፡*
> *[ዶ/ር ግሬን ስኮርጂ]*

የኢየሱስ ከድንግል መጸነስና መወለድ ሦስተኛ እንድምታ እርሱ ተስፋ የተገባው ሕዝቡን ከኀጢአትና ከሞት ለማዳን የተላከው እውነተኛ መሲህ መሆኑን ማመልከቱ ነው፡፡ በማቴዎስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 21 ላይ ዮሴፍ ይህንን ትንቢት በህልም ተቀብሏል፡፡

> ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ። (ማቴ 1፥21)

በማቴዎስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 22 እና 23 ደግሞ ማቴዎስ ትንቢቱን በዚህ መንገድ ፈትቶታል

> በነቢይ ከጌታ ዘንድ።
> እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል
> ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል፥ ትርጓሜውም።
> እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው። (ማቴ 1፥22-23)

በዚህ ማብራሪያ መሠረት፣ ማቴዎስ የጠቀሰው ኢሳያስ 7 ቁጥር 14 ሲሆን ይህም የሚያመለክተው የኢየሱስ መወለድ ይህንን ትንቢት በማሟላቱ፣ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ማረጋገጡን ነው፡፡

አንዳንድ ወንጌል አማኝ ምሁራን እንደሚያምኑት ከድንግል ስለ መወለድ የተነገረው ትንቢት በቀጥታ የሚያመለክተው ኢየሱስን ነው ይላሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ወደ ኢየሱስ የሚያመለክተው በተምሳሊትነት ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ሆኖም ሁሉም ወንጌል አማኞች መንፈስ ቅዱስ ተዓምራዊ በሆነ መንገድ ማርያም እንድትፀንስ እንዳደረገ፣ የኢየሱስም ከድንግል መወለድ እግዚአብሔር ህዝቡን ከኀጢአትና ከሞት ለማዳን የሚጠቀምበት በትንቢት የተነገረለት መሲህ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

ከድንግል ከመወለዱ አንፃር የኢየሱስን ትስጉት ከተመለከትን አሁን ደግሞ የዳዊት ዘር መሆኑን እንመልከት፡፡

## የዳዊት ዘር

*በማቴዎስ ምዕራፍ 1 ላይ፣ ማቴዎስ የኢየሱስን የትውልድ ሐረግ እርሱ እንዴት የአብርሃም ልጅ፣ የዳዊት ልጅ እንደሆነ በማመልከት ይጀምራል፡፡ ይህም ለማቴዎስ እጅግ አስፈላጊ ነበር፡፡ በንጉሥ ዳዊት ዘመን እግዚአብሔር መንግሥቱን እንደሚያፀና፣ ግዛቱም እንዴት በምድር ሁሉ እንደሚገለጥ ወደ ኋላ ተመልሰን ብሉይ ኪዳንን ስንመለከት የዚህን ምክንያት በትክክል እንረዳለን፡፡ እናም ዳዊት በእግዚአብሔር ሕዝብ*

*ላይና እግዚአብሔር በመረጠው ስፍራ  የእግዚአብሔርን አገዛዝ የሚያሳይ፣ እግዚአብሔር ሊያመጣ ያለው አገዛዝ ቀዳሚ ተምሳሊት ወይንም ምልከት ነው፡፡ ስለዚህም ኢየሱስ እንደሚመጣና ይህንን አገዛዝ እንደሚያፀና ወደ ኋላ ወደ ብሉይ ኪዳን ተመልሶ መስመሩን መመልከቱ በእውነት አስፈላጊ ነው፡፡ እንግዲህ ይህ አንዱ አስፈላጊ ምክንያት ነው፡፡ ሌላው ምክንያት ደግሞ፣ በብሉይ ኪዳኑ መጽሐፍ በ2 ሳሙኤል 7 ለዳዊት የተገባ የተስፋ ቃል ያለበትና ከእርሱ ወገን አንዱ ዞፋኑ ለዘላለም እንደሚፀናና የእግዚአብሔርን ንጉሣዊ አገዛዝ እንደሚመሠርት የተነገረበት ነው፡፡ ይህ ተስፋ በአንድ በኩል ስንመለከተው በአንድ ወቅት እስራኤል ያለ ንጉሥ በነበረችበት ወቅት ደብዛው ጠፍቶ ነበር፡፡ ለአምስት-ስድስት መቶ ዓመታት ነገሥታት አልነበሩም፡፡ ከዚያ በኋላ ግን ኢየሱስ መጣ፣ በወንጌላትም እንደምናነብበው አሁን በዳዊት ዞፋን የተቀመጠው እርሱ ነው፡፡መሲሁ ሲመጣ፣ ከዳዊት ዘር የሚመጣ መሆኑ እጅግ በጣም ወሳኝና አስፈላጊ ነው፡፡ [ዶ/ር ፒተር ዎከር]*

ኢየሱስ ክርስቶስ ከዳዊት ወገን መሆኑን ማወቅ እጅግ በጣም ወሳኝ ነው ምክንያቱም መሲህ ወይንም ክርስቶስ የመሆንን ሕጋዊ መብት የሚያሰጠው ያ ነውና፡፡ በ10ኛው ዓ.ዓ. እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር ቃል ኪዳን አደረገ፣ ይህም ከዳዊት ዝርያዎች በአንዱ ንግሥና በምድር ላይ የማይሻር መንግሥት እንደሚመሠርት ተስፋ የሰጠበት ነው፡፡ የዚህንም ቃል ኪዳን ማጣቀሻ በ2ሳሙኤል 7 እና በ1ኛ ዜና 17 ላይ እናገኛለን፡፡

የዳዊት በትረ መንግሥት ከሰለሞን ሞት በኋላ ለሁለት ተከፈለ፡፡ ብሉይ ኪዳን ግን ከዳዊት ዘር የሆነው ንጉሥ፣ "መሲህ" ወይንም "ክርስቶስ" መንግሥቱን መልሶ እንደሚገነባ ይተነብያል፡፡ ይህንንም በመዝሙር 89 ቁጥር 3 እና 4፤ 110 ከቁጥር 1 እስከ 7፤ 132 ቁጥር 17 በመሳሰሉት ቦታዎች ላይ እናገኘዋለን፡፡ የዳዊትን በትረ መንግሥት ያድሳል ምርኮኞቹንም ወደ ተስፋዪቱ ምድረ መልሶ ያስገባል፡፡ ለታደሰችውም ሀገር የእግዚአብሔርን ትልቅ በረከት ያመጣል፡፡ እነዚህም ተስፋዎች በብዙ ቦታዎች የተጻፉ ሲሆን፣ ኤርምያስ ምዕራፍ 23፣ 30 እና 33፤ ሕዝቅኤል ምዕራፍ 34 ከቁጥር 20 እስከ 31 እና ምዕራፍ 37 ከቁጥር 20 እስከ 28 ይካተቱባቸዋል፡፡ በማቴዎስ ምዕራፍ 1 እና በሉቃስ ምዕራፍ 3 የተመዘገበው የኢየሱስ የትውልድ ሐረግ ከዳዊት ዘር የሚመጣ መሆኑን አጽንዖት የሚሰጠው ለዚህ ነው፡፡ ዓላማቸውም ኢየሱስ የመሲህነትን ወይንም የክርስቶስነትን ቢሮ ሊቀበል ይገባዋል የሚለውን ማመልከት ነው፡፡

የኢየሱስን ከድንግል መወለድና የዳዊት ዘር መሆኑን ከመረመርን አሁን ደግሞ የያዘውን ጣምራ አንድነት እንዳስሳለን፡፡

## ጣምራ አንድነት

"ጣምራ አንድነት" የተሰኘው ቴክኒካዊ ቃል የሚያመለክተው፡

*ኢየሱስ ሁለት ራሳቸውን የቻሉ ማንነቶች የያዘ (መለኮታዊ ተፈጥሮ እና ሰብዓዊ ተፈጥሮ) አንድ ሰብዕና ነው፡፡ ሁለቱም ተፈጥሮዎች የየራሳቸውን ባሕርያት ይይዛሉ፡፡*

ኢየሱስ ሁለተኛው የስላሴ አካል ነው፡፡ ለዓለምና ለዘላለምም ምሉዕ ባሕርያቶቹን እንደያዘ ምሉዕ መለኮትነትን ተላብሷል፡፡ ሲፀነስና ሰው ሆኖ ሲወለድ፣ በማንነቱ ውስጥ የሰብዓዊ ፍጡርን መሠረታዊ ባሕርያት የያዘ እውነተኛ ሰውነትን ጨመረ፡፡

በ451 ዓ.ም. በኬልቄዶን የተሰበሰበው የሃማኖቶች ጉባዔ፣ ስለ ጣምራ አንድነቱ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ትምህርት ያጠቃለለና የኬልቄዶን የሃይማኖት መግለጫ፣ የኬልቄዶን ምልከት፣ የኬልቄዶን ማብራሪያ በሚሉ የተለያዩ ስያሜዎች የሚጠራውን አንቀጽ አወጣ፡፡

*ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍፁም አምላክ ፍፁምም ሰው ነው፤ እውነተኛ አምላክም፣ እውነተኛ ሰውም ነው፣ አካልም ነፍስም አለው... እኛ ያለን ሁሉ አለው፣ እርሱ ግን ያለኀጢአት ነው... ሁለቱም ተፈጥሮዎቹ፣ ያለመምታታት፣ ያለመለዋወጥ፣ ያለመከፋፈል፣ ያለመለያየት ከአንድነቱ ውስጥ ፈጽመው ሳይነጠሉ፣ የእያንዳንዳቸው ተፈጥሮ እንደተጠበቀ የየራሳቸውን ማንነት ይዘው በፍፁም ስምምነት አንድ አካል አንድ ማንነት ይዞ ይኖራል፡፡*

ይህ ማብራሪያ ወደ ቴክኒካዊነቱ ያደላል፣ ለእኛ ዓላማ ግን በሦስት ክፍሎች እናጠቃልለዋለን፡፡ አንደኛ፣ ኢየሱስ ሁለት ኀላዌ አለው እነርሱም መለኮታዊ ማንነትና፣ ሰብዓዊ ማንነት፡፡

*በጣምራ አንድነት ውስጥ የምንነጋገረው፣ ስለ ተፈጥሮ ነው፡፡ የምንለው ሁለት ተፈጥሮ አንድ ማንነት ተፈጥሮዎቹም በአንድ ማንነት ውስጥ ተስማምተዋል ነው፡፡ "ተፈጥሮ" ስንል የሰብዓዊ ማንነቱ መገለጫ የሆኑ ነገሮች ሁሉ እና መለኮታዊ ማንነቱን ጨምሮ ማለት ነው፡፡ እንግዲያው ሰብዓዊ ተፈጥሮ ሁለት ነገሮችን ያካተተ ሊሆን ይገባዋል እነርሱም አካልና ነፍስ ናቸው ወይንም መንፈሳዊና አካላዊ ንጥረ ነገር ያም እንደ ሰብዓዊ ሰው ለመኖር የሚያስፈልግ ምሉዕ ህላዌ ነው፡፡ መለኮታዊ ማንነቱ ደግሞ ሁሉንም የያዘ ማለት ሲሆን፣ ሁሉንም ኃይል፣ ሁሉንም አምላካዊ ማንነት ያካተተ ነው፡፡ ተፈጥሮ ስንል፣ ኢየሱስ ሁለቱም ኑባሬዎች፣ ሁለቱም የማንነት መገለጫዎችና ሁለቱም አኗኗሮች አሉት ማለታችን ነው፡፡ እናም እርሱ ሙሉ በሙሉ ሰው ነው፣እንደ ሰብዓዊ ሰው ሊቆጠር የሚችልበት ማንኛውም ነገር አለው (ያለ ኀጢአት)፡፡ መለኮታዊ ተፈጥሮ*

*ስንልም፣ ለአምላክነት የሚገባ ማንነት ሁሉ አለው፣ መለኮታዊ ነው ማለታችን ነው፡፡[ዶ/ር ጆን ማኪንሌይ]*

ዘላለማዊው የእግዚአብሔር ልጅ ለአምላክነት ወሳኝ የሆኑ ሁሉንም ባሕርያት ዘወትር ይዟል እንደያዘም ይኖራል፡፡ ለምሳሌ፣ በማንነቱ፣ በጥበቡና በኃይሉ፣ አይወሰንም፣ ዘላለማዊ ነው፣ ኢ-መዋቲ ነው፡፡ በውጤቱም በብሉይ ኪዳን ስለ እግዚአብሔር የተነገረው ነገር ሁሉ ለኢየሱስም እውነት ነው፡፡ ይህም በዮሐንስ 1 ከቁጥር 1 እስከ 3፤ ምዕራፍ 10 ቁጥር 30፤ ዕብራውያን ምዕራፍ 1 ቁጥር 2 እና 3 በመሳሰሉት ምንባቦች ተገልጧል፡፡ ይህም ማለት ኢየሱስ ያለምንም ጥርጥር ፍፁም ክርስቶስ ነው ማለት ነው፡፡ እርሱ ዘወትር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይፈጽማል፣ አንዳችም በደል አይገኝበትም፡፡ እርሱ የተስፋውን ቃል አያጥፍም፣ ለመፈፀምም አያቅተውም፡፡ በመስቀል ላይ ስለ እኛ ሲሞትም የውስጣዊ ማንነቱ እንከን አልባነት ድንበር የለሽና ዋጋ ያለው መስዋዕት ሆኖ እንዲዘልቅ አድርጎታል፡፡

በተመሳሳይ መንገድም፣ ኢየሱስ ለሰብዓዊ ማንነት መሠረታዊ የሆኑ ባሕርያትንም ይዟል ፣ እነርሱም ሰብዓዊ አካልና ሰብዓዊ ነፍስ ናቸው፡፡ እርሱ ለድካም፣ ለአደጋና ለሞት ተጋላጭ የሆነው ለዚህ ነው፤ አካላዊ ውሱንነትም የነበረበትና ሌሎችም በዚህ ምክንያት ነው፡፡ የኢየሱስን ፍፁም ሰውነት እንደ ዕብራውያን ምዕራፍ 2 ቁጥር 14 እና 17፤ ምዕራፍ 4 ቁጥር 15፤ ፊሊጵስዩስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 5 እስከ 7 በመሳሰሉት ምንባቦች ውስጥ ተጽፎ እናነባለን፡፡ የእርሱ ሰውነት እንደ ክርስቶስ ላለው ድርሻ ወሳኝነት አለው፡፡ የዳዊት ዝርያ እንዲሆን ያስቻለው፣ ሰብዓዊ ፍጡራን እንደሚይዟቸውም ቢሮዎች እንደ ነቢይ፣ ካህንና ንጉሥ እንዲይዝ ያበቃው ይኸው ነው፡፡ በዕብራውያን ምዕራፍ 2 ቁጥር 14 እስከ 17 የተጻፈውን ስናነብብ፣ የትክክለኛ ሰው ሞት ብቻ ለሰው ልጆች ስርየት ሊሆን እስከቻለ ድረስ ስለ እኛ ሞቶ ምትካችን መሆን የቻለው ለዚህ ነው፡፡

> *በትስጉት ውስጥ፣ እግዚአብሔር በዘላለም ሃሳብ ወልድን በማርያም ላይ በመጸለልና በመንፈስ ቅዱስም በመፀነስ የእኛን ሰብዓዊ ማንነት እንዲካፈል አደረገው፡፡ እንግዲህ እኛ ሁላችን ከሰብዓዊነታችን ጋር የተዛመዱ ነገሮች አሉን፣ እግዚአብሔርም በአምሳሉ እንደ ሰው ሲፈጥረን መሠረታዊ የሆኑትን ነገሮች ሰጥቶናል፡፡ ኢየሱስም እኛ ሰዎች ያሉን ስሜቶች ሁሉ አሉት፣ የሰው ልቡና አለው፣ በተረዱዋቸው ነገሮች ላይ ተመሥርተው ሰዎች ውሳኔዎችን እንደሚወስኑ ሁሉ እርሱም ይወስን ነበር፡፡ ኤድዋርድ እንደተናገረውም፣ "ይህንን የመረዳታችን የመጨረሻው ጫና የተገለጠው" በመጨረሻ በፈጸመው ተግባር ነው፡፡ ስለዚህም ከእኛ ማንነት ጋር የሚዛመድ ነገር ሁሉ እና እንደ ሰው የምንፈፅመውን ተግባር ሁሉ፣ ኢየሱስም የራሱ አድርጎታል (ከኀጢአት በስተቀር)፡፡ ነገር ግን እጅግ ምስጢራዊ በሆነ መንገድ፣ በእግዚአብሔር በአባቱ ዘንድ የነበረውን ክብር ውጫዊ መገለጫ ትቶ ራሱን ባዶ ቢያደርግም፣ እንደ እግዚአብሔር*

*ልጅ ያሉትን ማዕከላዊ የባህርይ መገለጫዎች ማለትም ዘላላማዊ ማንነቱን አልተወም፡፡ እርሱ ያኔም ሁሉን ቻይ ነበር፣ ሁሉን አዋቂ ነበር፣ እርሱ ያኔም የማይለወጥ ቅድስና ነበረው፣ ቤዝዎት ለምን መከናወን እንዳለበት እንደ እግዚአብሔር ልጅ ፍፁም የሆነ እውቀት ነበረው በተጨማሪም የዘላለማዊ አምላክነቱ ክፍሎች የሆኑትን እነዚህን ነገሮች፣ አንዳቸውንም አልተዋቸውም፡፡ እንግዲያው በጣምራ አንድነት ውስጥ ስላሉ ተፈጥሮዎች ስንጠይቅ፣ መቤዠት የሚያስፈልገው ሰው ስለሆነ እግዚአብሔርም የሰጠን ሰው ነው፡፡ ይህንን የመሰለውን ቤዛነት ሊፈጽም የሚችለውም እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ መለኮት ያስፈልገን ነበር፡፡ እግዚአብሔር አዳኝ ነው፡፡ ስለዚህም በአንድ ማንነት ውስጥ ምሉዕ አምላክነትና ምሉዕ ሰውነት ይኖራሉ፡፡ [ዶ/ር ቶማስ ኔትለስ]*

ሁለተኛ፣ የኬልቄዶኑ የሃይማኖት መግለጫ በኢየሱስ ሁለት ተፈጥሮዎች የየራሳቸው ማንነት አላቸው በሚለው ነገር ላይ ሃሳቡን አስቀምጧል፡፡ ኢየሱስ መለኮትና ሰው የተባሉ ባሕርያትን ያጣመረ ክልስ ተፈጥሮ የለውም፡፡ ሰብዓዊ ባህርያቱ መለኮታዊ ባህርያቱን እንቅፋት አልሆኑባቸውም፤ መለኮታዊ ባህርያቱ ደግሞ በመጠኑም ቢሆን ሰብዓዊ ተፈጥሮው ሻል እንዲል አላደረጉም፡፡ ይልቁኑ ሁለቱም ያለ አንዳች ገደብ የማይለዋወጡ ሆነው ይኖራሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ዮሐንስ የኢየሱስን መለኮትነትና ሰውነት በዮሐንስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 3 እና ምዕራፍ 8 ቁጥር 40 ላይ ባረጋገጠበት መንገድ ውስጥ ይህንን እንመለከታለን፡፡ ኢየሱስ ምንም እንኳን አምላክ ቢሆንም፣ በእውቀት፣ በቁመትና በሞገስ ማደግ ያስፈለገው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ከሰብዓዊ ተፈጥሮው አኳያ ነው መራመድ፣ መናገር፣ ምክንያትን ማቅረብና የመሳሰሉትን ማድረግ ያስፈለገው፡፡ የእግዚአብሔርንም ፈቃድ ማወቅ ያስፈልገው ነበር፡፡ እንግዲህ ኢየሱስ እንደ ክርስቶስ ለሚፈጽመው ተግባር እጅግ ወሳኝ የሆኑት እነዚህ ነገሮች ናቸው ምክንያቱም በዕብራውያን ምዕራፍ 2 ቁጥር 17 እና 18 ላይ እንደምናነብበው ከሰብዓዊነት አኳያ በእውቀትና በሞገስ እንዲያድግ፣ ከዚህም የተነሳ እጅግ ምህረትን የተሞላና በድካማችንም ሊራራልን እንዲችል የሚያደርጉት እነርሱ ናቸውና፡፡

ሦስተኛ፣ የኬልቄዶኑ የሃይማኖት መግለጫ ኢየሱስ አንድ ስብዕና መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

*ስለ ጣምራ አንድነት በምናስብበት ጊዜ፣ በዚያ ቀመር ውስጥ የስብዕና፣ ጥሙርነት፣ ፍቺው ባለቤት ወይም ወኪል ነው፡፡ ሁለቱን ተፈጥሮዎች የያዘ ማንነት ነው፡፡ እንደ እግዚአብሔር፣ አሊያም እንደ ሰው ቢገለጥም፣ እንደ ማንነቱ ከሚከናወኑትተግባራት ሁሉ በስተጀርባ ያለ ላዕላይ እውነታ፣ እርሱ ያው አንድነቱ ነው፡፡ እንግዲያው፣ "ስብዕና" ምንም ይሁን ማን ተፈጥሮን በውስጡ የያዘ ብለን ማሰብ እንችላለን፡፡ ያ አካል የማን ነው? ያ አካል የእኔ ነው፡፡ እኔ ነኝ፡፡ በቃ እኔ ነኝ፡፡ "ስብዕና" እርሱ ነው፡፡ ተፈጥሮ እኔ ያለኝ ነገር ነው፣ ስብዕና ደግሞ ከሌሎችና ከራስ ኀሊና ጋር የሚቆራኘው ጥልቅ እውነታ ነው፡፡ [ዶ/ር ጆን ማኪንሌይ]*

*በትስጉትነት ውስጥ የተገለጠው የእግዚአብሔር ጥበብ፣ ሰዋዊ ፈቃድ፣ መለኮታዊ ፈቃድ፣ ሰዋዊ ስሜት፣ መለኮታዊ ስሜት፣ ሰዋዊ እውቀት፣ ሰዋዊ አለማወቅ ከመለኮት ሁሉን አዋቂነት ጋር በአንድነት የሚኖሩት በዚህ አንድ ስብዕና ውስጥ መሆኑ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ባልተለመደ መንገድ፣ በሰብዓዊነቱ ውስጥ ከሚገኘው ክርስቶሳዊ ተልእኮው አንፃር ታዛዥ እና የተሰጠ ስለ መሆኑ ሲናገር ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ብዙ የምንረዳው ነገር ይኖራል፡፡ በነጠላ ማንነቱ የሚገለጥባቸው አንዳንድ ጊዜዎች አሉ፡፡ እውነት እላችኋለሁ፣ "ኀጢአታችሁን ይቅር እላለሁ፡፡" ኀጢአትን ይቅር የሚል ያለ እግዚአብሔር ማን አለ? እነዚህ ሁሉ የተከናወኑት በአንዱ ሰው፣ በዚያው በአንዱ ገፅታ ነው፡፡ አንድ ጊዜ እንደገና እናንሳው፣ ለቤዛነት ስብዕና ጥምረት ያስፈልጋል፣ ይህም አምላክም ሰውም የተጣመሩበት ጣምራ አንድ ማንነት፡፡ [ዶ/ር ቶማስ ኔትለስ]*

ኢየሱስ ልክ አንድ ሰው መለኮታዊ ስብዕናን በእንግድነት እንዳሳደረ አይነት ሁለት ስብዕናዎች ወይንም ሁለት ልቡናዎች የሉትም፡፡ ወይንም ደግሞ ልክ መለኮታዊ ማንነት በሰዋዊ ማንነት ውስጥ እንደተዳቀለበት አይነት ሁለት ልዩ ልዩ ማንነቶች ቅልቅል ወይም ድቅል አንድነትም የለውም፡፡ በዮሐንስ ምዕራፍ 17 ከቁጥር 1 እስከ 5 እና በቆላስያስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 9 እንደምናነብበው፣ ኢየሱስ ለዘወትር የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ የሚታወቀው ሁለተኛው የስላሴ አካል ነው ሆኖም ይኖራል፡፡ ይህ ነገር እጅግ ወሳኝ ነው ምክንያቱም ኢየሱስ አሁንም በፍፁምነት የትኛውንም መለኮታዊ ብቃት ይገልጣልና፡፡ ለምሳሌ፣ ከሰብዓዊነቱ አንፃር፣ እውቀትን ማወቅ ይገባዋል፡፡ ከመለኮትነቱ ተፈጥሮና ስብዕና አንፃር ደግሞ፣ ዘወትር ሁሉን አዋቂ ነው እንደሆነም ይኖራል፡፡ ኢየሱስ በፍፁምነት መለኮታዊ ባህርያትን በመግለጡ ምክንያት፣ ያለ ጥያቄ ልንታመንበትና ልናገለግለው፣ የገባውንም ተስፋና እቅድ እንደሚፈፅመው ልንደገፍበት እንችላለን፡፡

ፍፁም አምላክ ፍፁምም ሰው ሆኖ የሚኖር ኢየሱስ ብቻ ነው፡፡ ይህም ለእኛ ታላቅ መጽናናትን ይሰጠናል፡፡ ፍፁም ሰው በመሆኑ በድካማችንና በመከራችን ሊራራልንና ሊረዳን ይችላል፡፡ አዳኛችን ሁሉንም አልፎባቸዋልና፡፡ ይህንንም ሕይወት ፈጽሞ ለኀጢአት ባለመረታት ፀንቶ ኖሮታልና እርሱን ሙሉ ለሙሉ እንታመነዋለን እንከተለዋለንም፡፡ ፍፁም አምላክም በመሆኑ፣ እኛን ለማዳን ያለውን ችሎታ ሊነጥቀው የሚችል ምንም ዓይነት ሰብዓዊ ድክመት እንደማይኖርበት ሙሉ መተማመን ይኖረናል፣ የገባልንን ተስፋና እቅድም ለመፈጸም የሚያስችለው የማይገደብ ኃይልም አለው፡፡ ኢየሱስ ፍፁም ሰው ፍፁምም አምላክ በመሆኑ፣ እርሱ እንከን የለሽ ገዢ፣ አማላጅ እና አዳኝ ነው፡፡

ከትስጉትነቱ አንፃር የኢየሱስን መወለድና ዝግጅት ከተመለከትን፣ ወደ ጥምቀቱ ለመሻገር እንዘጋጅ፡፡

## ጥምቀት

የኢየሱስን ጥምቀት ለአገልግሎት እንዲዘጋጅ አስተዋፅዖ ያበረከቱትን ሦስት መንገዶች በመመልከት እንዳስሰዋለን፣ በመጀመሪያ ክርስቶስነቱ የተረጋገጠበት መሆኑን እንዳስሳለን፡፡

# ክርስቶስነቱን አረጋግጧል

በአንድ መንገድ፣ ኢየሱስ የክርስቶስነቱን ቢሮ የያዘው ገና በትሥጉትነቱ ጅማሬ ላይ ነው፡፡ ከዳዊት ሥርወ - መንግሥት ወገን ሆኖ ተወለደ፣ በመላእክትም ክርስቶስነቱ ታወጀ፡፡ በሌሎቹ የስላሴ አካላት ለዓለም እስከታወጀበት እስከ ጥምቀቱ ቀን ድረስ ግን ይህ ሃላፊነቱ ይፋ አልሆነም ነበር፡፡ መንፈስ ቅዱስ በእርግብ አምሳል በላዩ ላይ በመውረድ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ እግዚአብሔር አብም ከሰማያት እርሱ ክርስቶስ መሆኑን በይፋ አውጇል፡፡ ምንም እንኳን መንፈስ ቅዱስም ሆነ እግዚአብሔር አብ በቀጥታ "ክርስቶስ" የሚለውን ቃል በዚያን ወቅት ባይጠቀሙም፣ እግዚአብሔር ግን ለመጥምቁ ዮሐንስ እነዚህ ምልክቶች የሚደርሱለት እርሱ ክርስቶስ መሆኑን አስቀድሞ ገልጦለታል፡፡ የዚህንም ዝርዝር በሉቃስ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 15 እስከ 22፤ ዮሐንስ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 19 እስከ 36 ባሉት ምንባቦች ውስጥ እናገኛለን፡፡ ይህ ማረጋገጫ ከእግዚአብሔር የሆነው ክርስቶስ በመጨረሻ እንደመጣ ለእስራኤልና ለዓለም ሁሉ በይፋ በማወጅ ለአገልግሎቱ ዝግጁ አድርጎታል፡፡

## ለአገልግሎቱ ተቀብቷል

የኢየሱስ መጠመቅ ሁለተኛው ውጤት ለክርስቶስነት አገልግሎቱ የተቀባበት መሆኑ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ተብሎ መጠራቱን አስመልክቶ ከሚነሱ ተቃውሞዎች አንዱ ለመሲህነት አገልግሎት በዘይት አልተቀባም የሚለው ነው፡፡ ነገር ግን ወንጌላት ከመዘገቡት እንደምንረዳው ኢየሱስ ሲጠመቅ በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቋል፡፡ ይህ ይፋ የሆነ ቅባት ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ ታውጆበታል፣ ለአገልግሎትም ኃይልን ተቀብሎበታል፡፡ የክርስቶስነት ቢሮ ግን ሰብዓዊ ነበር፡፡ ስለዚህም፣ ሊያድናቸው የመጣላቸውን ሰዎች ይመስል ዘንድ ኃይሉንና ክብሩን ሰውሮ ነበር፡፡ ልክ እንደሌሎቹ እንደተቀቡ ሰዎች ሁሉ፣ ኢየሱስም ለአገልግሎቱ ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይደገፍ ነበር፡፡ ይህንንም እንደ ሉቃስ ምዕራፍ 4 ከቁጥር 1 እስከ 14 እና የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 10 ቁጥር 38 በመሳሰሉት ቦታዎች እናገኘዋለን፡፡

እስኪ ዮሐንስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 34 ኢየሱስ ከመንፈስ ቅዱስ ስለተቀበለው ኃይል የሚናገረውን አድምጡ፡

> እግዚአብሔር የላከው የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራልና፤ እግዚአብሔር መንፈሱን ሰፍሮ አይሰጥምና። (ዮሐንስ 3፥34)

## ጽድቅን ፈጸመ

አሁን ደግሞ ቀጥለን የምናነሳው የኢየሱስ መጠመቅ ሦስተኛ ውጤት ሲሆን እርሱም ጽድቅን መፈጸሙ ነው፡፡ ኢየሱስ ሊጠመቅ ወደ መጥምቁ ዮሐንስ ሲመጣ፣ ዮሐንስ ተቃወመው ምክንያቱም ኢየሱስ ቀድሞም ጻድቅ ነበረና፡፡ ኢየሱስ በፍፁም ኃጢአትን አድርጎ አያውቅም፣ ስለዚህም ንስሓ መግባት አያስፈልገውም ነበር፡፡ ኢየሱስ ግን በግሉ ጻድቅ ብቻ መሆን እንደማይበቃ፤ እርሱ ሊያደርገው የተገባውን የጽድቅ ሥራ ሁሉ መፈጸም እንደሚገባው በመናገር ምላሽ ሰጠ፡፡ በማቴዎስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 14 እና 15 ላይ ያደረጉትን ውይይት አድምጡ፡፡

> ዮሐንስ ግን። እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን? ብሎ ይከለክለው ነበር።
> ኢየሱስም መልሶ፦ አሁንስ ፍቀድልኝ፤ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና አለው። ያን ጊዜ ፈቀደለት። (ማቴዎስ 3፥14-15)

የኢየሱስ ጥምቀት ወሳኝነት ግልጽ የሚሆንልን በእርሱ ዘመን ያጠምቅ የነበረው ዮሐንስ ብቻ እንዳልነበር ስንረዳ ነው፡፡ ዮሐንስን ጨምሮ፣ የተለያዩ የአይሁድ ቡድኖች ራሳቸውን ከኢየሩሳሌም ርኩሰት ለይተው የእስራኤል የጽድቅ ቅሬታዎች አድርገው ይቆጥሩ ነበር፡፡ በተደጋጋሚም አባሎቻቸውን ለመቀስቀስ ይጠቀሙ የነበረው ጥምቀትንና መታጠብን ነበር፡፡ ስለዚህ፣ ኢየሱስ በዮሐንስ ሲጠመቅ፣ አስፈላጊ የሆነውን የጽድቅ ተግባር በመፈፀም በእስራኤል ካሉት ታማኝ ቅሬታዎች ጋር ራሱን አመሳስሎ፣ የጽድቁንም ተግባር አረጋግጦ ነበር፡፡

የኢየሱስን መወለድና ዝግጅት ከትሥጉትነቱና ከጥምቀቱ አንፃር ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ትኩረታችንን ወደ እርሱ መከራ እናዞር፡፡

# መከራ

የኢየሱስ የመከራ ታሪክ በሁሉ ዘንድ የታወቀ ነው፡፡ ዝርዝሮቹም በማቴዎስ ምዕራፍ 4 ከቁጥር 1 እስከ 11 እና ሉቃስ ምዕራፍ 4 ከቁጥር 1 እስከ 13 ውስጥ ተመዝግበዋል፡፡ ጠቅለል ስናደርገው ግን፣ ኢየሱስ በሰይጣን ከመፈተኑ በፊት ለአርባ ቀናት ወደ ፆመበት ወደ ምድረበዳ መንፈስ ቅዱስ ወስዶት ነበር፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ በስጋው ድክም ባለበት ጊዜ እንኳን፣ በመንፈስና በአዕምሮ ብርቱ ነበር፡፡ እጅግ ተርቦ እያለ እንኳን፣ መለኮታዊ ኃይሉን የእርሱን ፍላጎት

ለማሟላት መጠቀምን እምቢ አለ፡፡ ሥልጣኑ እያለው እንኳን፣ የእርሱን ጥቅም ለማስከበር ሲል ሥልጣኑን ማሳየት አልፈለገም፡፡ ዓለምን ለአብ የመማረክ ግብ ቢኖረውም እንኳን የእግዚአብሔርን ጠላት በማገልገል የሚገኘውን ቀላል የሚመስል የኀጢአት መንገድ እምቢ አለ፡፡

በርካታ የነገረ-መለኮት ምሁራን በሰይጣን የተፈተነውን የኢየሱስን ፈተና በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 አዳምና ሔዋን በኤደን ገነት ከተፈተኑበት ጋር ያስተያዩታል፡፡ ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ 5 ከቁጥር 12 እስከ 19 እንዳመለከተው፣ ልክ እንደ አዳም ሁሉ፣ ኢየሱስ የሕዝቡ ወኪል ነበር፡፡ አዳም ወደቀ በጠቅላላው የሰው ዘር ላይም እርግማንን አመጣ፣ ኢየሱስ ግን ፈተናውን ተቋቁሞ፣ ለሕዝቡ ሁሉ ድነትን አመጣ፡፡

> ኢየሱስ ተፈትኗል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረውም፣ እኛ እንደምንፈተነው ሁሉ በሁሉ ተፈትኗል፣ ሆኖም አንዳችም ኀጢአት አልተገኘበትም፡፡ መከራ ብለን ስንል ወይንም የምድረበዳው ፈተና ስንል፣ ከጥምቀቱ በኋላ ይፋ አገልግሎቱን ሊጀምር ሲል ተለትሎ የመጣውን ባለሦስት ፈርጅ ፈተናና ኢየሱስ ከሰይጣን ጋር ፊት ለፊት የተፋለመበትን እንደሆነ ማንም ይህን ማሰብ አይሳነውም፡፡ አብዛኛዎቻችን ሰይጣንን በቀጥታ ገጥመነው አናውቅ ይሆናል ምክንያቱም ከእርሱ ጀሌዎች አንዱ ይበቃናልና፤ ለኢየሱስ ግን ሰይጣን ራሱ በአካል መምጣት ነበረበት፡፡ ግን በዚህ ወቅት ብቻ ነው የተፈተነው ብሎ ማሰብ ስህተት ነው፡፡ የኢየሱስ ሕይወት በፈተና የተሞላ ነበር፡፡ እነዚህ ፈተናዎች ግን እጅግ የበዙና በማንነቱና በተልዕኮው ላይ በቀጥታ ያነጣጠሩ ነበሩ፡፡ ነጥቡ፣ እኔ እንደማስበው፣ኢየሱስ ወኪላችን መሆኑ፣ ምትካችን መሆኑ፣ ሁለተኛውና የመጨረሻው አዳም መሆኑ ነው፡፡ እናም ስለዚህ፣ አዳም በገነት እንደተፈተነ ሁሉ፣ የመጨረሻውም አዳም እንዲሁ፣ በእባቡ መፈተን ነበረበት፡፡ የእኛ ወኪል ከሆነ፣ እኛ እንደምንፈተነው ሁሉ እርሱም በሁሉ ሊፈተን ይገባዋል፡፡ ያ ካልሆነ ምትካችን ሊሆን አይችልም፡፡ ኢየሱስ በአገልግሎቱ ዘመን ሁሉ በኀጢአት የወደቀበት አንድም ጊዜ እንደሌለ ቅዱሳት መጻሕፍት በጣም በግልጽ ያስቀምጣሉ፡፡ እርሱ ያለ ኀጢአት ነበር፡፡ እርሱ በሃሳብ፣ በንግግር እና በድርጊትም ያለ ኀጢአት ነበር፡፡ ነገር ግን የእኛን ኀጢአት የመሸከምንና ምትካችን የመሆንን ዓላማ ለማሳካት መፈተኑ አስፈላጊ ነበር፡፡ [ዶ/ር ዴሪክ ደብልዩ. ኤች. ቶማስ]

በዚህ ትምህርት ያነገብነውን ዓላማ ለማሳካት፣ በኢየሱስ መፈተን ሦስት ገፅታዎች ላይ እናተኩራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ በመፈተኑ መታዘዝን ተማረ፡፡

# መታዘዝ

ዕብራውያን ምዕራፍ 5 ቁጥር 8 እና 9 እንደሚናገረው፡

> ምንም ልጅ ቢሆን፥ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ፤ ከተፈጸመም በኋላ በእግዚአብሔር እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ሊቀ ካህናት ተብሎ ስለ ተጠራ፥ ለሚታዘዙለት ሁሉ የዘላለም መዳን ምክንያት ሆነላቸው።

ኢየሱስ ተጀምሮ እስኪጨረስ ያለ ኀጢአት ነው፤ እግዚአብሔርን አልታዘዝ ብሎ አያውቅምም፡፡ ሆኖም ግን እርሱ ፍፁም እና በእርግጥ ሰው ነበር፡፡ እንግዲያው፣ በሕይወቱ ዘመን የሚያልፍባቸውን መከራዎችና ተግዳሮቶች በማሸነፍ የእግዚአብሔርን የጽድቅ ጥያቄ መሟላትን ሊማር ግድ ነበር፡፡ በስቃይ ያለፈባቸውን መከራዎች ስንመለከት፣ የእግዚአብሔርን ህግ በመፈፀም እና አብ በእርሱ ሕይወት ውስጥ ላለው ፈቃድ ፈጽሞ በመሰጠት ኢየሱስ እግዚአብሔርን ታዘዘ፡፡ ይህም መታዘዙ በክርስቶስነቱ ለሚሠራው ሥራ አዘጋጀው፣ በዕብራውያን ምዕራፍ 5 ቁጥር 9 ላይ እንደምናነብበው፣ እግዚአብሔር የሚቀበለው መስዋዕት እንዲሆን አብቅቶታል፣ ስለዚህም እርሱ የዘላለም ድነት ምንጭ ሆኗል፡፡

# ድካምን መረዳት

ሁለተኛው የምናነሳው ሃሳብ የኢየሱስ መከራ የሕዝቡን ድካም እንዲረዳ ያደረገው መሆኑን ነው፡፡ ኢየሱስ ለመከራው እጁን አልሰጠም፡፡ ሆኖም ግን ምሬቱን ቀምሶታል፡፡ ሰይጣን ያቀረበለት ግብዣ ሰው ሁሉ የሚጓጓለት እንደሆነ አውቋል በፆም የደከመ ሰውነቱም ለእነርሱ ያለውን መሻት ያባብሰዋል፡፡ ይህም ልምምዱ በሕይወታችን በሚገጥሙን መከራዎች የምናደርገውን ትግል እንዲረዳ እና እንዲራራልንም አድርጎታል፡፡ ዕብራውያን ምዕራፍ 4 ቁጥር 15 እንዲህ ይነበባል፡

> ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ፥ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም። (ዕብ 4፥15)
>
> *ኢየሱስ የኀጢአትን ፈተና ተጋፍጧል ተቋቁሟልም፣ ይህም ለክርስቲያኖች ትልቅ መጽናናትን ያመጣል ምክንያቱም እርሱ በሁሉ መንገድ ፍፁም ሰው ነውና፡፡ ኢየሱስ ተፈትኗል ሆኖም ግን አልተሸነፈም፡፡ ኢየሱስ የፀናባቸው ነገሮች ሁሉ ክርስቲያኖች ከፈተናዎች ጋር ሲጋፈጡ ሊያደርጉ የሚገባቸው ነገር ተምሳሊት ይሆናቸዋል፡፡ [ዶ/ር ሲሞን ቫይበርት]*

*ኢየሱስ ስለተጋፈጠውና ስለተቋቋመው የኀጢአት ፈተና ስናወሳ ዕብራውያን ምዕራፍ 4 ረዘም ያለ ማብራሪያ ይሰጠናል፡፡ ክፍሉም ከሚያነሳቸው ነገሮች አንዱ አብዛኛዎቻችን ክፉን ለማድረግና የተሳሳተን ነገር ለመሥራት ስንገፋፋ እኛ ብቻ ያ ነገር የደረሰብን አስታዋሽም የሌለን ብቸኞች እንደሆንን የሚሰማን መሆኑን ነው፡፡ እንደ እውነቱም፣ ኢየሱስ በምድር ሕይወቱ መፈተን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ጠንቅቆ ያውቃል፣ እናም ዛሬ በሰማያዊ ስፍራ የእኛ ሊቀ ካህን ሆኖ ሲቀመጥ ይህንን መረዳት ይዞ ነው፡፡ ስለዚህም ብቻችንን እንዳይደለን እናውቃለን፣ ኢየሱስ የማያውቀውና የማይረዳው እኛ ገና የምናስረዳው ምንም ነገር የለም እርሱ ሁሉን ያውቀዋል፡፡ ስለዚህም በምናልፍበት ሁኔታ ውስጥ የእኛ ረዳት ሊሆን ዘወትር ዝግጁ ነው፡፡ [ዶ/ር ጀምስ ዲ. ስሚዝ ሳልሳዊ]*

# እንከን የለሽነት

ስለ ኢየሱስ መፈተን የምናነሳው ሦስተኛው ሃሳብ እንከን የለሽነቱ ነው፡፡ እንከን የለሽነት የሚለው ቃል በዚህ አውድ መሠረት ኀጢአትን ሊያደርግ አለመቻሉ ነው፡፡ ለበርካታ ምዕተ ዓመታት ክርስቲያኖች ኢየሱስ ኀጢአት የለሽ የመሆኑን እውነታ በብርቱ ሲጠቅሱት ኖረዋል፡፡ የነገረ-መለኮት ምሁራን ስለ ኢየሱስ እንከን የለሽነት ሲያወሱ በተደጋጋሚ ከፈተናው ጋር በማያያዝ ያነሱታል ምክንያቱም በእርሱ ሕይወት ቢሆን ቢሆን ኃጢአት ሊሠራ የሚችልበት ወቅት ያ ወቅት ነበር፡፡

ኢየሱስ ፈጽሞ ኃጢአት አለመሥራቱን ሁሉም ክርስቲያኖች ይረዳሉ፡፡ ለፈተና አልተሸነፈም ወይም የክፋት ሃሳብ ወይም ምኞት ፈጽሞ አልነበረውም ወይንም አንድም እንኳን የኃጢአት ቃል አልወጣውም፡፡ የእርሱ ኃጢአት የለሽነት 2 ቆሮንቶስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 21፤ ዕብራውያን ምዕራፍ 4 ቁጥር 15 እና ምዕራፍ 7 ቁጥር 26፤ 1ጴጥሮስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 22፤ እና 1 ዮሐንስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 5 በመሳሰሉ ምንባቦች ውስጥ ተረጋግጧል፡፡ ኃጢአት ሊሠራ አለመቻሉ ደግሞ ሌላው እውነት ነው፡፡ ከዚህ ቀደም እንደተመለከትነው ኢየሱስ የስላሴ ሁለተኛው አካል ነው፡፡ አምላክ ኃጢአት አይሠራም፣ ምክንያቱም ለማንነቱ ተፃራሪ የሆነ ተግባር ሊፈፅም አይችልም፡፡ የእግዚአብሔር ሦስቱም አካላት ኃጢአትን አድርገው አያውቁም ሊያደርጉም አይችሉም፡፡ ይህንንም በእንባቆም ምዕራፍ 1 ቁጥር 13፤ ያዕቆብ ምዕራፍ 1 ቁጥር 13፤ 1ዮሐንስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 5፤ እና በሌሎችም በርካታ ስፍራዎች ውስጥ እናገኘዋለን፡፡

ሆኖም ግን ይህ የክርስቶስን መከራ እውንነት ሊያሳንሰው  አይችልም፡፡ ከሰብዓዊ ተፈጥሮው የተነሣ፣ በሰብዓዊነት አተያይ ኢየሱስ መከራን ተቀብሏል፡፡ ለእርሱ የሚደረጉለትን ነገሮች ዋጋ ይሰጣቸው ነበር፣ የሚስገኙለትን ጥቅም በውል ይረዳ ነበር፡፡ ስለዚህም፣ በምንም መንገድ የእርሱ መታዘዝና የሰዎች ችግር ተካፋይነቱ አንሶ ሊታይ አይችልም፡፡ እንዲያውም፣ ኢየሱስ እንከን የለሽ በመሆኑ ምክንያት፣ የእርሱ መታዘዝና የሰው ችግር ተካፋይነቱ በውል ይጨምራል፣

ያለ አንዳች እንከን ከመታዘዙ የተማረ ከሆነ፣ መሻታችንን ሙሉ ለሙሉ በሚያሟላ መንገድ ለእኛ አሁን ምላሽ ይሰጠናል፡፡

የኢየሱስ የመወለድና የዝግጅት ወቅቶች በወንጌላት በጥቂቱ ከመቀመጣቸው የተነሳ አንዳንድ ጊዜ ቸል ይባላሉ፡፡ ነገር ግን እጅግ ጠቃሚ የሆኑ በርካታ እውነቶችን ይዘዋል፡፡ ከነዚህም እጅግ የሚልቀው ተስፋ የተገባውና በእግዚአብሔር የተቀባው የመጣ መሆኑ መረጋገጡ ነው፡፡ ለክርስቶስነት አገልግሎት ኢየሱስ መወለዱና መዘጋጀቱ የእግዚአብሔርን ታላቅ ፍቅርና ምህረት ይገልጣል፣ ምክንያቱም እርሱ የኃጢአትና የሞት እስረኞች እንድንሆን አልፈቀደም፣ ይልቁኑ አንድ ልጁ ለእኛ ክርስቶስ ይሆንልን ዘንድ በመላክ ተስፋውን ፈፀመ፡፡

ከመወለዱና ከዝግጅቱ አንፃር የኢየሱስን የክርስቶስነት ሃላፊነት ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ የአደባባይ አገልግሎቱን እንመለከታለን፡፡

# 3. የአደባባይ አገልግሎት

የዚህን ትምህርት ዓላማ ለማሳካት፣ የአደባባይ አገልግሎቱን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ወደ ኢየሩሳሌም በድል እስከገባበት ጊዜ ድረስ ያለውን የኢየሱስን አገልግሎት እናብራራለን፡፡ አንድ ጊዜ አሁንም በዚህ ወቅት የተከናወኑትን ዝርዝር ተግባራት ከመመልከታችን አስቀድሞ ጠቅለል አድርገን እንመለከታቸዋለን፡፡

ኢየሱስ የአደባባይ አገልግሎቱን ሲጀምር ዕድሜው ሰላሣ እንደነበር የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 3 ቁጥር 23 ይነግረናል፡፡ ሁሉም ወንጌላት በተለይም ዮሐንስ የሚሰጡንን ፍንጮች መሠረት በማድረግ፣ አብዛኛዎቹ ምሁራን የኢየሱስ የአደባባይ አገልግሎት ለሦስት ዓመታት ያህል እንደዘለቀ ይስማማሉ፡፡ በተለይም፣ በዮሐንስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 23፤ ምዕራፍ 6 ቁጥር 4፤ በምዕራፍ 11 ቁጥር 55 እና በምዕራፍ 5 ቁጥር 1 እንደምንመለከተው፣ ኢየሱስ በዚህ ወቅት ሦስት ወይም አራት የፋሲካ በዓላትን እንደተካፈለ ዮሐንስ ይጠቅሳል፡፡

በማቴዎስ ምዕራፍ 4 ቁጥር 13 እስከ 17 መሠረት፣ ኢየሱስ የአደባባይ አገልግሎቱን የጀመረው ከገሊላ ባሕር ሰሜናዊ ምሥራቅ አቅጣጫ፣ በገሊላ አውራጃ በምትገኘው የቅፍርናሆም ከተማ ነው፡፡ በማቴዎስ 4 ቁጥር 23 እና 24 እንደምንመለከተው፣ በገሊላ አውራጃና በሌሎችም የእስራኤል ከተሞች ሁሉ እየተዘዋወረ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሰብኳል ተዓምራትንም አድርጓል፡፡ በማቴዎስ ምዕራፍ 10 እና በማርቆስ ምዕራፍ 3 እንደተመዘገበውም፣ በዚህ ወቅት ዐሥራ ሁለቱን ደቀመዛሙርት መርጦ በእግዚአብሔር መንግሥት አዋጅ ውስጥ እንዲሳተፉ አድርጓል፡፡ በኋላም አገልግሎቱን ሰማርያንና ይሁዳን ጨምሮ ወደ ሌሎች የእስራኤል ክልሎች አስፋፍቷል፡፡ በአደባባይ አግልግሎቱ ማብቂያም

ላይ፣ ኢየሱስ ሊሰቀል በዓላማ ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዟል፡፡ በእግረ መንገዱም፣ ኢየሱስ ለማዳን በተቀባባት በዚያችው መንግሥት ሕዝቦች ሊገደል እንዲገባው ደቀመዛሙርቱን ያዘጋጃቸው ነበር፡፡

ምንም እንኳን የኢየሱስ ዋነኛ አገልግሎት የእግዚአብሔር መንግሥት ስለ ቀረበች የንስሃንና የእምነትን መልካም የምሥራች መስበክ ቢሆንም፣ ይህን ግን በስፋትና በተለያየ መንገድ የማከናወን ነፃነት ነበረው፡፡ የተለያዩ ዓይነት ሰዎችን አገልግሏል፣ አብዛኛዎቹን እስራኤላውያንን ተጋፍጧል፣ ማለትም የሃይማኖት መሪዎችን፣ ማኅበረሰብ ያገለላቸውን፣አህዛብን እና ሌሎችንም ዓይነት ኃጢአተኞች ማለት ነው፡፡ በበርካታ ሺዎች ከሚቆጠሩት አንስቶ፣ በግለሰብ ቤት እና ግለሰቦችንም ጨምሮ የተለያዩ ቡድኖችን አግኝቷል፡፡ በተለያዩ ቦታዎች ማለትም በግለሰብ ቤቶች፣ በምኩራቦችና በገላጣ ስፍራዎች ሁሉ አገልግሏል፡፡ መጠነ ሰፊ የሆኑ የማስተማሪያ ስልቶችንም ተጠቅሟል፣ ለምሳሌ፣ ምሳሌዎች፣ መጠይቆች፣ ትንቢቶች፣ ስብከቶችና አልፎም ተዓምራት ይጠቀሳሉ፡፡ በሁሉም አቅጣጫ፣ እርሱ በልዩ ሥልጣን ያገለግል እንደነበረ ሰዎች ተረድተው ነበር፡፡ ስለዚህም ይጋፈጡት የነበሩት አንዳንዶቹ በማመንና በንስሓ፣ የተቀሩት ደግሞ በቁጣና ባለመቀበል ነበር፡፡

ወንጌላት ስለ ኢየሱስ የአደባባይ አገልግሎት እኛ ከዚህ በታች በጥቂቱ ለመግለጽ ከምንሞክረው በላቀ መንገድ ብዙ መረጃዎችን ይሰጡናል ለአሁኑ ግን፡ በመጀመሪያ፣ ስለ ኢየሱስ የወንጌል አዋጅ፣ ሁለተኛ፣ ስለ ገለጠው ኃይል፣ ሦስተኛ ደግሞ፣ ለክርስቶስነት አገልግሎት ስለ መቀባቱ ማረጋገጫ በጥቂቱ እንመልከት፡፡ በመጀመሪያም ኢየሱስ ስለ ሰበከው ወንጌል እንመልከት፡፡

## ወንጌል

ኢየሱስ ወንጌልን በብዙ መንገድና ቅርጽ ሰብኳል፣ ጥቂቶቹ በጣም የረቀቁ፣ ሌሎቹ ደግሞ ቀጥተኛ ናቸው፡፡ ምሳሌዎችን፣ ስብከቶችን፣ የንግግር ልውውጦችን፣ የበረከት ትንቢቶችን እና የፍርድ መልእክቶችን፣ የወደፊት ሁነቶችን፣ ጸሎቶችን እና ተዓምራትንም ጭምር ይጠቀም ነበር፡፡ የወንጌላቱ ፀሐፊዎች ግን መልእክቱን ሲያጠቃልሉ፣ ከምትመጣው የእግዚአብሔር መንግሥት አንፃር የንስሓ ጥሪ ከማቅረቡ አገልግሎት ጋር በዋናነት ያያይዙታል፡፡ እስኪ በማቴዎስ ምዕራፍ 4 ቁጥር 17 ስለ ኢየሱስ ወንጌል የተፃፈውን ማጠቃለያ አድምጡ፡

> ከዚያ ዘመን ጀምሮ ኢየሱስ፡- መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያለ ይሰብክ ጀመር። (ማቴ 4፥17)

በተመሳሳይ መንገድም ማርቆስ በወንጌሉ ምዕራፍ 1 በቁጥር 14 እና 15 ላይ ስለ ኢየሱስ መልእክት ገልጧል፡፡ ማቴዎስም ተመሳሳዩን የወንጌል መልእክት መጥምቁ ዮሐንስ እንዳስተላለፈ በማቴዎስ ምዕራፍ 3 ቁጥር ሁለት ላይ ጽፏል፡፡

በመቀጠል ስለ ሁለቱ የኢየሱስ ወንጌል ገፅታዎች እንመለከታለን፡፡ መጀመሪያ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ስለመምጣቷ ያስተላለፈውን መልእክት፤ ሁለተኛ፣ ለአጣዳፊ ንስሓ ያደረገውን ጥሪ እንመለከታለን፡፡ በመጀመሪያ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ኢየሱስ ያስተማረውን እንመልከት፡፡

## መንግሥት

*ወንጌላትን ከፍተን ማንበብ ስንጀምር፣ በአግራሞት እንድንሞላ የሚያደርገንና በኋላም ልባችንን ያለ ጥርጥር ሰንጎ የሚይዘው አንድ ነገር፣ ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት በፍፁም ግልጥነት ያስተማረውና በአኗኗሩም ያሳየው እውነት ነው፡፡ የኢየሱስን አገልግሎት ያመለከት ከነበረው ከመጥምቁ ዮሐንስ ስብከትና ከኢየሱስ የመጀመሪያ ቃላት፣ እንደምንረዳው ማለትም፣ "የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናት" ወይም "የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች" ወይም "መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች" የሚሉትና በሌሎቹም ቀጣይ ትምህርቶቹ ሁሉ፣ "በመንፈስ ድኆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና" የሚሉትን ጨምሮ፣ ስለመንግሥተ ሰማያት የተናገራቸው ምሳሌዎች፣ በአህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም በመግባት ከዳዊት ዘር የሆነው ንጉሥ ስለ መሆኑ ራሱን ያሳየበት መንገድ፣ ወንጌላት፣ ወንጌላውያን፣ የወንጌል ፀሐፍት፣ ያለምንምንም ጥርጥር እንድንረዳ የሚፈልጉት የኢየሱስ መልእክት፣ አጠቃላይ ሕይወቱ ሁሉ በጠቅላላ ስለ እግዚአብሔር ንግሥና ወይንም ስለ እግዚአብሔር መንግሥት መሆኑን ያሳያሉ፡፡ [ዶ/ር ጆናታን ፔኒንግተን]*

በእርሱ ዘመን እንደነበሩ አይሁድ ሁሉ፣ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ሁሉ ላይ ዘላለማዊ ሉዓላዊ መሆኑን ያውቃል፡፡ ብሉይ ኪዳን በተጨማሪም በምድር ላይ በሚመሠርተው መንግሥቱ ዘላለማዊ ንግሥናው እንደሚገለጥ ያመለከተናል፡፡ ቀደም ባሉት ትምህርቶቻችንም፣ ይህንን ሂደት የጀመረው ዓለምን ፈጥሮ አዳምንና ሔዋንን ምክትል ገዢዎቹ አድርጎ ሲያስቀምጣቸው መሆኑን ተመልክተናል፡፡ እንርሱ ግን ዓለምን ለማስዋብ ለመግዛት የተሰጣቸውን አደራ ባለመወጣት ወደቁ፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ግን እንደገና ወደፊት በመግፋት ታላቅ መንግስት በሆነችው በእስራኤል ውስጥ ተገለጠ፡፡ ሆኖም ግን እንደገና በእስራኤል በደል ምክንያት በመጣው ግዞት ወደ ኋላ ተጎተተ፡፡ ምንም እንኳ እግዚአብሔር በዕዝራና በነህምያ አማካይነት መንግሥታቸውን ቢያድስም፣ የሕዝቡ አለመታመን ግዞቱ ለበርካታ ምዕተ ዓመታት እንዲራዘም አድርጎታል፡፡ በኢየሱስም ዘመን፣ እስራኤል በግዞት

በርካታ ዓመታትን አሳልፋ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ከነበረከቱ በምድር ላይ በሙላት የሚመልሰውን ክርስቶስን በመጠባበቅ ላይ ነበረች፡፡ ስለዚህም፣ መንግሥተ ሰማያት በመካከላችሁ ናት የሚለውን የምሥራች ኢየሱስ ሲያውጅ፣ አስደናቂ ተስፋን የፈነጠቀ መልእክት ነበር፡፡

ኢየሱስ በእርሱ ዘመን የእግዚአብሔር መንግሥት የመጨረሻው እርከን በምድር እንደመጣች መልካሙን የምሥራች አወጀ፡፡ የምንግሥተ ሰማያትም ስርዓት በመላው ዓለም በይፋ እንደሚታይ ተገለጠ፡፡ በማቴዎስ ምዕራፍ 5 ከቁጥር 3 እስከ 12 ያለውን ስንመለከት፣ የታመኑት የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሁሉ በእግዚአብሔርን መንግሥት ውስጥ ይባረካሉ፡፡ መከራዎቻቸውም ያከትማሉ፣ ምድርንም ይወርሳሉ፡፡ የትኛውም ባዕድ ኃይል በሃሰት አምልኮ አይማርካቸውም፡፡ ለፀጥታና ለሰላም በሚልም ሰበብ የትኞቹም ሙሰኛ የሃይማኖት መሪዎች ከእስራኤል ጠላቶች ጋር ሊደራደሩ አይችሉም፡፡ ኃጢአተኞች ይቅር ይባላሉ፡፡ ግዞተኞቹም ነፃ ይወጣሉ፡፡ በደዌና በሕማም እርግማን ውስጥ ያሉት ይፈወሳሉ፡፡ ጌታ ራሱም የእስራኤልን ጠላቶች ያሸንፋል፣ ሰዎችንም ከኃጢአታቸው ያነፃል ፍጥረትንም በጠቅላላ ያድሳል፡፡

ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ኢየሱስ ያስተላለፈው መልእክት አስደናቂ የመሆኑን ያህል፣ ቅድመ ሁኔታም ነበረው፡ ንስሓ፡፡

## ንስሓ

የእግዚአብሔር መንግሥት ፈጥና እንደምትመጣና የእግዚአብሔርንም ታማኝ ሕዝቦች እንደምትባርክ ብቻ ሳይሆን፣ በጠላቶቹም ላይ ፍርድን እንደምታመጣ ኢየሱስ አስጠንቅቋል፡፡ እንግዲያው፣ እስራኤል ይህንን የበረከት ተስፋ መቀበል ከፈለገች፣ ንስሓ ልትገባ ይገባታል፡፡

> *ንስሓ መግባት ከኃጢአት ፊትን መመለስን ያካትታል፡፡ እንደ ወንጌላውያን የንስሓ ዘይቤም፣ ከአንድ ነገር መመለስ ብቻም አይደለም፡፡ ይልቁኑ ወደ አንድ ነገርም ፊትን መመለስ እንጂ፡፡ ያም አንድ ነገር አንድ ሰው ነው፡፡ እርሱም ኢየሱስ ነው፣ ወደ እርሱ በእምነት ዘወር ልንል ይገባል፡፡ ስለዚህ፣ ኃጢአትን በመተው ወደ ክርስቶስ በእምነት ዘወር ማለት ይገባል፡፡ በዚያውም፣ ንስሓ ምን ምን ነገሮችን እንደሚያካትትና ምን እንደሚመስል በተለያየ ደረጃ ልንመለከት ልናስብበትና ልንጠየፈውም ይገባል፡፡ ከነዚህም አንዱ ስለ ኃጢአት አዕምሮአዊ እውቀት መጨበጥ ነው፡፡ በአንድ በሆነ መንገድ ወይንም ቅርፅ የእግዚአብሔርን ሕግ እንደተላለፍኩ ካልተረዳሁ ራሴን እንደኃጢአተኛ ልቆጥር የምችልበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ ከዚያም ባለፈ የፈጸምኩት*

*ተግባር እግዚአብሔርን ደስ እንደሚያሰኝ እኔ ግን ለጉዳዩ ግድ እንዳልሰጠኝ በጽንሰ-ሃሳብ ደረጃ የሚረዳ አንድ ሰውም ሊኖር ይችላል፡፡ ስለዚህ ሁለተኛው ደረጃ የመመለስ ተግባር ነው፣ ማለትም አንድ ስህተት መፈፀሜን ማመን ብቻ ሳይሆን መጠየፌን የሚገልጽ ስሜታዊ ምልክት ማሳየት ነው፡፡ በተግባሬ ማዘን ይገባኛል፡፡ በተግባሬ እግዚአብሔር የሚሰማውን ሃዘን እኔም ይሰማኛል ማለት ነው፡፡ እነዚህ ሁለቱ ፈቃዳችንን ወደሚመለከተው ወይንም ከኃጢአት በመመለስ በገባነው ቃል ኪዳን መሠረት መፈጸም ያቃተንን ነገር ደስ ብሎን ለመፈጸም ወደምንችልበት ወደ ክርስቶስም በመመለስ ለእርሱ ደስታና ክብር ራሳችንን ወደ ምንሰጥበት ወደ ሦስተኛው እርከን ይመራሉ፡፡ [ዶ/ር ሮበርት ሊስተር]*

ስለ ንስሓ ስናስብ ዘወትር የአንድን ሳንቲም ገፅታ መቶ በመቶ መገልበጥን ማሰብ መልካም ነው፡፡ ልክ እንደዚያው ሁሉ፣ በአንዲት ቅፅበት ከኃጢአት ወደ ጽድቅ ዘወር ማለት እንችላለን፡፡ ከኃጢአት መመለስ የምንጀምረው የእግዚአብሔርን ሕግ ስለመጣሳችን እና ጎረቤቶቻችንንም የነካ ከሆነ እነርሱን ስለመጉዳታችን በእውነት በማዘን ነው፡፡ ወደ ሙላትም የምናደርሰው ስለ በደላችን ስንናዘዝና እግዚአብሔርም ይቅር እንዲለን ስንጠይቅ ነው፡፡ እነዚህን መሳይ የኃጢአት ገፅታዎችን በኤርምያስ ምዕራፍ 31 ቁጥር 19 እና በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 ቁጥር 37 እና 38 ውስጥ እናገኛቸዋለን፡፡ ንስሓ ማለት ይህ ብቻ ሳይሆን ወደ እግዚአብሔር በመመለስ ለወደፊቱ ልንታዘዘው በመወሰን እንዲያነፃንና እንዲያድሰን መጠየቅ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ደግመን ፈፅሞ ኃጢአት አንሠራም ማለት አይደለም፡፡ እውነተኛ ንስሓ ሕግጋቱን በመፈፀም እግዚአብሔርን ደስ የማሰኘትን መሻት ያካትታል ማለት ነው፡፡ ይህንንም በኢዩኤል ምዕራፍ 2 ቁጥር 12 እና 13፤ 2ቆሮንቶስ ምዕራፍ 7 ቁጥር 10 እና 11 በመሳሰሉት ውስጥ እናገኛለን፡፡

*ንስሓ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትልቅ ቃል ነው፡፡ እርሱም ሁለንተናዊ (ሜታኖያ) ነው፡፡ ከኃጢአታችን መመለስ ማለት፣ ሁለንተናዊ ለውጥን በሙላት መረዳትን ያካትታል፡፡ ከኃጢአት መንገዶቻችን ሁሉ እንመለሳለን፡፡ ማለትም ቀድሞ በዚያኛው ጎዳና ስንሄድ ኢየሱስ ሕይወታችንን ነካ፣ አሁን በዚህኛው መንገድ መጓዝ ጀመርን ማለት ነው፡፡ እንለወጣለን፡፡ እርሱ እንድንለወጥ በሚፈልግበት ነገር ሁሉ እንለወጣለን፡፡ እውነቱን ስንናገር፣ እርሱ ሁሉንም ማለት ነው፡፡ ይህ የሁለንተና ልቡናዊ ለውጥ ነው ንስሓ፡፡ በአዕምሮ እውቀት አምነንበታል ያልነውን መለወጥ ብቻ ኣይደለም፡፡ በመሠረቱ "እውቀት" ለሚለው ቃል የገባውን የብሉይ ኪዳን ቃል እወደዋለሁ፡፡ እርሱም "ያዳ" የሚል ሲሆን መለማመድና መገናኘት ማለት ነው፡፡ እንግዲያው በአዕምሯችን የምናውቀው ነገር ብቻ ሳይሆን፣ እጃችንም፣ እግራችንም፣ ስሜታችንም፣ ልባችንም እንዲያው ጠቅላላው እኛነታችን ማለት ነው፡፡ የልቡና ለውጥ*

*ማለት የሁሉ ነገር ለውጥ ነው፡፡ ሁሉን ነገር መለወጥ ስንጀምር፣ መለወጥ እንጀምራለን፡፡ ለምሳሌም ያህል፣ የምናደርገው የምናምንበትን ብቻ ይሆናል፡፡ ባህርያችንን መለወጥ እንጀምራለን፡፡ የባህርይ ለውጥ ከሌለ፣ ለውጥ የለም ማለት ነው፡፡ “የምትሠራው የምታምንበትን ነው የምታምንበትም የምትሠራውን ነው” የሚል የሴሚነሪ ፕሮፌሰር ነበረኝ፡፡ በልቡናዊ ንስሓ የሚከናወን ብዙ ነገር አለ፡፡ [ዶ/ር ማቲው ፍሬድማን]*

የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ ምድር መጥታለች የሚለው የኢየሱስ መልእክት አስደናቂ ዜና ነው፡፡ ሆኖም ግን ከንስሓ አስፈላጊነት ተነጥሎ ሊታይ አይችልም፡፡ በኃጢአታቸው የሚናዘዙና በእምነት ወደ እግዚአብሔር ዘወር የሚሉ ብቻ የመንግሥቱን በረከት የመቋደስ እድል ያገኛሉ፡፡

ከወንጌሉ አዋጅ በተጨማሪ፣ የኢየሱስ የአደባባይ አገልግሎት የመልእክቱን እውነተኝነት የሚያረጋግጡ የኃይል አገልግሎቶችም ተካተውበት ነበር፡፡

## ኃይል

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 10 ቁጥር 38፣ ሐዋርያው ጳውሎስ የኢየሱስን ተዓምራዊ ኃይል በዚህ መንገድ አጠቃልሎታል፡

> እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው፥ እርሱም መልካም እያደረገ ለዲያብሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረና፤ (ሐሥ 10፥38)

ኢየሱስ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል የሚገልጡ በርካታ ተዓምራትን አድርጓል፡፡ በዮሐንስ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 1 እስከ 11 ባለው ክፍል ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ ሲለውጥ በተፈጥሮ ላይ ጌታ መሆኑን ገልጧል፡፡ ማቴዎስ ምዕራፍ 12 ቁጥር 22፤ ማርቆስ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 23 እስከ 26 እና ሉቃስ ምዕራፍ 9 ከቁጥር 38 እስከ 43 ባሉት ክፍሎች ውስጥ በክፉ መናፍስትና በተፅእኖዎቻቸው ላይ ያሳየውን ሥልጣን እንመለከታለን፡፡ ማርቆስ ምዕራፍ 10 ከቁጥር 46 እስከ 52፤ ሉቃስ ምዕራፍ 8 ከቁጥር 43 እስከ 48 እና ዮሐንስ ምዕራፍ 9 በሽተኞችንና የአካል ጉዳተኞችን መፈወሱን እንመለከታለን፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በማቴዎስ ምዕራፍ 9 ከቁጥር 18 እስከ 26፤ ሉቃስ ምዕራፍ 7 ከቁጥር 11 እስከ 15 እና ዮሐንስ ምዕራፍ 11 ከቁጥር 41 እስከ 45 ላይ ኢየሱስ ሙታንን ማስነሳቱም ተጽፏል፡፡ በመሠረቱ፣ ኢየሱስ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ከተነሱት ከሌሎቹ ነቢያት ይልቅ በርካታ ተዓምራትን አድርጓል፡፡ አዲስ ኪዳን ቢያንስ 35 ተዓምራትን መዝግቧል፣ የዮሐንስም ወንጌል ከነዚህም ውጪ

ሌሎች በርካታ ተዓምራትን እንዳደረገ ጠቅሷል፡፡ ይህንንም በዮሐንስ ምዕራፍ 21 ቁጥር 25 ላይ እንዲህ ተጽፎ እናነባለን፡

> ኢየሱስም ያደረገው ብዙ ሌላ ነገር ደግሞ አለ፤ ሁሉ በእያንዳንዱ ቢጻፍ ለተጻፉት መጻሕፍት ዓለም ራሱ ባልበቃቸውም ይመስለኛል። (ዮሐንስ 21፥25)

ኢየሱስ የገለጠው ተዓምራዊ ኃይል ከግምት ውስጥ ልናስገባቸው የሚገቡ ሁለት እንድምታዎች አሉት፡፡ በመጀመሪያ፣ ክርስቶስ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ ሁለተኛ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወደ ምድር የማምጣቱን ወቅታዊ ስኬቱን አረጋግጠዋል፡፡ እስኪ በመጀመሪያ የኢየሱስ ተዓምራት እንዴት ማንነቱን እንዳረጋገጡ እንመልከት፡፡

## የተረጋገጠ ማንነት

የኢየሱስ ተዓምራታዊ የኃይል ሥራዎች ክርስቶሳዊ ማንነቱን፣ምለትም የእርሱን መንግሥት የመጨረሻ ደረጃ ለመግለጥ በእግዚአብሔር የተቀባው መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ እንደ ክርስቶስ፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ባለ ሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ነበር፡፡ ተዓምራቶቹም ኢየሱስ የተናገራቸውን ነገሮች ሁሉ እግዚአብሔር ያጸደቃቸው መሆኑን ያሳያሉ፡፡ ይህንንም በሉቃስ ምዕራፍ 7 ቁጥር 22፣ በዮሐንስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 36 እና በምዕራፍ 10 ከቁጥር 31 እስከ 38 ባሉትና በመሳሰሉት ክፍሎች ውስጥ እንመለከታለን፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ በቅዱሳት መጻሕፍት የተጠቀሱ ሰዎች የኢየሱስን ተዓምራት ከክርስቶስ አገልግሎት መጠነ ሰፊ የተቀባ ቢሮ ጋር ያገናኙታል፡፡ ለምሳሌ፣ በሉቃስ ምዕራፍ 7 ቁጥር 16፤ በዮሐንስ ምዕራፍ 6 ቁጥር 14 እና ምዕራፍ 7 ቁጥር 40 ላይ የተጠቀሱትን የእርሱ የነቢይነት አገልግሎት ፍፃሜዎች አድርገው ተመልክተዋቸዋል፡፡ ኢየሱስ ራሱም በሉቃስ ምዕራፍ 17 ከቁጥር 12 እስከ 19 ባለው ክፍል ውስጥ የእርሱን ተዓምራዊ ኃይል ከካህናት አገልግሎት ጋር አገናኝቶ ገልፆታል፡፡ በማቴዎስ ምዕራፍ 9 ቁጥር 27፣ ምዕራፍ 12 ቁጥር 23፣ ምዕራፍ 15 ቁጥር 22 እና ምዕራፍ 20 ቁጥር 30 ላይ ተዓምራቱ ከንግሥና ቢሮው ጋር ተያይዘው ተጠቅሰዋል፡፡ በዮሐንስ ምዕራፍ 10 ከቁጥር 37 እስከ 38 ላይ ኢየሱስ የተናገረውን አድምጡ፡

> እኔ የአባቴን ሥራ ባላደርግ አትመኑኝ፤
> ባደርገው ግን፥ እኔን ስንኳ ባታምኑ አብ በእኔ እንደ ሆነ እኔም በአብ እንደ ሆንሁ ታውቁና ታስተውሉ ዘንድ ሥራውን እመኑ። (ዮሐ 10፥37-38)

የኢየሱስ ተዓምራት የወንጌሉ መልእክት እውነት መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ እርሱ በእውነት ክርስቶስና የእግዚአብሔርን መንግሥት የመጨረሻ እርከን በምድር እንድትመጣ ያደረገ ክርስቶስ ነው፡፡ በሉቃስ ምዕራፍ 11 ቁጥር 20 እንዲህ ተናግሯል፡

> እኔ ግን በእግዚአብሔር ጣት አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ፥ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ደርሳለች።

የኢየሱስ አስደናቂ ሥራዎች የሰይጣን የጭቆና አገዛዝ ከእግዚአብሔር ሕዝብና ፍጥረት ላይ እንዲያከትም መንግሥተ ሰማያትን በምድር ያመጣ ክርስቶስ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡

የኢየሱስ የኃይል አገልግሎት ክርስቶስ መሆኑን እንዳረጋገጠ ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ እንዴት ስኬቱን እንዳረጋገጡ እንመልከት፡፡

## የተረጋገጠ ስኬት

የኢየሱስ ተዓምራት የይገባኛል ጥያቄ ያነሳባቸውን ነገሮችና ተስፋዎቹን ለመፈፀም አስፈላጊ የሆነው ኃይል ያለው መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ በሰማይ ያለችው የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር እንድትሆን ለማድረግ ሚያስፈልገው ኃይል ሁሉ አለው፡፡ በመሠረቱ፣ አብዛኞቹ ተዓምራዊ በረከቶቹ የዚያን መንግሥት ቅምሻ የሚያቀርቡ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ ሙታንን ሲያስነሳና በሽተኞችን ሲፈውስ በዮሐንስ ራዕይ ምዕራፍ 21 ቁጥር 4 እንደተጠቀሰው ሞትና ሕማም የሌለባትን መንግሥት ከወዲሁ ማሳየቱ ነው፡፡ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችንም ሲመግብ፣ በዘፀአት ምዕራፍ 23 ቁጥር 25 እና 26፤ ኢዩኤል ምዕራፍ 2 ቁጥር 26 እና ሉቃስ ምዕራፍ 12 ከቁጥር 14 እስከ 24 ድረስ ያሉትን ስናነብ በእርሱ ዘላለማዊ መንግሥት የሚኖረውን መትረፍረፍ የሚያመለክት ነው፡፡

ኢየሱስ በተጨማሪም የመንግሥቱን ጠላቶች ለማጥፋት የሚያስፈልገው ኃይል እንዳለውም አሳይቷል፡፡ ለምሳሌ፣ አጋንንትን ሲያስወጣ፣ የማትነዋወጥ መንግሥት መመሥረት የሚችልበት ኃይል እንዳለው ማሳየቱ ነበር፡፡ ይህም መንግሥት በማቴዎስ ምዕራፍ 12 ከቁጥር 22 እስከ 29 ባለው ክፍል እንደምናየው ማንም የማይችለው ነው፡፡

የኢየሱስ ኃይል ያዩትን ሁሉ ትኩረት ይስብ ነበር፡፡ ጠላቶቹ በተንኮል የእርሱን ኃይል እንደ ሰይጣን ማታለል ሊያወድሙት ቢሞክሩም፣ እውነቱ ግን የኢየሱስ ኃይል ከእግዚአብሔር የመጣ መሆኑ ነው፡፡ ያም ኃይል እርሱ ክርስቶስ መሆኑን፣ ሊያመጣ የሚያስበውን፣ ተስፋዎቹን እና ተግዳሮቶቹን ሁሉ መጋፈጥ የሚችልበት አቅም ያለው መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ይህም ለእኛ እንደ ክርስቲያኖች በአድናቆት እንድንሞላና በእጁ እንድንጽናና ያደርገናል፡፡ ይህም ማለት በኢየሱስ ማመናችን በትክክለኛው ስፍራ አርፏል ማለት ነው፡፡

ምንም ያህል ጥርጥር ይኑረን፣ እግዚአብሔር በኢየሱስ የጀመረውን ሥራ ለማጠናቀቅ ምንም ያህል ረጅም ይሁን፣ ምንም ይሁን ምን ኢየሱስ እርሱን ልንታመን የሚገባበትን በርካታ ምክንያቶች ሰጥቶናል፡፡ እርሱ በእውነት የተቀባው ክርስቶስ ነው፡፡ ለእርሱ ታማኝ ከሆንን፣ በእርሱ ዘላለማዊ መንግሥት ውስጥ የከበሬታና የበረከት ስፍራ ስንዳለን እናውቃለን፡፡

የኢየሱስን የወንጌል አዋጅና ኃይል መግለጥ ተመልክተናል፣ አሁን ደግሞ የእርሱ የአደባባይ አገልግሎት ለክርስቶስነት አገልግሎት የተቀባ መሆኑን ስለማረጋገጡ እንመለከታለን፡፡

## ማረጋገጫ

ኢየሱስ እንደ ክርስቶስ የመቀባቱ ነገር በአደባባይ አገልግሎቱ ወቅት በብዙ መንገድ ተረጋግጧል፡፡ ለአሁኑ ማብራሪያችን ግን ሊጠቀሱ በሚገባቸው ሁለት ማረጋገጫዎች ላይ እናተኩራለን፡፡ እነርሱም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለመሆኑ የጴጥሮስ ሐዋርያዊ መግለጫ፤ የኢየሱስ በክብር መለወጥ ናቸው፡፡ በጴጥሮስ ሐዋርያዊ መግለጫ እንጀምር፡፡

## ሐዋርያዊ ማረጋገጫ

በማቴዎስ ምዕራፍ 16 ከቁጥር 15 እስከ 17 ውስጥ ማቴዎስ የመዘገበውን የጴጥሮስን መግለጫ አዳምጡ፡

> እርሱም፡- እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው።
> ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ፡- አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ።
> ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፡- የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ።

ይኸው ተመሳሳይ ሁነት በማርቆስ ምዕራፍ 8 ከቁጥር 27 እስከ 30 እና በሉቃስ ምዕራፍ 9 ከቁጥር 18 እስከ 20 ባሉት ውስጥም ተመዝግቧል፡፡

*የጴጥሮስ መግለጫ በወንጌላት ውስጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፣ ምክንያቱም ስሙም ወንጌላት ተብለው በሚጠቀሱት በማቴዎስ፣ በማርቆስና በሉቃስ ወንጌላት ውስጥ ተመዝግቧልና፡፡ የሦስቱም ወንጌላት የመጀመሪያ ኢጋማሻቸው ትኩረት የሚያደርገው በኢየሱስ መለኮታዊ ሥልጣን ላይ ነው፤ ማለትም፡- በተዓምራቶቹ የተገለጠው ሥልጣኑ፣ ክፉ መናፍስትን በማስወጣቱ፣ በፈውሱ፣ በተፈጥሮ ላይ በገለጠው ተዓምርና በትምህርቶቹ ተረጋግጧል፡፡ እናም፣ ጴጥሮስ አግኝቶታል፡፡ ኢየሱስ በእውነት ክርስቶስ መሆኑን አውቋል፡፡ ከዚያ በኋላም በእውነት በመከራ ውስጥ ወደ ማለፉ የመሲህነት*

*ሃላፊነቱ ተሸጋግሯል፡፡ ይህንን ካልን በኋላ፣ ማቴዎስ፣ ማርቆስና ሉቃስ በጴጥሮስ መግለጫ ላይ በጥቂቱ ለየት ያለ ትኩረቶችን አድርገዋል፡፡ ማርቆስና ሉቃስ፣ እስከዚያች ወቅት ድረስ የተከናወኑት ተዓምራቶች፣ ኢያሱስ በእውነት ክርስቶስ፣ በእርግጥም መሲሁ መሆኑን አረጋግጠውለታል፡፡ ስለዚህም እግዚአብሔር በኢየሱስ አማካይነት በሥራ ላይ ለመሆኑ እውቅና ሰጥቷል እናም በሰብዓዊ ሚዛኑ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ለይቷል የሚሉ ይመስላሉ፡፡ ማቴዎስ ደግሞ፣ ከመግለጫው በቀጥታ ያስከተለው፣ ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፡- "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ፡፡" ማቴዎስ ይህ ነገር በኢየሱስ ሥራ ውስጥ የተገለጠ መለኮታዊ መገለጥ በመሆኑ ላይ ትልቅ አፅንዖት ሰጥቷል፡፡ ሥልጣኑ በተገለጠባቸው ምልክቶች በኩል መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፣ ያወቀው ግን ጴጥሮስ ብቻ ነው ምክንያቱም እግዚአብሔር ገልጦለታልና፡፡ እንዲህ ከሆነ ሰማያዊ መገለጥ የመሆኑ ነገር በጣም ወሳኝ ነው፤ በማቴዎስ ወንጌልም ይኸው ወሳኝነት ተገልጧል፡፡ [ዶ/ር ማርክ ስትራውስ*]

ኢየሱስ ለክርስቶስነት አገልግሎት ስለ መቀባቱ ጴጥሮስ የሰጠው ማረጋገጫ ከእግዚአብሔር በቀጥታ የመጣ መገለጥ ነው፡፡ እንደተመለከትነው፣ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን በተዓምራቶቹ አማካይነት ሰዎች ሊለዩ ይገባል፡፡ ግን ጴጥሮስ እንደ ሐዋርያት ቃል አቀባይ የሰጠው ማረጋገጫ ከዚያ እጅግ ይልቃል፡፡ ከእግዚአብሔር የሆነ ሥልጣን ያለው ትንቢታዊ መገለጥ ነው፡፡ እንዲያውም፣ ኢየሱስ በእውነት ክርስቶስ የመሆኑ እውነታ የማይሻር ማረጋገጫ ነው፡፡

*በወንጌላት ከተጠቀሱት አስገራሚ ነገሮች መካከል አንዱ ኢየሱስ "እኔ ማን እንደሆንኩ ትላላችሁ?" በማለት ላቀረበው ጥያቄ "አንተ የህያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ፡፡ አንተ መሲሁ ነህ፡፡" በማለት ጴጥሮስ ያወጀበት ወቅት ነው፡፡ ጥርት ያለ መግለጫ የተሰጠበት ወቅት ነው፡፡ የሚያስገርመው ነገር ምንድን ነው? አስገራሚነቱ፣ ኢየሱስ ራሱ እንደተናገረው፣ ጴጥሮስ በማንነቱ ሊረዳው የማይችለውን ነገር እግዚአብሔር በቀጥታ ለጴጥሮስ የገለጠበት የመገለጥ ወቅት ስለነበር ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለ500 ዓመታት ያህል ይህ መሲህ ይመጣል ተብሎ በናፍቆት ሲጠበቅ የነበረ መሆኑ ሌላው ምክንያት ነው፡፡ እንግዲህ ጴጥሮስ በፊት ለፊቱ የቆመውን ሰው፣ "አንተ መሲሁ ነህ" ብሎ ሲያውጅ፣ በዚያ ብትኖሩ በትልቅ አግራሞትና ጥበቃ ትሞላላችሁ ደግሞም ትበረታላችሁ፣ ያም ወቅት በዚህ ሁኔታ በድንገት ተከሰተ፡፡ [ዶ/ር ፒተር ዎከር]*

የጴጥሮስ ሐዋርያዊ መግለጫ ኢየሱስ ለክርስቶስነት አገልግሎት ያረጋገጠ መሆኑን ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ የኢየሱስን በክብር መለወጥ እንመልከት፡፡

## መለወጥ/ የመገለጥ ተራራ

"መለወጥ (Transfiguration)" የሚለውን ቃል የነገረ-መለኮቱ ምሁራን ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ በክብር የተገለጠበትን ወቅት ለማመልከት የሰጡት ቃል ነው፡፡ ወቅቱም ገጽታው በቅፅበት የተለወጠ መሆኑ፣ መለኮታዊ ክብሩን በከፊል ያሳየ የመሆኑ እውነት የተገለጠበት ነው፡፡ ይህ ወቅት በማቴዎስ ምዕራፍ 17 ከቁጥር 1 እስከ 8፤ በማርቆስ ምዕራፍ 9 ከቁጥር 2 እስከ 8 እና በሉቃስ ምዕራፍ 9 ከቁጥር 28 እስከ 36 ባሉት ክፍሎች ተመዝግቧል፡፡ በ2ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 16 እስከ 18 ባለውም ክፍል ለማገናዘቢያ ተጠቅሷል፡፡

ጠቅለል አድርገን ብንመለከተው፣ ኢየሱስ ጴጥሮስን፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን ይዞ ለጸሎት ወደ ተራራ ወጣ፡፡ በዚያም ሳሉ፣ የኢየሱስ ፊት ተለወጠ፡፡ ፊቱ በክብር አበራ፣ ልብሶቹም እንደበረዶ ነጭ ሆኑ፡፡ የኢየሱስ መልክ ሲለወጥ፣ ሙሴና ኤልያስ ከእርሱ ጋር ታዩ፣ የአግዚአብሔርም ድምፅ ከሰማያት የእርሱ ልጅ መሆኑን በማረጋገጥ ተሰማ፡፡ ጴጥሮስም ለኢየሱስ፣ ለሙሴና ለኤልያስ መጠለያ እንዲሠሩ ሃሳብ ሲያቀርብ፣ እግዚአብሔር ግን ነጥሎ ኢየሱስ ትልቅ ክብር እና መታዘዝ የሚገባው መሆኑን ገለጠ፡፡ ይህ ነገር ወሳኝነት አለው ምክንያቱም ሙሴ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሕግ ሰጪና ነፃ አውጪ ነበር፣ ኤልያስ ደግሞ እስራኤል ከክህደቷ እንድትመለስ ጥሪ ያቀረበ የታመነ ነቢይ ነበር፡፡ ፍቺውም ኢየሱስ የህግና የነቢያት ቀጣይ አገልግሎት ክፍል ሆኖ ቆመ፣ በቀደሙት የእስራኤል መሪዎችም ሲጠበቅ የነበረውንም መሻት ያሟላ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ በተጨማሪም ከሁሉ ይልቅ የተቀባው፣ የእግዚአብሔርንም መንግሥት ወደ ምድር የሚያመጣው የመጨረሻው የዳዊት ዘር ነውም ማለት ነው፡፡

> *እንግዲህ ይህ የመገለጥ ተራራ ኢየሱስ ከደቀመዛሙርቱ ከሦስቱ ጋር ብቻ የወጣበት፣ አስገራሚ ትዕይንት የታየበት ነው፡፡ እነርሱም የክርስቶስን ክብር አዩ፡፡ እናም እኛ፣ በመጀመሪያ የክርስቶስን ሁለት የማንነት ብልጭታዎች እናገኛለን፣ ይህ ሰው፣ ስለ እርሱ ዘወትር እውነት ሆኖ በሚኖር የማንነቱ ክብር ተገለጠ፣ አንድ የገና መዝሙር እንደጠቀሰውም፣ በሥጋ ውስጥ ቢሰወርም እኛ ግን እግዚአብሔርን አየን፡፡ በዚህም እኛ ይህንን የከበረ ኀላፄውን አንጸባራቂ መገለጥ አየን፣ ደቀመዛሙርቱ ከተራራው ሲወርዱ እንኳን ፊታቸው ያበራ የነበረው ለዚህ ነው ፡፡ ከሁሉ ይልቅ ግን ከቃል ኪዳኑ ሙላት አንፃር ስንመለከተው፣ እጅግ አስደናቂ ነው፣ ምክንያቱም በተለወጠ ወቅት ያገኛቸው እነማንን ነበር? ስንል፣ ሙሴንና ኤልያስን ነበር፡፡ በዚህም ኢየሱስ የህግ፣ ደግሞም የነቢያት አገልግሎት ፍፃሜ ሆኖ ተገለጠ፣ መሲሃዊ ማንነቱንም በዚህ መንገድ ወደ ሙላት አመጣ፡፡ አሮጌውም ኪዳን መሲሁ ኢየሱስ ከህግ ሰጪው ከሙሴ ጋር ሲገናኝ*

*ተፈፀመ፡፡ የነቢያት አገልግሎትም ከኤልያስ ጋር ሲገናኝ ተፈፀመ፣ ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ሲገናኝ በዚያ አስደናቂ የመገለጥ ተራራ ላይ መሲሃዊ ማንነቱን ገለጠ፡፡ [ዶ/ር ኬ. ኤሪክ ቶኔስ]*

አስካሁን ድረስ ኢየሱስ በውልደቱና በዝግጅቱ ወቅት ለክርስቶሳዊ አገልግሎቱ እንዴት እንደተዘጋጀና የአደባባይ አገልግሎቱን ተመልክተናል፣ አሁን ደግሞ ወደ ህማማቱና ወደ ሞቱ ዘወር እንላለን፡፡

# 5. ህማማትና ሞት

"ህማማት" የሚለውን ቃል የምንጠቀመው ኢየሱስ የታገሰውን መከራ በተለይም በተሰቀለበት ሳምንት ያሳለፈውን ለማመልከት ነው፡፡ ከኢየሱስ ታሪክ ውስጥ የከፋው የጨለማ ወቅት ይህ ወቅት ነበር፣ ምክንያቱም በዚህ ሳምንት ኢየሱስ በሰው ሁሉ ተንቋል፣ ተከታዮቹ ከድተውታል፣ ከሳሾቹም ለሞት አሳልፈው ሰጥተውታል፡፡ ከዚህ ሁሉ የከፋው ደግሞ፣ በሰማይ ያለው አባቱ በእኛ ምትክ መለኮታዊውን ቁጣና ፍርድ በላዩ አዝንቦበታል፡፡ ግን በዚህም የጨለማ ታሪክም ውስጥ ቢሆን የተስፋና የብርሃን ወጋገን ታይቷል፡፡ የኢየሱስ ህማማትና ሞት ስላሴ እኛን ለማዳን ምን ያህል ርቀት እንደተጓዘ ያሳየናል፡፡ የእኛን ምስጋና፣ መታዘዝና ውዳሴ ሊቀበል የሚገባውን መለኮታዊ ፍቅርና መስዋዕትነት ያመለክተናል፡፡

በዚህ ትምህርት፣ ወደ ኢየሩሳሌም የገባበትን ጊዜ መነሻው በማድረግ ከስቅለቱ በኋላ በመቃብር ውስጥ መገኘቱን መደምደሚያው ያደረገውን የኢየሱስን ህማማትና ሞት እናብራራለን፡፡ ምንም እንኳን ይህ የኢየሱስ የሕይወት ክፍል አንድ ሳምንት ብቻ የቆየ ቢሆንም፣ እጅግ ወሳኝ የሆኑ ክስተቶችን በውስጡ ይዟል፡፡ አንድ ጊዜ እንደገና፣ ስለ ወቅቱ አጭር መግለጫ በመስጠት እንጀምር፡፡

በ30 ዓ.ም. ገደማ ኢየሱስ የፋሲካን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ፡፡ በአህያይቱ ውርንጭላ ላይ ተቀምጦ ወደ ከተማዪቱ ሲቃረብ፣ በርካታ ሰዎች እንደ እስራኤል ንጉሥ ከፍ ባለ ድምፅ ተቀበሉት፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ወደ ከተማዪቱ የገባበት ሁኔታ በተለምዶ የድል አገባብ ተብሎ ይታወቃል፡፡ ይህንንም በማቴዎስ ምዕራፍ 21 ከቁጥር 1 እስከ 11፤ በማርቆስ ምዕራፍ 11 ከቁጥር 1 እስከ 11፣ በሉቃስ ምዕራፍ 19 ከቁጥር 28 እስከ 44 እና በዮሐንስ ምዕራፍ 12 ከቁጥር 12 እስከ 19 ባሉት ክፍሎች ውስጥ እናባለን፡፡

አንድ ጊዜም በኢየሩሳሌም፣ ኢየሱስ በመቅደስ ውስጥ በነበሩ ነጋዴዎች ላይ ተቆጥቶ ነበር፡፡ ከዚያም በትንቢታዊ እርግማንና በንጉሣዊ ፍርድ፣ ገበታቸውን ገለበጠ ከመቅደስም አባረራቸው፡፡ ይህንን መቅደሱን የማንፃት ሥራ ወንጌላት በማቴዎስ ምዕራፍ 21 ከቁጥር 12

እስከ 17፤ ማርቆስ ምዕራፍ 11 ከቁጥር 15 እስከ 18 እና በሉቃስ ምዕራፍ 19 ከቁጥር 45 እስከ 48 መዝግበውታል፡፡ ቀጥሎም ባሉት ቀናት ውስጥ፣ ኢየሱስ ከሃይማኖት መሪዎች ጋር ሲከራከር እና ሊያዳምጡት ወደ እርሱ የመጡትን ሁሉ ሲያስተምር ቆየ፡፡ ከዚያም፣ ከአይሁድ ፋሲካ ቀደም ብሎ ባለው ምሽት፣ በተለምዶ የመጨረሻው እራት (የጌታ እራት) ተብሎ የሚጠቀሰውን ገበታ ኢየሱስ ከደቀመዛሙርቱ ጋር በላ፡፡ በዚህ ገበታ ወቅት፣ ጌታ እንደ ተስፋ ቃሉ ተመልሶ እስከሚመጣበት ቀን ድረስ ይህንን የጌታ እራት ለእርሱ መታሰቢያነትና ለኅብረት በቀጣይነት እንዲደረግ አዘዘ፡፡ ይህ ሁነት በማቴዎስ ምዕራፍ 26 ከቁጥር 17 እስከ 30፤ በማርቆስ ምዕራፍ 14 ከቁጥር 12 እስከ 26 እና በሉቃስ ምዕራፍ 22 ከቁጥር 7 እስከ 23 ላይ ተመዝግቧል፡፡ በዚያው ሌሊት፣ በትምህርት፣ በተለምዶም የመሰነባበቻ ንግግር ተብሎ በሚታወቀው በዮሐንስ 13 እስከ 16 በተመዘገበው ንግግር እና በዮሐንስ 17 በሚገኘው የታላቅ ሊቀ ካህን ፀሎቱ በኩል ያስተምራቸው ነበር፡፡ በዚያውም ምሽት፣ በሉቃስ ምዕራፍ 22 ቁጥር 3 እና 4 እና በዮሐንስ ምዕራፍ 13 ከቁጥር 27 እስከ 30 እንደተፃፈው፣ ደቀመዝሙሩ ይሁዳ ከአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች ጋር በመከረው መሠረት ኢየሱስን አሳልፎ ሊሰጥ ወጣ፡፡ ከዚያ በኋላ፣ ኢየሱስና የቀሩት ደቀመዛሙርት ጌተሰማኒ ወደሚሰኝ የአትክልት ስፍራ ሄዱ፡፡ ኢየሱስም እየጸለየ ሳለ፣ ይሁዳ የአይሁድን የሃይማኖት መሪዎችና ወታደሮች መርቶ ወደ አትክልቱ ስፍራ አመጣቸው ኢየሱስንም ያዙት፡፡ በአይሁድ ሊቀ ካህን በቀያፋና በአይሁድ ሸንጎ ፊት ተከሰሰ፣ በሮማው ገዥ በጲላጦስ እና በአይሁድ ንጉሥ ሄሮድስ አንቲጳስ ፊትም ለፍርድ ቆመ፡፡ ወቅቱ በፈጠረባቸውም ጫና፣ የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ትተውት ሸሹ፣ ጴጥሮስም ሦስት ጊዜ ካደው፡፡ ኢየሱስ ራሱም፣ ተገረፈ፣ ተሳለቁበት ለሞትም አልፎ ተሰጠ፡፡ እነዚህ ክስተቶች በማቴዎስ ምዕራፍ 26 ከቁጥር 31 እስከ ምዕራፍ 27 ቁጥር 31፤ በማርቆስ ምዕራፍ 14 ከቁጥር 32 እስከ ምዕራፍ 15 ቁጥር 20፤ በሉቃስ ምዕራፍ 22 ቁጥር 39 እስከ ምዕራፍ 23 ቁጥር 25 እና ዮሐንስ ምዕራፍ 18 ቁጥር 1 እስከ ምዕራፍ 19 ቁጥር 16 ላይ ተመዝግበዋል፡፡

ኢየሱስ በተያዘበት ቀን ማግሥት እኩለ ቀን ላይ ተሰቀለ፡፡ በመስቀልም ላይ በሚስማር ተቸንክሮ ነፍሱ እስክትወጣ ድረስ በአደባባይ ተሰቀለ፡፡ በዚህ ሁሉ ጣዕርና መከራ ውስጥ ሆኖም ሳለ፣ ንስሓ ለገባው ዘራፊ የምህረትን ተስፋ ሰጠ፣ እናቱን አደራ ሰጠ ለሞት አሳልፈው የሰጡትንም ይቅር እንዲላቸው እግዚአብሔርን ጠየቀ፡፡ ወደ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ወደ እግዚአብሔር ጮኾ ነፍሱን ሰጠ፡፡ እነዚህም ሁነቶች በማቴዎስ ምዕራፍ 27 ከቁጥር 32 እስከ 54፤ ማርቆስ ምዕራፍ 15 ከቁጥር 21 እስከ 39፤ ሉቃስ ምዕራፍ 23 ከቁጥር 26 እስከ 47 እና ዮሐንስ ምዕራፍ 19 ከቁጥር 16 እስከ 30 ላይ ተመዝግበዋል፡፡

በዚያንም ወቅት፣ የመሬት መንቀጥቀጥ ተከሰተ የቤተመቅደሱም መጋረጃ ከላይ ወደታች ተቀደደ፡፡ የሮሜው ወታደር በጦር ወግቶት መሞቱን ካረጋገጠ በኋላ፣ የኢየሱስ ሰውነት

ከመስቀል ላይ ተወሰደ፡፡ ሰንበትም ሊገባ ስለነበረ፣ ከተከታዮቹ ጥቂቶቹ ሥጋውን ለቀብር በፍጥነት አዘጋጁና በውስተ መቃብር ውስጥ አስቀመጡት፡፡ የዚህ ዘግናኝ ከሰዓት በኋላ ክስተት በማቴዎስ ምዕራፍ 27 ከቁጥር 51 እስከ 61፤ ማርቆስ 15 ከቁጥር 38 እስከ 47፤ ሉቃስ ምዕራፍ 23 ከቁጥር 44 እስከ 56 እና በዮሐንስ ምዕራፍ 19 ከቁጥር 34 እስከ 42 ላይ ተመዝግቧል፡፡

የኢየሱስን ህማማትና ሞት በወቅቱ ተከሰተው በነበሩ ሦስት ክስተተቶች ላይ በማትኮር ማለትም፡ የኢየሱስን ወደ ኢየሩሳሌም በድል መግባት፣ በጌታ ላይ ላይ የነበረበትን ሁኔታ፣ እና ስቅለቱን እንመለከታለን፡፡ በመጀመሪያ በድል መግባቱን እንመለከታለን፡፡

## በድል መግባት/ሆሳዕና

ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም የገባው በነቢዩ በዘካርያስ ምዕራፍ 9 የተነገረው ይፈፀም ዘንድ በአህያ ውርንጭላ ላይ ተቀምጦ ነው፡፡ አህያይቱ በሰላም ወቅት ነገሥታት በተራሮች ላይ ምንም ስጋት የሌለባቸው መሆኑን ለማመልከት የሚጋልቡባት ምልክት ናት፡፡ ይህ ተምሳሊታዊ ድርጊት በዓላማ የተደረገ ነው፡፡ የኢየሱስን የተገባው የእስራኤል ንጉሥነት ለማመልከት፤ ለመንግሥቱ ወንጌል ታማኞች ለሆኑት ማረጋገጫ ለመስጠት እና ተቀራኒዎቹን ለመገሰፅ ነበር፡፡

ኢየሱስ ወደ ከተማይቱ ሲቃረብም፣ ሰዎች አወቁት እንኳን ደህና መጣህም ብለው ተቀበሉት፡፡ ክብርንም ይሰጡት ዘንድ፣ የዘንባባ ዝንጣፊ እና መደረቢያዎቻቸውንም እንኳን ሳይቀር በመሬት ላይ በማንጠፍ እና ከፍ ባለ ድምጽ አመሰገኑት፡፡ በማርቆስ ምዕራፍ 11 ቁጥር 9 እና 10 እንደምናነብበው፡

> የሚቀድሙትም የሚከተሉትም። ሆሣዕና፤ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፤
> በጌታ ስም የምትመጣ የአባታችን የዳዊት መንግሥት የተባረከች ናት፤
> ሆሣዕና በአርያም እያሉ ይጮኹ ነበር።

ነገር ግን ሁሉም ኢየሱስን በመልካም አልተቀበሉትም፡፡ በእርሱ መምጣት ከሁሉ ይልቅ በጣም ደስ ሊሰኙ ይገባቸው በነበሩ የአይሁድ መሪዎች፣ ቀሳውስት በሕግ መምህራን ተጠልቶ ተቃውሞ ገጥሞትም ነበር፡፡ በእግዚአብሔር የተቀባውን ባለመቀበላቸው፣ አገልግሎታቸው ከእግዚአብሔርና ከእርሱ ሥራ ጋር ተቃራኒ መሆኑን አረጋገጡ፡፡ ኢየሱስ

ወደ ከተማይቱ ሲገባ የተናገረውን በሉቃስ ምዕራፍ 19 ከቁጥር 41 እስከ 44 ያለውን አድምጡ፡

> ሲቀርብም ከተማይቱን አይቶ አለቀሰላት፥
> እንዲህ እያለ። ለሰላምሽ የሚሆነውን በዚህ ቀን አንቺስ ስንኳ ብታውቂ፤
> አሁን ግን ከዓይንሽ ተሰውሮአል።
> ወራት ይመጣብሻልና፥ ጠላቶችሽም ቅጥር ይቀጥሩብሻል ይከቡሻልም
> በየበኩሉም ያስጨንቁሻል፤
> አንቺንም በአንቺም ውስጥ የሚኖሩትን ልጆችሽን ወደ ታች ይጥላሉ፥
> በአንቺ ውስጥም ድንጋይ በድንጋይ ላይ አይተዉም፥ የመጐብኘትሽን
> ዘመን አላወቅሽምና።

በኢየሱስ የመጨረሻ ሳምንት መጀመሪያ ላይ የሃይማኖት መሪዎቹ ኢየሱስን በሕዝቡ ፊት ዋጋ ለማሳጣት በማለም በተለያዩ ጥያቄዎች በማጣደፍ ተቃውሞውን ቀጠሉ፡፡ የሮሜ ባለሥልጣናትም ይቃወሙት ዘንድ ለማነሳሳት ሞከሩ፣ የኢየሱስንም ክርስቶሳዊ ሥልጣን ደጋግመው ይሚገቱ ነበር፡፡

> *በኢየሱስ የድል መግባትና ከዚያም ተከትለው በነበሩት ቀናት የሃይማኖቱ ባለሥልጣናት ኢየሱስን ሲቃወሙት ሕዝቡ ግን ያመሰግኑት ነበር፡፡ ሰዎች ከእርሱ አንፃር እንዲህ የተለያየ አፀፋዊ ምላሽ ይሰጡ የነበሩት ለምንድን ነው? በተለያየ ደረጃ ልንረዳው እንችላለን፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ፣ በጣም የሳቱት በሥልጣን ላይ የነበሩት ናቸው፡፡ በዚህም የምንመለከተው ኃይልንና ሥልጣንን አስመልክቶ ያለውን ጥቅል ነገር ነው፡፡ የሰው ተፈጥሮ እንደዚያ ነው፣ እናም የአይሁድ ባለሥልጣናትም ከተቀረው የሰው ዘር የተለዩ አልነበሩም፡፡ በሥልጣን ላይ ያሉ ሰዎች ሥልጣናቸውን መልቀቅ አይፈልጉም፣ኢየሱስ ደግሞ ሥልጣናቸውን የሚፈታተን ሆኖ መጣ፡፡ የእግዚአብሔርንም መንግሥት እጅግ አጥብበው፣ በብሔርተኝነት መንገድ ብቻ፣ በኃሰኝነት መንገድ ብቻ፣ በነገድ አስተሳሰብ ብቻ ተመለከቱት ስለዚህም ከሁሉ በከፋ መንገድ ሳቱት፡፡ በሉቃስም ወንጌል ልክ ለማርያም እንደተነገራት ዓይነት፣ ይህ ሕፃን በእስራኤል ውስጥ ለብዙዎች መውደቅና መነሳት ምክንያት እንደሚሆን እና የማሰናከያ ዐለት እንደሚሆን እንረዳለን፡፡ የዮሐንስ ወንጌል የሚጀምረው ይህ ወደ ዓለም የመጣው ብርሃን ጨለማ የማይቀበለው እንደሆነ በመናገር ሲሆን፣ አንዳንድ ትርጉሞችም "አላወቀውም" ይሉታል እኔ እንደማስበው ግን "ሊበረታበት አልቻለም" ብለን ልንረዳው ይገባል፡፡ ኢየሱስ የመጣው የዓለም ብርሃን ሆኖ ነው፣ ጨለማውም ሊረዳው የማይችልበት ብዙ ነገር አለው፡፡ የሃይማኖት መሪዎቹም የገለጡት ይህንን ነው፡፡ ይህን ስንል ግን ብዙም ሳይቆይ በተለምዶ የህማማት ሳምንት ብለን በምንጠራው ሳምንት፣ የኢየሱስ ተከታዮች የነበሩት ሕዝቦች*

*እንኳን ሳይቀሩ፣ በርናባስን ፍታው ብለው መጮኻቸውን ልናስታውስ ይገባል፡፡ ኢየሱስ የመጣው ሰዎች እግዚአብሔር እንዲያደርግላቸው የሚፈልጉትን ነገር ሊያሟላ አልነበረም፡፡ የመጣው ግን፣ እግዚአብሔር እንዲሆን የፈለገውን ለመፈፀም ነው፡፡ ያም ማለት፣ ለግል ነፃነታችን ፈተና ሊሆን እና ለራስ ገዝነታችን ፈተና ሊሆን ነው፡፡ ለራሳችን መሞት አንፈልግም፣ እናም ኢየሱስ የሰዎችን ፈቃድ የሚገለባብጥን ፈተና አመጣ፣ ለዚህም ነው ከሰብዓዊ ሚዛን አንፃር ተቃውሞ የገጠመው፡፡ [ቄስ ሚካኤል ግሉዶ]*

በድል መግባቱን ከተመለከትን፣ የኢየሱስ የህማማትና የሞት ሳምንት ሁለተኛ ዋና ክስተት የሆነውን የጌታ እራት ድንጋጌ እንመልከት፡፡

# የጌታ እራት

ቀደም ብለን እንደተመለከትነው፣ የኢየሱስ ህማማትና ሞት የተከሰተው በፋሲካ ሳምንት ነው፡፡ ስለዚህም፣ በዚህ ሳምንት ኢየሱስ ያደረገው ከደቀመዛሙርቱ ጋር የፋሲካን እራት መብላት ነው፡፡ ይህንንም ያደረገው ከመያዙ እና ከመሰቀሉ ቀደም ብሎ ሲሆን ክስተቱም በተለምዶ የመጨረሻው እራት በመባል ይታወቃል፡፡ በዚህ የመጨረሻ እራት ወቅት፣ ክርስቲያኖች ዘወትር ሊያስታውሱ የሚገባቸው በጣም ልዩ ነገር ኢየሱስ ሠርቷል፡፡ የጌታ እራት የክርስቲያኖች ሥርዓት እንዲሆን ደንግጓል፡፡

እንደተናገርነው፣ የጌታ እራት የፋሲካ መብል ነው፡፡ እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብጽ ባርነት ነፃ ያወጣበት እውነት መታሰቢያ ነው፡፡ በመብሉ መጨረሻ ላይ ግን፣ የፋሲካን ተምሳሊትነት እንደ ክርስቶስ ለሚያከናውነው *ሥራው* ትኩረት መሳቢያ ለማድረግ ተጠቀመበት፡፡ በተለይም ለእራቱ ሁለት ነገሮችን መረጠ እነርሱም ያልቦካ ዳቦ እና ወይን ናቸው፡፡ ለሁለቱም አዲስ ፍቺን ሰጣቸው፡፡ እንደ ሉቃስ ምዕራፍ 22 ከቁጥር 17 እስከ 20፣ ኢየሱስ ዳቦውን ለኃጢአት መስዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር ከሚያቀርበው ከሥጋው ጋር፣ ወይኑን ደግሞ ለተመሳሳይ መስዋዕት ከፈሰሰው ከደሙ ጋር፣ አገናኝቷቸዋል፡፡ በተጨማሪም፣ በማቴዎስ ምዕራፍ 26 ቁጥር 29፣ በማርቆስ ምዕራፍ 14 ቁጥር 25 እና በሉቃስ 22 ቁጥር 19 የሰጣቸውን ምክሮችና ትምህርቶች ስናዋህዳቸው፣ ኢየሱስ እነዚህን ውቅረ ነገሮች እርሱ ተመልሶ እስከሚመጣ ድረስ የዘላለም መታሰቢያ እንዲያደርጉዋቸው ደቀመዛሙርቱን እንዳስተማራቸው እንረዳለን፡፡

*በክርስቲያናዊ ትውፊት ውስጥ የጌታ እራት እንደ ክርስቶስ ገሃድ ቃላት ይገለጣሉ ምክንያቱም በመስቀል ላይ የሚከናወነውን ነገር ይገልጣሉና፡፡ የተቆረሰው ዳቦ፣ በመስቀል የተቸነከረውን የክርስቶስን አካል፣ የተቀዳው ወይን፣ ስለ እኛ የፈሰሰውን ደሙን የሚያመለክት ሲሆን፣ በዚህም ነጥብ ላይ ተምሳሊትነቱ እርሱ ስለ እኛ መሞቱን፣*

*ከኀብስቱ በመብላትና ከጽዋው በመጠጣት የበረከቱ ተካፋይ መሆን የምንችልበትን አቅም ያስገኝልናል፡፡ ስለዚህም ስንበላና ስንጠጣ፣ ክርስቶስ ለእኛ ያደረገውን ነገር ከመካፈላችን ባሻገር ታላቅ የሆነ መንፈሳዊ መበረታታትን እናገኛለን፡፡ [ዶ/ር ስምዖን ቫይበርት]*

በጌታ ራት ፍቺ ውስጥ ልንጠቅሳቸው የሚገቡ ሁለት ገጽታዎች አሉ፣ በክርስቶስ ቤዛነት እንጀምራለን፡፡

## ስርየት

የጌታ እራት መሠረታዊ ተምሳሊትነት ለመረዳት በጣም ቀላል ነው፡፡ ዳቦው የክርስቶስን አካል ሲወክል፣ ወይኑ ደግሞ ደሙን ይወክላል፡፡ ግን እነዚህ ለምን ወሳኝ ሆኑ? ምክንያቱም በሉቃስ ምዕራፍ 22 ቁጥር 19 እንደተጻፈው *ሥጋው* ስለእኛ ተቆረሰ፣ ደሙ ደግሞ በማቴዎስ ምዕራፍ 26 ቁጥር 28 *መሠረት* ለብዙዎች የኃጢአትን ይቅርታ ያስገኝ ዘንድ ፈሰሰ፡፡ በሌላ አባባል፣ የእርሱ *ሥጋ*ና ደም እጅግ ወሳኝ ናቸው ምክንያቱም እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ለማስተሰረይ በመስቀል ላይ ያደረገልንን ያሳያሉና፡፡ ይህንን ነጥብ ስለ ስቅለት ስንነጋገር የበለጠ እንመለከተዋለን፡፡

## አዲስ ኪዳን

ስለ ጌታ እራት የምናነሳው ሁለተኛው ፍቺ የአዲስ ኪዳን ብስራት መሆኑን ነው፡፡ በሉቃስ ምዕራፍ 22 ቁጥር 20 ላይ ኢየሱስ የተናገረውን አድምጡ፡

> እንዲሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን አንሥቶ እንዲህ አለ፦ ይህ ጽዋ ስለ እናንተ በሚፈሰው በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው። (ሉቃስ 22፥20)

በዚህ ስፍራ ኢየሱስ ያጣቀሰው ነቢዩ ኤርምያስ በትንቢቱ ምዕራፍ 31 ከቁጥር 31 እስከ 34 አስቀድሞ የተናገረውን የኪዳን መታደስ ነው፡፡

አዲሱ ኪዳን እግዚአብሔር አስቀድሞ በአዳም፣ በኖህ፣ በአብርሃም፣ በሙሴና በዳዊት ዘመን የሰጠው የኪዳን ተስፋ ኀዳሴና ዋስትናን የያዘ ነው፡፡ እነዚህ ቀደምት የእግዚአብሔር ኪዳን መስተዳድሮች እግዚአብሔር ለህዝቡ ያለውን ደግነት፣ ከእነርሱም የሚጠብቀውን ፍፁም መታዘዝ፣ ለሚታዘዙ ያለውን የበረከት ተስፋ እና በማይታዘዙት ላይ የሚመጣውን እርግማን የሚገልፁ ናቸው፡፡ ኢየሱስ ደግሞ እንደ ክርስቶስነቱ፣ እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር ለገባው ኪዳን የመጨረሻው እርከን አስተዳዳሪ ነው፡፡ ይህም እርከን በፈሰሰው ደሙ

“የጸደቀውን” ወይም “የታተመውን” ኪዳን የሚያመለክት ነው፡፡ በዕብራውያን ምዕራፍ 9 ቁጥር 15 ተጽፎ እንደምናነብበው፡

> ስለዚህም የፊተኛው ኪዳን ሲጸና ሕግን የተላለፉትን የሚቤዥ ሞት ስለ ሆነ፥ የተጠሩት የዘላለምን ርስት የተስፋ ቃል እንዲቀበሉ እርሱ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው። (ዕብ 9፥15)

የኢየሱስን በድል መግባትና የጌታ እራት አስተዳደሩን ተመልክተናል፣ አሁን ደግሞ ስቅለቱን እንመለከታለን፡፡

# ስቅለት

ስቅላት በጥንታዊው የሮሜ አገዛዝ ውስጥ አገልግሎት ላይ የሚውል የሞት ቅጣት አፈጻጸም ነው፡፡ ይህ ቅጣት የሚበየንባቸው ሰዎች በመስቀል ላይ ይታሰራሉ፣ ወይንም በሚስማር ይቸነከራሉ፣ እንደ ኢየሱስ አይነቱ ደግሞ፣ በመታፈን ነፍሳቸው እስኪወጣ ድረስ በመስቀሉ ላይ ተንጠልጥለው ይቆያሉ፡፡ በመሠረቱ የኢየሱስ ስቅላት ለየት ይላል፣ ምክንያቱ የኃጢአት ስርየት ሆኖ ስለሚያገለግል ነው፡፡ በዕብራውያን ምዕራፍ 9 ከቁጥር 11 እስከ 28 እንደምናነብበው፣ እንደ ክርስቶስነቱ፣ በህዝቡ ፋንታ የመሞት ሃላፊነት ነበረበት፡፡

ከስቅላት ጋር የተያያዙና አሁን ጠቅሰን የማንጨርሳቸው በርካታ አስተምህሮዎች ስላሉ፣ በሁለቱ ላይ ብቻ እንገደባለን፡ የእኛ ኃጢአት በክርስቶስ ላይ ስለመቆጠሩ፤ መለኮት በኃጢአት ላይ በመበየኑ ምክንያት ስለመሞቱ እንመለከታለን፡፡ አስቀድመን ስለ መቆጠር ሃሳብ እንመለከታለን፡፡

## መቆጠር/ልውውጥ

ልውውጥ ማለት በቀላሉ ሃላፊነት መውሰድ ወይም ምትክነት ማለት ነው፡፡ የእኛ ኃጢአት በመስቀል ላይ በኢየሱስ ላይ ስለ መቆጠሩ ስንናገር ግን ፣ እግዚአብሔር የኃጢአተኞችን ኩነኔ በኢየሱስ ላይ ማኖሩን ማመልከታችን ነው፡፡ ስለዚህ፣ ኃጢአታችን በኢየሱስ ላይ ተቆጠረ ስንል፣ እግዚአብሔር ስለ እኛ ኃጢአት ተጠያቂ አደረገው ማለት ነው፡፡ ኢየሱስ ፈፅሞ ኃጢአት አልሠራም፣ ሰውነቱም በበደል አልረከሰም፡፡ ከህግ አኳያ ግን፣ እግዚአብሔር በእርሱ ላይ የተቆጠሩትን ኃጢአቶች ሁሉ እንደፈፀመ ቆጠረበት ማለት ነው፡፡

በብሉይ ኪዳን ይቀርቡ እንደነበሩት የኃጢአት መስዋዕቶች ሁሉ፣ ኢየሱስም በህዝቡ ምትክ ሆኖ በመስቀል ላይ ራሱን ሰጠ፡፡ የዕብራውያን መጽሐፍ ስለዚህ ነገር በምዕራፍ 9 እና 10

በዝርዝር ይናገራል፡፡ የእኛ ምትክ የመሆኑ የክርስቶስ ድርሻ መጽሐፍ ቅዱስ የእኛ ምትክ መሆኑን ደጋግሞ በሚያመለክተው እውነት ውስጥ ተንፀባርቋል፡፡ ይህም በሮሜ ምዕራፍ 3 ቁጥር 25፤ በኤፌሶን ምዕራፍ 5 ቁጥር 2 እና በ1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 2 ተጠቅሷል፡፡ እርሱ እንደ ማቴዎስ ምዕራፍ 20 ቁጥር 28፣ 1ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 6 እና ዕብራውያን ምዕራፍ 9 ቁጥር 15 በመሳሰሉት ስፍራዎች  የእኛ ቤዛ ተብሎ የተጠራው ለዚህ ነው፡፡

የእኛ ኃጢአት በእኛ ላይ ከመቆጠሩ አስቀድሞ ኢየሱስ እንከን የለሽና ፍፁም ነበር፡፡ ምንም እንኳን ነገሩ እንግዳ ቢመስልም፣ የእኛ ኃጢአት አንድ ጊዜ በእርሱ ላይ ከተቆጠረ በኋላ፣ በእርሱ ላይ በተቆጠረው ኃጢአት ሁሉ እግዚአብሔር እንደ ወንጀለኛ ቆጠረው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ በ2ቆሮንቶስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 21 ላይ የተናገረው ስለዚሁ ነው፡፡

> እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው። (2ቆሮ 5፥21)

*"ይህ ፍትሃዊነት ነውን፣ አግባብስ ነውን፣ የእኛንስ ኃጢአት በክርስቶስ ላይ መቁጠሩ ለእግዚአብሔር ጽድቅ ይሆንለታልን?" የሚሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ስንጀምር፣ ወደ ሰብዓዊ የህግ ችሎት ሄደን "በግድያ የሚጠየቅን የአንድን ሰው ወንጀል ግድያውን ባልፈጸመ አንድ ሰው ላይ እንዲቆጠር ማድረግ እንችላለንን?" ብለን ለመጠየቅ እየሞከርን ነው ማለት ነው፡፡ መልሱ "አይቻልም" ነው፡፡ ከሰብዓዊ ፍትህ አንፃር ስህተት ነው፡፡ ነገር ግን ስለ እግዚአብሔር ፍትህ የምናውቀው የመጀመሪያ ነገር ፍፁም መሆኑን ነው፣ እናም ፍፁም በመሆኑ ምክንያት፣ የሚሠራው ነገር ሁሉ ፍፁም መሆኑን እናውቃለን፡፡ እንደምታውቁት ግን መጽሐፍ ቅዱስ በእውነት ለምን ፍፁም እንደሆነ ይነግረናል፡፡ ለምሳሌ፣ እግዚአብሔር በድንገት አንድን ሰው መርጦ፣ የእኔን በደል እንዲያው በመላ በእርሱ ላይ ቢጭንበት፣ በፍፁም አግባብነት ያለው አይሆንም፣ ፍትሃዊም አይደለም፡፡ የእግዚአብሔርንም የጽድቅ ልክ አያሟላም፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን የሰው ዘር በልጁ አማካይነት ሊቤዥና የእኛን ኃጢአት ሊሸከም ብቃት ባለውና እንከን በማይገኝበት ጽድቁና መታዘዙ ምክንያት ኃጢአታችንን እንዲያስተሰርይ ገና የሰው ዘር ከመፈጠሩ አስቀድሞ ቢወስንስ? እንዲያው ለአንድ ሰው ብድግ ተብሎ "በል ይህንን ኃጢአት ትሸከማለህ" ተብሎ በመላ የተሰጠ ሃላፊነት፣ ያለ ውዴታ የሆነ ሃላፊነት ባይሆንስ? ኢየሱስ በወንጌላት፣ "ነፍሴን ከእኔ ማንም አይነጥቃትም፣ እኔ ግን ነፍሴን በፈቃዴ ለበጎቼ እሰጣለሁ" ቢልስ? ያን ጊዜ ኃጢአተኛውን የሰው ዘር ለመቤዠት በአንድ ልጁ፣ ነፍሱን በፈቃዱ በሰጠውና ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ይኖረን ዘንድ ኃጢአታችንን እንዲሸከም ባደረገው እቅዱ*

*የተገለጠውን ያህል የእግዚአብሔር ፍትህ በሌላ በምንም ነገር ሊገለጥ እንደማይችል ትረዳላችሁ፡፡ የእግዚአብሔር ፍትህ ፍፁም ነው፡፡ በመስቀል ላይ ከተከናወነውም የሚበልጥ እንከን የለሽ ምስል ሊኖር ከቶውኑ አይችልም፡፡*
*[ዶ/ር አር. አልበርት ሞህለር፣ ትንሹ]*

የእኛ ኃጢአት በክርስቶስ ላይ መቆጠሩን ተመልክተናል፣ አሁን ደግሞ ከስቅለቱ ጋር ወደሚገናኘው ሁለተኛ ርዕሳችን ወደ ፍርድ እንዛወር፡፡

## ፍርድ

ሰብዓዊ ሞት በኃጢአት ላይ የተበየነ መለኮታዊ ፍርድ ነው፡፡ ይህንንም በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ከቁጥር 17 እስከ 19፤ በሕዝቅኤል ምዕራፍ 18 ቁጥር 4 እና በሮሜ ምዕራፍ 5 ከቁጥር 12 እስከ 21 ባሉት ውስጥ እናገኘዋለን፡፡ ኃጢአት በሰው ዘር የመጣው አዳም በዘፍጥረት 3 ኃጢአትን ሲሠራ ነው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ቀጥሏል ምክንያቱም የአዳም ኃጢአት በእኛ ላይ ተቆጥሯልና፡፡

የኢየሱስም ሞት በኃጢአት ላይ የተላለፈ መለኮታዊ ፍርድ ነው፡፡ እግዚአብሔር የእኛን ኃጢአት በእርሱ ላይ ሳይጭን፣ ኢየሱስ ሊሞት አይችልም፡፡ በመስቀል ላይ ኃጢአታችን በእርሱ ላይ ከተቆጠረ በኋላ ግን፣ መሞቱ አይቀሬ ብቻ ሳይሆን አስፈላጊም ነበር፡፡ ይህንን ለመሰለው ትልቅ በደል እግዚአብሔር ሊሰጠው የሚገባ ፍትሃዊ ምላሽ ይኸው ብቻ ነበር፡፡ ኢየሱስ በተጨማሪም ከትንሣኤው በፊት ለሦስት ቀናት በሞት ኃይል ስር መቆየቱ የዚሁ ፍርድ አካል ነበር፡፡ የምሥራቹ ግን በኃጢአታችን ላይ እግዚአብሔር የሚቆጣውን ቁጣ እርሱ ተሸከመልን፣ ስለዚህም እኛን የሚያስፈራን የመለኮታዊ ፍርድ ቅሪት የለም፡፡ ኢየሱስ በዮሐንስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 24 እንደተናገረው ማለት ነው፡

> እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፥ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም። (ዮሐ 5፥24)

*ኃጢአትን ፍቺ የምሰጠው እኔ ብሆን ኖሮ፣ ስለ ምንነቱ እሰጠው የነበረው እጅግ ጥቅል የሆነውን አመለካከት ነበር፡፡ ሆኖም እግዚአብሔር ስለ ኃጢአት ያለው መረዳትና የእርሱን ፍርድ ስለሚያስከትለው አደገኛነቱ የሚሰጠው ብይን ልሰማ ከምችላቸው ፍቺዎች ሁሉ የተመረጠው ነው፡፡ በመሠረቱ ኃጢአቴን መመልከት ደስ ኢያሰኘኝም፡፡ ኃጢአት በሕይወቴ ወይንም በዓለም ላይ የሚያስከትለውን ፍዳ አልወደውም፡፡ እግዚአብሔር ካልፈረደበት ግን፣ ማንም ሊገታው አይችልም፡፡ እኔም ከኃጢአት ተፈጥሮ*

*ማምለጥ የምችልበት መንገድ ይገኝ ይሆንን ብዬ እሞክር ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ፍርድ ማለት ግን እርሱ ኃጢአት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ያውቃል፣ የሠራሁትን በደል ያውቃል፣ ደግሞም ኃጢአት በእኔ ዙሪያና በእኔ ላይ የሚሠራውን ያውቃል ማለት ነው፡፡ እናም እነዚህን ፈተናዎቼንና ትግሎቼን ለማሸነፍ ጌታ በመስዋዕታዊ ሞቱ ራሱን መስጠቱ በዙሪያዬ ለሚያደባው የኃጢአት ፈተና ትክክለኛው ምላሽ ነው፡፡ ያለዚያ ፍርድ፣ ያለዚያ መረዳትና ኃጢአት ብለን የምንጠራውን አሰቃቂ ነገር በዚያ ዓይነት የጽድቅ መንገድ ባይጋጠመው ኖሮ ቤዛነት አይገኝም ነበር፡፡ እንግዲያው የክርስቶስ ስርየት ብቸኛው መልካም የምሥራች ነው፡፡ በዓለም ላይ ያሉ ሌሎች ሃይማኖቶች ኃጢአት ብለን የምንጠራውን ነገር ወይንም የኃጢአትን እይታ፣ ለመሸሽ በመሞከር፣ ስሙንና መልኩን ቀየር ለማድረግ፣ ኃጢአት ብሎ ነገር የለም በማለት፣አካልን በመካድ ሊጋጠሙት ይፈልጋሉ፡፡ ኢየሱስ ግን በጽድቅ ፍርዱ ተሞልቶ መጣ፣ ኃጢአትም ምን እንደሆነ በትክክል ነገረን፡፡ ይህንንም ካደረገ በኋላ፣ ሁሉንም ነገር ጠቅልሎ ወሰደውና በመስቀል ላይ ጨረሰው፡፡ ስለዚህ ለክርስቲያኖች፣ ደግሞም ለሁሉም ሰው፣ ከሁሉ የሚበልጠው የምሥራች ይህ ነው፡፡ [ዶ/ር ቢል ዩሪ]*

*ኢየሱስ ሥጋ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ ሥጋ የሆነው ቃል ነው፡፡ እርሱ በእግዚአብሔር ዘንድ የነበረው ቃል፣ እግዚአብሔር የነበረው ቃል ነው፡፡ አባቱን ሊገልጥ ከአባቱ ልብ ውስጥ ወጥቶ የመጣው ልጅ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ሕይወቱን በመስቀል ላይ ሲሰጥ፣ ፍርዳችንን ሲወስድ፣ በአመፀኝነታችንና እግዚአብሔርን በመካዳታችን ፊት እግዚአብሔር ራሱ በልጁ በኩል የእኛን በደል እንደ እርሱ ቆጥሮ እርሱ ራሱ ፍርዳችንን ተሸከመልን፡፡ ምን ዓይነት የምሥራች ነው? እግዚአብሔር እጅግ ይወደናል ስዚህም የኃጢአት ዕዳችንን ራሳችን እስክንከፍል አልጠበቀም በዚህም እርሱን አወቅነው፡፡ እኛንና እርሱን የለያየንን ገደል በራሳችን መሸጋገሪያ እስክንሠራለት አልጠበቀም፡፡ ነገር ግን ወደ እኛ መጣና የኃጢአትን አስጠያፊነቱን፣ እርጉምነቱን፣ ክፋቱን እና ሰይጣናዊነቱን በራሱ ላይ ጫነ፣ ከዚያም ምህረቱን ብቻ ሳይሆን መለኮታዊ ኀልዎቱን፣ መለኮታዊ ሕይወቱን እና መለኮታዊ ፍቅሩንም በልባችን ውስጥ አፈሰሰ፡፡ ይህም እጅግ መልካም ዜና ነው፡፡ [ዶ/ር እስቴፈን ብላክሞር]*

በዚህ ትምህርታችን፣ የኢየሱስን የክርስቶስነት ወይንም የመሲህነት አገልግሎት በሦስት ክፍለ ጊዜያት ከፍለን ተመልክተናል፡ ልደቱና ዝግጅቱ፣ የአደባባይ አገልግሎቱ እና ህማማቱና ሞቱ፡፡ አሁን ደግሞ በመጨረሻ፣ የኢየሱስን እንደ ክርስቶስ መክበር እንመለከታለን፡፡

# 5. ክብር

የኢየሱስን መክበር ከትንሣኤው አንስቶ ወደፊት በግልጽ ተመልሶ እስከሚመጣበት ጊዜ ድረስ ያሉትን ዘመናትት አካትተን እንመለከታለን፡፡ በመጀመሪያ የዚህን ክፍለ ጊዜ ጠቅለል ያለ መግለጫ በመመልከት እንጀምራለን፣ ከዚያም ጥቂቶቹን ዘርዘር አድርገን እንመለከታለን፡፡

ከስቅላቱና ከመቀበሩ በኋላ ባለው የሳምንቱ ፊተኛ ቀን፣ ኢየሱስ ከሞት ተነሣ፡፡ ለአርባ ቀናትም ለበርካታ ደቀመዛሙርቱ ታየ፡፡ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት አስተማራቸው፣ የቅዱሳት መጻሕፍት ፍጻሜ የሆነውን የእርሱን ድርሻ አብራራላቸው፣ የእርሱንም ቤተክርስቲያን አመራር በደቀመዛሙርቱ አማካይነት መሠረተ፡፡ እነዚህ ሁነቶች በማቴዎስ ምዕራፍ 28፤ በማርቆስ ምዕራፍ 16፤ በሉቃስ ምዕራፍ 24፤ በዮሐንስ ምዕራፍ 20 እና 21 እና በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 1 እስከ 11 ተመዝግበዋል፡፡

በነዚህ አርባ ቀናት ፍጻሜ ላይም ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ባረካቸው እያዩትም ወደሰማይ አረገ፣ መላዕክትም ተመልሶ እንደሚመጣ አወጁ፡፡ እነዚህ ጭብጦች በሉቃስ ምዕራፍ 24 ከቁጥር 36 እስከ 53 እና በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 1 እስ 11 ተመዝግበዋል፡፡

ካረገ በኋላም ኢየሱስ ሞቱን የኃጢአት መስዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር ካቀረበ በኋላ በአብ ቀኝ ተቀመጠ፡፡ በዚህም በሕዝቦቹ ጉዳይ ላይ ገዢ መሆን ጀመረ፣ ይህም ተመልሶ መጥቶ በጠላቶቹ እስኪፈርድና ሕዝቦቹንም በአዲሲቷ ሰማይና ምድር እስኪባርክ ድረስ ይቀጥላል፡፡ ይህንንም በኤፌሶን ምዕራፍ 1 ከቁጥር 20 እስከ 22፤ በ2ተሰሎንቄ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 7 እስከ 10 እና በራዕይ ምዕራፍ 20 ከቁጥር 11 እስከ ምዕራፍ 22 ቁጥር 7 በዝርዝር እናገኛለን፡፡

የኢየሱስን መክበር አራት ገፅታዎች ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ትንሣኤውን እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ እርገቱን እናነሳለን፡፡ ሦስተኛ፣ በሰማይ ያለውን ቆይታ እንመለከታለን፡፡ አራተኛ፣ ዳግም በግልፅ መመለሱን እንመለከታለን፡፡ ከሞት በመነሣቱ እንጀምር፡፡

## ትንሣኤ

ሞት የሰው ዘር ከሚጋፈጣቸው አሳዛኝ ክስተቶች መካከል ትልቁና ኃጢአት በዓለም ላይ ያመጣው አስከፊ ገፅታ መገለጫ ነው፡፡ የምሥራቹ ግን እግዚአብሔር ክርስቶስን ስለ እኛ ሞትን ድል እንዲነሣ የቀባው መሆኑ ነው፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከመቃብር ሲወጣ፣ እርሱ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን ያገኘውና የመንግሥቱም ወራሽ የሆነው ልጁ መሆኑን

ለፍጥረት ሁሉ አረጋገጠ፡፡ ከዚህም በላይ የሚያስደንቀው፣ የእርሱ ታማኝ ተከታዮች ወደ ፊት የሚነሱ መሆኑን ማረጋገጡ ነው፡፡

የኢየሱስን ትንሣኤ አስመልክቶ ዘርዝረን የማንጨርሳቸው በርካታ ወሳኝ ገፅታዎች አሉ፡፡ ስለዚህ ትኩረታችንን በሁለቱ ላይ ብቻ እናደርጋለን፣ የእግዚአብሔርን የመቤዠት ዕቅድ የሚያፋጥን መሆኑን በመመልከት እንጀምራለን፡፡

# የመቤዠት ዕቅድ

የእግዚአብሔር የሰውን ዘርና ተፈጥሮን በጠቅላላ የመቤዠት ዕቅድ ሙሉ በሙሉ የሚያርፈው በራሱ ላይ ነው፡፡ ይህም የእርሱን መንግሥት በምድር ላይ በዳዊት ዘር በኩል በሌላ አባባልም በክርስቶስ መልሶ ለመመስረት በሰጠው የኪዳን ተስፋ ፍፃሜ ላይ ያርፋል፡፡ ኢየሱስ ሞቶ ቢቀር ኖሮ ይህንን ሊፈፅም አይቻለውም፡፡ በዚህ ረገድ፣ የኢየሱስ ትንሣኤ እግዚአብሔር የኪዳን ተስፋውን ለመፈፀም ያስቻለው እጅግ ወሳኝ እርምጃ ነው ማለት ነው፡፡ በሉቃስ ምዕራፍ 24 ከቁጥር 45 እስከ 46፤ በዮሐንስ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 17 እስከ 22፤ የሐዋርያት ሥራ 17 ቁጥር 3 እና ሮሜ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 1 እስከ 4 ላይ እንደምናየው፣ አዲስ ኪዳን ትንሣኤን የኢየሱስ የክርስቶስነት አገልግሎት ማረጋገጫ ብሎ የሚጠራው ለዚህ ነው፡፡

ሁለተኛ የምናነሳው የኢየሱስ ትንሣኤ ገፅታ ለአማኞች በርካታ የድነት በረከቶችን የሚያስገኝ መሆኑን ነው፡፡

# የድነት በረከቶች

አዲስ ኪዳን የኢየሱስን ትንሣኤ ከድነታችን ጋር ከምንቀበላቸው በረከቶች ጋር አያይዞ ይጠቅሰዋል፡፡ በሮሜ ምዕራፍ 4 ቁጥር 25 እንደተጠቀሰ የኃጢአትን ይቅርታ ያገኘንበትን ጽድቅ አስገኝቶልናል፡፡ በ1ጴጥሮስ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 3 እስከ 5 እንደተገለፀው በመንፈስ ዳግም የመወለዳችን ምንጭና ዘላለማዊ ውርስን የምንቀበልበትን ደጅ የከፈተልን እርሱ ነው፡፡ በ2ቆሮንቶስ ምዕራፍ 4 ከቁጥር 10 እስከ 18 እንደምናነበውም በሰውነታችንና በሕይወታችን እውነተኛ የክርስቶስ ምስክር የምንሆንበትን በጎውን ሥራ በእኛ የሚሠራም እርሱ ነው፡፡ በሮሜ ምዕራፍ 6 ቁጥር 4 እና 5፤ በ1 ቆሮንቶስ ምዕራፍ 15 ከቁጥር 42 እስከ 53 እንደምናነብበው ኢየሱስ የለበሰውን አካል የምንለብስበት የአማኞች የወደፊት አካላዊ ትንሣኤ ምንጭም ነው፡፡ ምንም እንኳን ክርስቲያኖች ይህንን መሳዩን በረከት ከስንት አንድ የምናስበው ቢሆንም፣ አሁን እየተደሰትንባቸው ያሉትንና ወደፊትም የምናገኛቸውን የድነት በረከቶች ለማግኘት የክርስቶስ ትንሣኤ እጅግ ወሳኝነት አለው፡፡

*የኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት መነሣት የአዲስ ኪዳን ማዕከላዊ ነጥብ ነው፡፡ ከዚያም ውስጥ በርካታ በረከቶች ይወጣሉ፡፡ በመጀመሪያ፣ ትንሣኤ ኢየሱስ ማን እንደሆነ ያስተምረናል፡፡ እርሱ መሲህ፣ ጌታና የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ያረጋግጥልናል፡፡ ስለዚህም ስለኢየሱስ ታላላቅ ነገሮችን ያስተምረናል፣ በዚያም ውስጥ ድንቅ በረከቶች አሉ፡፡ ከዚያም ባለፈ፣ ለክርስቲያኖች ይህ ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ ዛሬም ሕያው ነው ማለት ነው፡፡ ከሞት ተነሥቷል፣ ስለዚህም እርሱ አሁን ልናውቀውና ልናገኘው የምንችለው ነው ማለት ነው፡፡ ከዚያም በበለጠ፣ የኢየሱስ ኃይል፣ የትንሣኤው ኃይል፣ ለእኛም ይሠራል ማለት ነው፡፡ በመሠረቱም እኛ ይህ አዲስ ሕይወት በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በውስጣችን ሊኖር እንደመጣ እናምናለን፡፡ ስለዚህ እንደ ክርስቲያን መኖር ማለት በራሳችን ብርታት ኢየሱስን ለመከተል መሞከር ማለት አይደለም፡፡ የእርሱ የትንሣኤ ጉልበት በውስጣችን ይኖራል ማለት ነው፡፡ በእርሱ ውስጥ የበለጠ ነገር አለ፡፡ ማለቴም፣ ትንሣኤ ስለወደፊታችን አስደናቂ ተስፋን ይሰጠናል፣ ትንሣኤ ስንሞት የሚጠብቀንን የሚያመለክት ነው፡፡ የኢየሱስን ትንሣኤ ስንመለከት፣ ሞት የመጨረሻችን አለመሆኑን የሚያመለክተውን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን እንመለከታለን፤ ከመቃብር ማዶ አዲስ ሕይወት አለ፣ ትንሣኤ! አዲስ አካል (ሕይወት) አለ፡፡ ስለዚህም ለክርስቲያኖች ከትውልድ ወደ ትውልድ፣ በሞት ውስጥ ስናልፍ ከበስቲያ አስደናቂ ተስፋ ይጠብቀናል፡፡ በኢየሱስ ስናምን በሞት በኩል የእርሱ ሕይወት ተካፋዮች ያደርገናል፡፡ አንድ ሌላ ነገር ልጨምር፣ ትንሣኤ በተጨማሪም እግዚአብሔር ፍጥረትን እንደሚያድስ ኪዳን የመግባቱ ምልክት ነው፡፡ የኢየሱስ ሰውነት አካላዊ ሰውነት ነው፣ ከትንሣኤ በኋላ መንፈስ ሆኖ ብቻ አልተገለጠም፣ አካላዊ ሰውነት ነበረው፡፡ ስለዚህም እግዚአብሔር የሰውን ዘር እንደገና እንደሚቤዥና እንደሚያድስ የሚያመለክት ነው፡፡ ተፈጥሮ ከፋት የለበትም፣ ወደፊት የሚታደስ ነገር ነው፡፡ ይህም ሃሳብ ሐዋርያው ጳውሎስ ፍጥረት በሙሉ እንደገና እንደሚታደስ በተናገረበት በሮሜ ምዕራፍ 8 ላይ ዝርዝር ትምህርት ተሰጥቶበታል፡፡ ይህንንም ፍንጭና መተማመኛ የሚሰጠን ትንሣኤ ነው፡፡ [ዶ/ር ፒተር ዎከር]*

የኢየሱስን ትንሣኤ በልቡናችን እንያዝና፣ ወደ ሰማይ ማረጉን እንዳስስ፡፡

## ዕርገት

የኢሱስ ዕርገት የተከሰተው በተዓምራዊ መንገድ፣ በእግዚአብሔር ልዩ ኅላዌ ወደ ሰማይ ሲወሰድ ነው፡፡ አሁን፣ በመሠረቱ፣ የእግዚአብሔር ልጅ በመለኮትነቱ በሁሉም ስፍራ በሁሉም ዘመን ይኖራል፡፡ ሰብዓዊ ማንነቱን በተመለከተ ግን፣ ዕርገት የኢየሱስ ሥጋና ነፍስ ከምድራዊው ዓለም ወደ ሰማያዊው ዓለም በመላእክት ታጅቦ እንዲሄድ አድርጓል፡፡ ቅዱሳት

መጻሕፍት ይህንን ሁነት በሉቃስ ምዕራፍ 24 ከቁጥር 50 እስከ 53 እና የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 9 እስከ 11 መዝግበውታል፣ በሌሎችም ስፍራዎች በማጣቀስ ተቀምጧል፡፡

ከዕርገቱ ጋር በተያያዘ የኢየሱስን የክርስቶስነት አገልግሎት ሁለት ገፅታዎች እንዳስሳለን፡፡ ኢየሱስ ለሐዋርያቱ የሰጣቸውን ሐዋርያዊ ሥልጣን እና በእግዚአብሔር ቀኝ በንግሥና መቀመጡን ማለት ነው፡፡ አስቀድመን ሐዋርያዊ ሥልጣንን እንመልከት፡፡

## ሐዋርያዊ ሥልጣን

ኢየሱስ ለየት ባለ መንገድ ኃጢአትን ማስተሰረዩንና ጽድቅን ሁሉ መፈጸሙን ተከትሎ፣ እግዚአብሔር በፍጥረት ሁሉ ላይ ተስተካካይ የማይገኝለት ሥልጣንና ኃይል ሰጠው፡፡ በማቴዎስ 28 ቁጥር 18 ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንደነገራቸው፡

*ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ*

ከዚያም በበለጠ፣ ኢየሱስ በዕርገቱ ደቀመዛሙርቱ በእርሱ ምትክ በማይሻር ሥልጣን ይናገሩና ቤተክርስቲያንን ይመሠርቱ ዘንድ ከዚህ ሥልጣኑ አካፈላቸው፡፡ ይህንን ሥልጣን የተቀበሉት ዐሥራ አንዱ የታመኑ ደቀመዛሙርትና፣ አሳልፎ በሰጠው ይሁዳ የተተካው በሐዋርያት ሥራ 1 ቁጥር 26 የተጠቀሰው ማቲያስ ሲሆኑ፣ ጳውሎስ ደግሞ ለየት ባለ መንገድ ሥልጣኑን የተቀበለው ናቸው፡፡ ከተሰጣቸውም ከዚህ ሥልጣን የተነሣ፣ እነዚያ ሐዋርያት ቅዱሳት መጻሕፍትን ይጽፉና ያረጋግጡም ነበር ደግሞም የማይሻሩ አስተምህሮዎችንም ያቀርቡ ነበር፡፡ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 24 እስከ 26 እንደምንመለከተው፣ ይህ ሥልጣን በቀጥታ ከኢየሱስ ለተቀበሉ ሐዋርያት የተሰጠ ልዩ ሥልጣን ነው፣ ስለዚህም በምንም መንገድ ወደ ሰው ዘር ሊተላለፍ አይችልም፡፡ ስለዚህም በዚያ ደረጃ የሚስተካከል ሥልጣን ያላቸው ሐዋርያት የሉም፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ዓለም አቀፋዊቷ ቤተክርስቲያን ምን እንደምትመስል በተናገረበት በኤፌሶን ምዕራፍ 2 ቁጥር 19 እና 20 ላይ እንዲህ ሲል ይህንን አረጋግጧል፡

> እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም።
> በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፥ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤

ይህ ሥልጣን የተሰጣቸው ሐዋርያት በቤተክርስቲያን ካሉት ከሌሎቹ ሁሉ የተለዩና ለዓለም አቀፋዊቷ ቤተክርስቲያን በጅማሬዋ ወቅት የተሰጡ ናቸው፡፡

ይህንን ሐዋርያዊ ሥልጣን በልቡናችን ይዘን፣ የኢየሱስን ወደ ሰማይ ማረግ ሁለተኛ ገፅታ የሆነውን ንግሥናውን እንመለከታለን፡፡

## መንበረ-ንግሥና

*አሁን፣ የክርስቶስ በሰማያት በእግዚአብሔር ቀኝ መቀመጥ ማለት ክርስቶስ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ጠላቶች ሁሉ ላይ ድልን ተቀዳጅቷል ማለት ነው፡፡ በተለይም በኤፌሶን መጽሐፍ ውስጥ በምዕራፍ 2 ጳውሎስ የሚናገርባቸው ጠላቶች በአየር ላይ ያሉትን መንፈሳውያን ኀይላት ማለትም የአሁኑን የጨለማው ዓለም ገዢዎችን ማለት ነው፡፡ እነዚህ ኀይላት በክርስቶስ ከሞት መነሣት ድል ሆነዋል፣ ክርስቶስም በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀጧል፡፡ አስደናቂው የምሥራች ደግሞ እኛም በእግዚአብሔር ቀኝ መቀመጣችን ነው፡፡ ስለዚህ እኛም እንደክርስቲያኖች በዚህ ዓለም የክፉ ኀይላት ላይ ድልን ተቀዳጅተናል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ አንዳንዶች እንደሚሉት እነዚህ ኀይላት በእኛ ላይ ኀይል የላቸውም ስለዚህም የማይታዩትን ኀይላት ልንፈራ አይገባንም፡፡ እነዚህን መፍራት አይገባንም ምክንያቱም ኢየሱስ ድል አድርጓቸዋል፣ እኛም ከእርሱ ጋር ድል አድርገናል፡፡ [ዶ/ር ፍራንክ ቴይልማን]*

ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲያርግ፣ መስዋዕቱን በሰማያት ባለው መቅደስ ካቀረበ በኋላ፣ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀመጠ፡፡ ይህም የሁነቶች ቅደም ተከተል፣ በዕብራውያን ምዕራፍ 1 ቁጥር 3፣ ምዕራፍ 9 ከቁጥር 11 እስከ 14 እና በምዕራፍ 10 ከቁጥር 12 እስከ 14 ተጠቅሷል፡፡

በእግዚአብሔር አብ ቀኝ የመቀመጡ ተግባር ኢየሱስ እንደ እግዚአብሔር አብ ሎሌ ወይም እንደ አገልጋይ ንጉሥ በሰማያት መቀመጡን ያመለክታል፡፡ የመሲሃዊው የክብር ስፍራ አስቀድሞ የተተነበየው በንጉሡ ዳዊት በመዝሙር 110 ላይ ነው፡፡ አሁን ደግሞ ያ ለኢየሱስ እንደተሰጠ አዲስ ኪዳን ደጋግሞ ያነሳዋል፡፡ ለምሳሌ፣ ይህንን በማርቆስ ምዕራፍ 16 ቁጥር 19፤ በሉቃስ ምዕራፍ 22 ቁጥር 69፤ በኤፌሶን ምዕራፍ 1 ቁጥር 20 እና 21 እና በ1ጴጥሮስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 22 እንመለከታለን፡፡

መንበረ-ንግሥናው የኢየሱስን የክርስቶስነት አገልግሎት ወደሙላት አምጥቶታል፡፡ እርሱ በአካለ *ሥጋ* ከመገለጡና በጥምቀቱ ወቅት ከመቀባቱ አስቀድሞም ተመርጧል፡፡ እስኪያርግና ዙፋኑን ይዞ በሙላት እስኪገዛ ድረስ ግን ምሉዕ አልነበረም፡፡

*የጌታችን እያንዳንዷ ተግባርና እንቅስቃሴ፣ እያንዳንዷቷም ከእኛ ጋር የሚኖረው የግል ግንኙነት ጊዜ ሁሉ ለቤዛነት አስፈላጊዎች ናቸው፡፡ በእግዚአብሔር አብ ዙፋን ቀኝ የመቀመጡም እውነታ፣ በመንፈሳዊ ቋንቋ ስንናገረው፣ በሰው ዘር ታሪክ ፍፃሜ ላይ ድል የሚጠብቀን የመሆኑ ማረጋገጫ ነው፡፡ እርሱ ጦርነቶችን ሁሉ ድል ያደረገ ንጉሥ ነው፡፡ ምናልባት አሁን በሙላት አንረዳው ይሆናል፣ እውነታው ግን ድል መንሳቱ ነው፡፡ ይህ መንፈሳዊ እሳቤ ነው፡፡ የፍጥረተ ዓለሙ ሁሉ መታደስ፣ ሁሉን ገዢነቱ፣ ለእኛ፣ እርሱ ጌታና ንጉሥ የመሆኑ ምስሎች ናቸው፡፡ ስለኢየሱስ ማንነት የምናስታውሰው ትልቅ ነገር፣ የነገሠውና የከበረው ሰው መሆኑ ነው፡፡ ሰው የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የእርሱ ትስጉትነት ፈጽሞ አይጠፋም፡፡ እርሱ አንድ ዓይነት መንፈስ አልሆነም፡፡ የሰውን ዘር ወደ ሰማያት ይዞ ገባ፣ በእግዚአብሔር አብ ቀኝም የተቀመጠው አይሁዳዊው አናፂ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፡፡ ስለ እኛም ሊያማልድ ለዘላለም ይኖራል፡፡ በገሃድ የታየውን ያንን የማያዳግም ድል ያስገኘ ደንቅ ጌትነት፣ ሉዓላዊነት እና ጌትነት በአንድነት በእርሱ ውስጥ አለ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ደግሞ አስደናቂው ቁርኝት፣ እኛን በእርሱ ውስጥ መሰወሩ፣ ስለ እኛ መማለዱ፣ ያ ጉልበታም ጸሎቱና ስለ እኛ ሕይወት ግድ መሰኘቱም ይቀጥላሉ፡፡ ስለዚህ ይህ ፍፁም አዳኝ ለእኛ ምሳሌ ሆኖ በዙፋን ላይ ተቀምጧል፡፡ አዎን፣ እርሱ ሊመለክና ሊሞገስ የተገባው ነው፣ ሆኖም የተገባው መሆኑ፣ ከዚህ ከአስደናቂው ራስን የመስጠት አስደናቂ እሳቤ ጋር ሚዛኑን ጠብቀን ስናስኬደው የበለጠ ይጎላል፡፡ ለረጅም ዓመታት ከክርስቶስ ኢየሱስ ደም የሚፈሳቸው ቁስሎቹ ጋር ተያይዘው በአሁን ጊዜ ስለሚዘመሩ መዝሙሮች አስባለሁ፡፡ ቀደም ብሎ የነበረኝ ምላሽ፣ አዎን ደምቷል ከዚያ ሞቷል የሚል ነበር፡፡ ግን ስለ ንግሥናው እየተዘመረ፣ በቀራኒዮ ስለተከናወኑትና ደም ስለሚፈሳቸው አምስት ቁስሎቹ ሲነገር ኋላ ሲገባኝ፣ ማለት የፈለጉት ትሥጉትነቱን አትርሱ፣ የንግሥና ሕይወቱ ሥግው ክርስቶስ የሰማይና የምድር ጌታ ነው ደግሞም የዕለት ከዕለት መሻታችንም ጌታ ነው ማለት ነው፡፡ እናም እንደ ክርስቲያኖች እርሱ በዙፋን ላይ ሆኖ ዛሬም የሚሠራውን ሥራ ስናስብ ይህ ነገር ትልቅ እንድምታ አለው ማለት ነው፡፡ [ዶ/ር ቢል ዩሪ]*

የኢየሱስን መክበር ከትንሣኤውና ከዕርገቱ አኳያ ከዳሰስን፣ አሁን ደግሞ በሰማያት ስለሚኖረው አገዛዝ እንመልከት፡፡

# አገዛዝ

“አገዛዝ” የሚለው ቃል ኢየሱስ በሰማያት በግርማዊነትና በኀይል የሚገዛበትንና የሚያስተዳድርበትን ተግባር የምንገልጥበት ነገረ-መለኮታዊ ቋንቋ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ እግዚአብሔር ሎሌያዊ ንጉሥ በመንበረ- ንግሥናው የሚያከናውናቸውን ሁሉ የሚያመለክት ነው፡፡

ቅዱሳት መጻሕፍት ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን ስለሚያደርጋቸው ነገሮች ሲጠቅሱ፣ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀምጧል ይላሉ፡፡ ይህ ቋንቋ አንዳንድ የዘመኑን መሪዎች ወደ ተሳሳተ መንገድ ይመራቸዋል፡፡ ኢየሱስ ከአብ ቀኝ ተቀምጦ የመመለሻውን ቀን እየጠበቀ ነው ማለት አይደለም፤ በዙፋን ላይ ተቀምጧል፡፡ ያም ማለት በመንግሥቱ ላይ ይገዛል ማለት ነው፡፡ በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠ ሎሌያዊ ንጉሥ ነው፡፡ እናም ተመልሶ እስኪመጣ በእኛ ላይ መግዛቱን ይቀጥላል ስለ እኛም ይማልዳል፡፡ የኢየሱስ አገዛዝ እርሱ በኀጢአትና በሞት ላይ ድል የነሳ መሆኑን ሲያረጋግጥ፣ በሕይወት ዘመናችን ሁሉ በሚገጥሙን ችግሮች መካከል የማያቋርጥ መፅናናትን እንዲሰጠን ሥልጣንን ሰጥቶታል፡፡

> *ስለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ እንደተቀመጠ ይነግሩናል፡፡ ይህም ክርስቶስ በቤተክርስቲያንና በፍጥረተ ዓለሙ ላይ የገዢነትን ሥልጣን እንደተቀበለ የሚያመለክት ስነ-ሰብዓዊ መግለጫ ነው፡፡ በዕርገቱም ወቅት፣ ከዚህ ጋር የሚስተካከልን ክብር እንዲካፈል ተደርጓል፡፡ ይህ የመቀመጡ መግለጫ ግን፣ ኢየሱስ ወደ ዕረፍት ስፍራ ማረጉን ኢያመለክትም፡፡ ይልቁኑ፣ የእኛ ንጉሥ፣ የእኛ ነቢይና የእኛ ካህን የመሆን ሥራውን ይቀጥላል፡፡ [ቄስ ጂም ማፐልስ]*

ኢየሱስ በሰማያት አገዛዙ ወቅት የሚሠራውን ሥራ ከከበረው ክርስቶስነቱ ድርሻ አንፃር የሚታዩትን ሦስት ገጽታዎች እንመለከታለን፡ አንደኛ፣ የእርሱን ትንቢታዊ ቃልና መንፈስ፡፡ ሁለተኛ፣ በአብ ፊት የሚያቀርበውን ካህናዊ ምልጃ፡፡ ሦስተኛ፣ በህዝቡ ላይ ያለውን ንጉሣዊ አገዛዝ እንመለከታለን፡፡ በመጀመሪያ የኢየሱስን ትንቢታዊ ቃልና መንፈስ እንመልከት፡፡

# ቃልና መንፈስ

የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 ቁጥር 33 ስንመለከት፣ ኢየሱስ ትንቢታዊ አገልግሎቱን ከገለጠባቸው ተቀዳሚ መንገዶች አንዱ መንፈስ ቅዱስን ለቤተክርስቲያን ስጦታ አድርጎ መላኩ ነው፡፡ ሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 መንፈስ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲመጣ፣ በእሳት ልሳኖች፣ እንደሚነጥቅ አውሎ ነፈስ በመሰለ ደምፅ፣ በየስፍራው በተበተኑ አይሁድ ቋንቋዎች እግዚአብሔር በሚመሰገንበት ኩነት እንደታጀበ መዝግቦልናል፡፡ ይህ ትንቢታዊ

*ሥራ ነው ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያንን በዓለም ላይ የኢየሱስ ትንቢታዊ ምስክር እንድትሆን ኀይልን ይሰጣታልና ነው፡፡ ጴጥሮስም እነዚህ ምልክቶች፣ በነቢዩ በኢዩኤል ምዕራፍ 2 በዘመኑ መጨረሻ መንፈሱ የእርሱን ታማኝ አገልጋዮች በኀይል እንደሚሞላቸው የተነገረው ትንቢት ፍጻሜ መሆናቸውን አብራርቷል፡፡*

ከበዓለ ሃምሳ ዕለት አንስቶ፣ የጰንጠቆስጤው ያልተለመደ መገለጫ ከተለመደው ሥርዓት ውጪ ቢሆንም እንኳን ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስ ትንቢታዊ በሆነ መንገድ ቤተክርስቲያንን ያገለግል ዘንድ መላኩን ቀጠለ፡፡ በዋናት ግን ዋነኛው የተለመደ ነገር መንፈሱን የሚልከው ቅዱሳት መጻሕፍትን ስናነብብ ግልጠትንና መረዳትን እንድናገኝ ነበር፡፡

በአገዛዙ ዘመን ውስጥ የኢየሱስ ትንቢታዊ አገልግሎት የቅዱሳት መጻሕፍትን አብርሆት መስጠትንም ያካትታል፡፡ እንደ 2ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 16 እና 17 እና 2ጴጥሮስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 15 እና 16 የመሳሰሉትን ስናነብብ ሐዋርያቱ የክርስቶስን የማይሻር ቃል ለህዝቡ በመነዳት ይጽፉ ዘንድ እንዲያበራላቸው መንፈሱን ይልክ እንደነበር እንረዳለን፡፡ ፊልጵስዩስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 14፤ 1ተሰሎንቄ ምዕራፍ 2 ቁጥር 13 እና ዕብራውያን ምዕራፍ 13 ቁጥር 7 የመሳሰሉትን ስናነብብ ደግሞ ኢየሱስ በቃሉ አማካይነት ቅዱሳት መጻሕፍትን ስለ እኛ በመጠበቅ፣ አገልጋዮቹም ለማኅበረ ምዕመናኖቻቸው ቃሉን እንዲሰብኩና ለጠፉትም ወንጌልን እንዲያደርሱ ጸጋን ይሰጣቸው ዘንድ መንፈሱን በመላክ ቤተክርስቲያንን ማገልገሉን እንደቀጠለ እንረዳለን፡፡

ከትንቢታዊ ቃሉና መንፈሱ በተጨማሪ፣ የኢየሱስ አገዛዝ የእርሱን ካህናዊ ምልጃም ያካትታል፡፡

# ምልጃ

በዕርገቱ ወቅት፣ ኢየሱስ የሕዝቡን ኀጢአት ለማስተሰረይ የገዛ ደሙን ለአብ አቀረበ፡፡ ይህ ተግባር የማይደገም ነው፡፡ ከእርሱ የሚገኙት ጥቅሞች፣ ማለትም፡- ይቅርታ፣ መንፃት እና ፈውስን የመሳሰሉት ግን በማይቋረጥ መንገድ በሕይወታችን ተግባራዊ ሊሆኑ ይገባል፡፡ የማይገደብ መንፃት፣ ጤናና ብልጽግናን በማግኘት ደስ የምንሰኘው ግን በአዲሲቷ ሰማይና ምድር ነው፡፡ በመካከሉ ግን፣ ስለ እኛ በአብ ፊት በመታየት በምድር ሕይወታችን ከእነዚህ በረከቶች በጥቂቱ እንድናገኝ ይማልድልናል፡፡ የእርሱም ምልጃ በዕብራውያን ምዕራፍ 7 ከቁጥር 25 እስከ 26፣ ምዕራፍ 9 ከቁጥር 11 እስከ 26 እና ምዕራፍ 10 ከቁጥር 19 እስከ 22፤ በተጨማሪም 1ዮሐንስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 2 ላይ ተጠቅሶአል፡፡

> *ክርስቶስ እንደ ካህናችን የሠራው ሥራ ሁለት ገፅታዎች አሉት፡፡ ከመስቀሉ አንፃር ስናስብ ሕይወቱን ስለእኛ መስጠቱን ያካትታል፣ ምትካችን ሆኖ ስለ እኛ ወደዚያ*

*ሄዷል፣ በእኛ ስፍራ ተተክቷል፣ የእኛን ኀጢአት ወስዷል ዕዳችንንም በጠቅላላ ከፍሏል። ካህን በተጨማሪም ስለ ህዝቡ የሚማልድ፣ መካከለኛ የሚሆን፣ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል የሚሆን፣ የሚጸልይላቸው፣ የሚወክላቸው ሰው ነው። ክርስቶስ እነዚህን ሁሉ ሥራዎች ሠርቷል። የመስቀሉ ሥራ የተሠራ ለማስመሰል አልተሞከረም የካህንት የምልጃ ሥራውም ሳይከናወን አልቀረም። ፈፅሞ። የመስቀሉ ሥራ በትክክል ተከናውኗል። እርሱ ምትካችን፣ ወኪላችን ነው፣ አሁንም ስለ እኛ ይፀልያል ይማልዳልም። ይህንን ለምን ያደርጋል? ይህንን የሚያደርገው የመስቀሉ ሥራ ውጤታማ ስላልሆነ አይደለም፣ ግን ይህንን ሥራ ቀጣይነት ባለው መንገድ መተግበር ስለሚፈልግ ነው። አሁንም ኀጢአትን እናደርጋለን፤ ገና የከበረውን አካል አላገኘንም። ከዚህ ቀደም ያደረገውን ሥራ እያቀረበ በአብ ፊት ስለኛ ይማልዳል። እንዴት መጸለይ እንዳለብን ለማናውቀው ለእኛ በመንፈስ ይፀልይልናል፣ ይህንንም ስለ እኛ በመግባት፣ መካከለኛ በመሆን፣ በሕይወታችን በእያንዳንዲቷ ጉዳይ ላይ ወክሎን መስዋዕታችን እና ማላጃችን ሆኖ ያደርገዋል። [ዶ/ር ስቴፈን ዌሉም]*

በሚያሳዝን መንገድ፣ ብዙ ክርስቲያኖች ኀጢአትን ሲሠሩ በሚሰማቸው የተሳሳተ ግንዛቤ ምክንያት፣ ምንም ተስፋ የሌላቸው፣ በራሳቸውም ጥረት ለውድቀታቸው መልስን ለማግኘት የሚፍጨረጨሩ ሆነው በእግዚአብሔር ፊት ይቆማሉ። አስደናቂው እውነታ ግን ክርስቶስ በመስቀል ላይ ስለ ኀጢአታችን ዋጋ እንደከፈለ ሁሉ፣ አሁንም እርሱ ስለ እኛ በሰማያት በአብ ፊት ይማልድልናል፣ አብም ይቅር ማለቱን እንደሚቀጥልና እንደሚባርከን ያረጋግጥልናል። በእግዚአብሔር ሰማያዊ የፍርድ ዙፋን ፊት መቼም ቢሆን ብቻችንን አይደለንም፣ ኢየሱስ ያለማቋረጥ በእኛ ምትክ ይጸልያል።

*ኢየሱስ አሁንም በእኛ ሕይወት ውስጥ እንደጠበቃችን፣ እንደ አማላጃችን፣ እንደ ወኪላችን ሆኖ፣ የማይቋረጥ፣ እንደ ቅርብ ወዳጃችን ሆኖ ሃላፊነቱን እየተወጣ ነው። በታላቁም ፈራጅ ፊት በየዕለቱ፣ ያለማቋረጥ በመቆም ስለ እኛ የሚለምንልን ጠበቃችን ነው። አስደናቂው የምሥራች ደግሞ ከሠራው የስርየት ሥራ የተነሳ አንድም ጉዳያችን የማያመልጠው መሆኑ ነው። እርሱ በእኛ ምትክ ሆኖ በሊቀ ካህንነት በሠራው ፍጹምና የተጠናቀቀ ሥራ፣ ዘወትር ውጤታማና ሁልጊዜም ስኬታማ ሆኖ ስለ እኛ ይግባኝ እያለ ይኖራል። [ዶ/ር ኬ. ኤሪክ ቶኔስ]*

የኢየሱስን ቃልና መንፈስ ደግሞም ምልጃ በልቡናችን ይዘን፣ አሁን ደግሞ ወደ ንጉሥነት ድርሻው እንሻገራለን።

# አገዛዝ

የኢየሱስ አገዛዝ በኤፌሶን ምእራፍ 5 ከቁጥር 23 እስከ 29፣ ቤተክርስቲያንን እንደ ሙሽራው፣ በ1ቆሮ ምዕራፍ 12 ቁጥር 27 ደግሞ እንደ አካል በማስተዳደር የሚገለጥ መሆኑን እንደሚያካትት እንመለከታለን፡፡

እንደ ዳዊት ልጅነቱና ዝርያነቱ ደግሞ፣ ኢየሱስ መንግሥታትን ይገዛል፣ ወደ ጽድቁ አገዛዝና አስተዳደርም ያፈልሳቸዋል፡፡ ይህንንም ሃሳብ በማቴዎስ ምዕራፍ 28 ቁጥር 19 እና 20፤ 1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 15 ከቁጥር 24 እስከ 28 እና ራእይ ምእራፍ 22 ቁጥር 16 ተገልጦ እናያለን፡፡

ከዚህም በተጨማሪ፣ እንደ እግዚአብሔር ፍጹማዊ ተምሳሊት እና እንደ ታደሰ ሰብዓዊ ዝርያ አምሳል፣ ኢየሱስ ባለ ሙሉ መብት የፍጥረታት ጌታ ሆኖ እንደሚገዛ በእብራውያን ምዕራፍ 2 ከቁጥር 7 እስከ 8 እናያለን፡፡

ከዚህም ባሻገር፣ ኢየሱስ በአለቆችና በሥልጣናት ሁሉ ላይ ማለትም በመላእክትና በአጋንንቶች ሁሉ ላይ እንዲሰለጥን ከፍ ከፍ ማለቱን በሮሜ ምዕራፍ 8 ቁጥር 38 እና 39፤ ቆላስያስ ምእራፍ 1 ቁጥር 16 እና ምዕራፍ 2 ቁጥር 15 ተጠቅሶ እናገኘዋለን፡፡ እስኪ ጳውሎስ የኢየሱስን ንጉሣዊ አገዛዝ በፊልጵስዩስ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 9 እስከ 11 እንዴት ጠቅለል አድርጎ እንደጠቀሰው አድምጡ፡፡

> በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥
> ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤
> ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፥
> ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው። (ፊልጵ 2፥9-11)

ኢየሱስ ሁሉን ይገዛል፣ ማለትም፣ ቤተክርስቲያንን፣ መንግሥታትን፣ ፍጥረትን የመላእክትንና የአጋንንቶችን መንፈሳዊ ዓለም ሁሉ ማለት ነው፡፡ አገዛዙ ግን ዘወትር እኛ እንዲህ ይሆናል ብለን ልንተነብይ የማንችልበት ዓይነት ነው፡፡ ነገር ግን እርሱ እንደ እግዚአብሔር እቅድ ይገዛል፡፡ ኢየሱስ ሁሉን በመግዛቱ ምክንያት፣ ተከታዮቹ ምንም የሚያስፈራቸው ነገር እንደማይኖር መጽሐፍ ቅዱስ ዋስትና ይሰጠናል፡፡ የእኛ ድል የተረጋገጠ ነው፡፡ ከእርሱ ቁጥጥርና ሥልጣን ውጪ በእኛ ላይ የሚሆን ምንም የለም፡፡ ከደቃቋ ንዑስ- አቶም አንስቶ እስከ ፍጥረተ ዓለም ግዙፍ እንቅስቃሴ ድረስ አሁን የሚኖረው ነገር ሁሉ በእርሱ ሥልጣንና

ኀይል ስር ነው፡፡ በስተመጨረሻም፣ የምድር አህዛብ ነገሥታቶች ሁሉና መንፈሳዊ አካላት በጠቅላላ፣ የእርሱን ሉዓላዊነት ያረጋግጣሉ ለእርሱም ይሰግዳሉ፡፡

የኢየሱስን ትንሣኤ፣ ዕርገትና አገዛዝ ከዳሰስን፣ ኢየሱስ እንደ ክርስቶስ ወደፊት የሚያከናውነውን እንመለከታለን፡፡ ያም ሁሉ እያዩት መመለሱ ነው፡፡

# ዳግም ምፅዓት

ኢየሱስ ክርስቶስ ከመሆኑ የተነሳ፣ የእግዚአብሔርንም መንግሥት በምድር ለመመሥረት በግልጽ ተመልሶ እንደሚመጣ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል፡፡ የክርስቶስ መመለስ የክርስትና እምነት ማረጋገጫ ነው፣ ይህንንም በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 1 ቁጥር 11፤ 1 ተሰሎንቄ ምዕራፍ 4 ከቁጥር 13 እስከ 18፤ 2 ተሰሎንቄ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 5 እስከ 10 እና 1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 15 ቁጥር 23 ላይ እንማራለን፡፡

ስለ ኢየሱስ ዳግም ምፅዓት የምናደርገውን ውይይት ያንጊዜ በሚያከናውናቸው ሁለት ክንውኖች ብቻ ገድበን እንመለከተዋለን፡፡ እነርሱም፡- በሰው ዘርና በመናፍስት ላይ የሚፈርደው ፍርድ እና የፍጥረት መታደስ ናቸው፡፡ አስቀድመን በመናፍስትና በሰው ዘር ላይ የሚፈርደውን ፍርድ እንመልከት፡፡

## ፍርድ

በመጨረሻው ቀን ኢየሱስ እንደ ክርስቶስነቱና እንደ ንጉሥነቱ የሚኖረው ሃላፊነት በመላእክት፣ በአጋንንቶች እና በሰው ዘር ሁሉ ላይ የሚገባቸውን ፍርድ ለመስጠት በዳኝነት መቀመጥ ነው፡፡ ኢየሱስ ራሱ በማቴዎስ ምዕራፍ 25 ከቁጥር 31 እስከ 46 እንደተናገረው፣ በሞት የተለዩ የሰው ዘር ሁሉ አንድ ቀን ይነሣሉ፣ እያንዳንዱም ሰው እንደ ሥራው ይፈረድበታል፡፡ መልካም ሥራን የሠሩ የዘላለማዊ ብሩክ ሕይወት ብድራት ይጠብቃቸዋል፡፡ ክፉ ሥራዎችን የሠሩ ግን በዘላላማዊ እሳት ይቀጣሉ፡፡ ይህም ፍርድ በተጨማሪ በዮሐንስ ምዕራፍ 5 ከቁጥር 22 እስከ 30፤ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 10 ቁጥር 42 እና ምዕራፍ 17 ቁጥር 31፤ 2 ቆሮንቶስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 10 ላይ ተጠቅሷል፡፡

እርግጥ ነው፣ ሰዎች መልካም ሥራን መሥራት የሚችሉት መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው በኀይል ሲያድር መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል፡፡ እንግዲህ ይህ መልካም ሥራ ለክርስቲያኖች በክርስቶስ የመጽደቃቸው እውነታ ካልሆነ በስተቀር በራሳቸው ፋይዳ ቢስ ናቸው፡፡ አማኞችን ካላመኑት በላጭ የሚያደርጋቸው ሌላ ምንም ነገር የለም፡፡ ጳውሎስ በኤፌሶን ምዕራፍ 2 ከቁጥር 8 እስከ 10 እንደጠቀሰው፡

ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤
ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።
እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን።
(ኤፌ 2፥8-10)

በማንነታችን፣ ፍጥረት ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት በደለኛ ነው፡፡ በመጨረሻው የፍርድ ቀን ግን፣ በክርስቶስ ያመንን እኛ፣ ስለ እኛ የሞተልን ሥላሰ፣ በክርስቶስ ሞት፣ ከፍርድ እናመልጣለን፣ እርሱም በእኛ በኩል ስለሠራው መልካም የእግዚአብሔር ሥራ ሽልማትን እንቀበላለን፡፡

በተባረከ ማንነታችን፣ ከሞት ፍርሃት ሙሉ በሙሉ ነፃ ወጥተናል፡፡ የከበረው ሰውነታችን ከኢየሱስ አካል ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡ እኛም በሰላም፣ በብልጽግና፣ ከኩነኔ ነፃ በመሆን፣ ከርኩሰት እና ከኀጢአት ከበባ ነፃ ወጥተን ለዘላለም እንኖራለን፡፡ ከሁሉም በላይ፣ አዳኛችንንና አምላካችንን ፊት ለፊት እያየን በእርሱም ጥላ ስር እናርፋለን፡፡

ከሽልማታችንም አንፃር፣ በአዲሲቷ ሰማይና ምድር ከክርስቶስ ጋር እንገዛ ዘንድ ሥልጣንን እንቀበላለን፣ ይህንንም በሮሜ ምዕራፍ 8 ቁጥር 17 እና 2 ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 12 ላይ እናገኘዋለን፡፡ ጳውሎስ በ1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 6 ቁጥር 3 እንዳስተማረን፣ ይህንን ሥልጣን ከምንለማመድባቸው መንገዶች አንዱ ከኢየሱስ ጋር በፍርድ ወንበር በመቀመጥ በመላእክትና በአጋንንቶች ላይ በመፍረድ ነው፡፡ ውጤቱም በሰው ዘርም ላይ ከሚሰጠው ፍርድ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ በማቴዎስ 25 ቁጥር 41 እንደምናነብበው፣ ጻድቃን መላእክት ይሸለማሉ፣ ክፉ መናፍስቶች ደግሞ ይፈረድባቸዋል፡፡

በመናፍስትና በሰው ዘር ላይ የሚሰጠውን ፍርድ በዚህ መንገድ ከተረዳን፣ በኢየሱስ መመለስ ወቅት የሚከናወነውን የፍጥረት መታደስ እንመልከት፡፡

## ተሃድሶ

ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ 8 ከቁጥር 19 እስከ 22 እንደሚያስተምረን፣ በአዳም በደል ምክንያት እግዚአብሔር ምድርን ሲረግም፣ እርግማኑ መላውን ፍጥረት ነክቷል፡፡ በውጤቱም ፍጥረተ-ዓለም ለርኩሰት የተሰጠ ሆኗል፡፡ ነገር ግን ሮሜ ምዕራፍ 8 ቁጥር 21 እና ራእይ ምዕራፍ 22 ቁጥር 3 ስናነብብ፣ ኢየሱስ ዳግም ሲመጣ የኀጢአትንና የሞትን ቀንበር ከፍጥረት ላይ ይሰብራል፡፡ ከዚያም እኛ፣ከመጀመሪያው ፍጥረት እጅግ የምትሻለውን

መልካምና ፍፁም ምድር እንወርሳለን እንገዛለንም፡፡ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ይህንን የፍጥረት መታደስ ከተትረፈረፈ ምግብ፣ በሰውና በእንስሳት መካከል ከሚኖረው ሰላም፣ ለእግዚአብሔር በደስታ ከሚቀርብ አምልኮ አንፃር ተመልክተውታል፡፡ ይህንንም በኢሳያስ፣ በኤርምያስና በዘካርያስ መጻሕፍት ውስጥ ዳር እስከ ዳር እናገኘዋለን፡፡ ሐዋርያው ጴጥሮስ በ2 ጴጥሮስ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 10 እስከ 13 እንደገለጠው፣ ይህ የፍጥረት ኀዳሴ የዓለምን በእሳት መጥፋት ያስቀድማል፡፡ ውጤቱ ግን ግሩም ነው፡፡ ጴጥሮስ በ2ጴጥሮስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 13 እንደተናገረው፡

> ነገር ግን ጽድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደ ተስፋ ቃሉ እንጠብቃለን።
>
> *ለምሳሌ ያህል በራእይ መጽሐፍ የምናገኘው የአዲስ ሰማይና ምድር ስዕል የገነትና የከተማ ምስል ነው፡፡ መልካምና ከፉን የምታስታውቀው ዛፍና የሕይወት ዛፍ በተለይ በዚያ ይገኛሉ፡፡ ደግሞም ታላቅ ከተማም አለች፡፡ በመካከልዋ ወንዞች የሚያልፉባት አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከሰማይ ትወርዳለች፣ ይህም ወደ ገነት መልሶ ይወስደናል፡፡ በገነት ውስጥ ያለው ደስታና መስኀብ ፣ ደግሞም በከተማ ውስጥ ሊኖር የሚችለው ምጥቀትና ሥልጣኔ በዚያ ይኖራሉ፡፡ እኛም ወደዚያ እንናፍቃለን፡፡ በዚያ ጭንቀት ጨርሶ የለም፡፡ እኔ እንደማስበው፣ ፍጥረት የእግዚአብሔር ምንነት ብርቱ መግለጫ መሆኑን ይቀጥላል፣ በሰማያትና በምድርም የእግዚአብሔር አስደናቂ ሥራዎች ይገለጣሉ፣ ሆኖም ግን ፈጽሞ አስጨናቂዎች አይሆኑም ምክንያቱም እግዚአብሔር ሕዝቡን ስለሚጠብቅ በዚያ ሃዘንና ትካዜ ፈፅሞ አይኖሩም፡፡ ጴጥሮስ እንደሚናገረው፣ ጽድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና ምድር እንጠብቃለን፡፡ ፍፁም ጽድቅ የምላባትና ፍትሃዊ ማኅበረሰብ ያለባት ናት፡፡ ለሁላችንም መልካም ነገር ያለባት ናት፡፡ በዚህ ምድር የሚገጥመን መከራ፣ የሚያስለቅሰን ሰቆቃ፣ ወደዚያ ወደ ክብራችን ስንሄድ እንደገና አናየውም፣ ሁሉ መልካም ይሆናል፡፡ የእግዚአብሔር ፍትህ ይገለጣል፣ እኛም ስለ እግዚአብሔር ምሕረት በምስጋና እንምላለን፡፡ [ዶ/ር ጆን ፍሬም]*

ስለዚያች ቀን እስኪ በዚህ መንገድ አስቡ፡፡ ፍጥረት እጅግ አስደናቂ መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን፡፡ ፍጥረት በኀጢአት እርግማን ስር ሆኖም አንኳን፣ አንዳንድ ጊዜ በውበቱ እንገረማለን፤ በውስብስብነቱ እንደነቃለን፣ ለእኛም የሚሰጠንን ደስታ በማሰብ በአድናቆት እንሞላለን፡፡ እስኪ አሁን ደግሞ የኀጢአት እርግማን፣ ስቃይ፣ ህመም፣ ጦርነት፣ ሞትም እንኳን የማይኖርበትን ፍጥረት አስቡ፡፡ ኢየሱስ ዳግም ሲመጣ ስለምናገኘው አዲስ ፍጥረት አስቡ ውበቱን፣ ድምቀቱን እና ደስታውን በዚያ መኖር ምንኛ ያስደንቅ? ኢየሱስ ሁሉን

የሚገዛ ክርስቶስ በመሆኑ፣ ለእኛ እንከን የሌለበትንና እግዚአብሔርን ለዘላለም እያከበርን የምንኖርበትን ዓለም ለማዘጋጀት ሥልጣኑም ኀይሉም አለው፡፡

እንደ ክርስቶስ ተከታዮች፣ ታላቁ ተስፋችን እርሱ ዳግም የሚመጣ መሆኑና የመንግሥቱን በረከቶች የሚያወርሰን መሆኑ ነው፡፡ ይህ የወደፊት ራእይ ለሚጠፉት የእርሱን ወንጌል ለማድረስ በሚኖር አጣዳፊነት እግዚአብሔርን እንድናገለግል ይቀሰቅሰናል፡፡ በክርስቶስ ውስጥ ያለ ስጋት ስለተቀመጥን በኀጢአታችን እንደማይፈረድብን ብናውቅም እንኳ ህይወትን በንፅሕና እንድንመራም ያበረታታናል፡፡ እርሱንም ተስፋ ስለሰጠን ታላላቅ በረከቶች እንድናመሰግነውና እንድንወድደው ያበረታታናል፡፡

# 6. ማጠቃለያ

ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰኘው በዚህ ትምህርታችን፣ የኢየሱስን የምድር አገልግሎት ወሳኝነት ውልደቱን የዝግጅት ጊዜውን፣ የአደባባይ አገልግሎቱን፣ ሕማማቱንና ሞቱን እናም በመጨረሻ መከበሩን በመዳሰስ ለመቃኘት ሞክረናል፡፡ እያንዳንዳቸው የኢየሱስ ሕይወት ክፍሎች እንደ እግዚአብሔር ክርስቶስ የኢየሱስን ድርሻ እንድንገነዘብ ጉልህ መረዳትን ይሰጡናል፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ከኖሩት ሁሉ የሚልቅ ኀያልና አስደናቂ ሰው ነው፡፡ ከሁሉ የሚያስደንቀው ደግሞ ዛሬም የሚኖር፣ ከሰማይ ዙፋኑም እንደ ንጉሥ፣ እንደ ካህንና እንደ ነቢይ ሆኖ የሚያገለግል መሆኑ ነው፡፡ እርሱን በታማኝነት ብናገለግለው፣ በሚቀጥለው ዓለም የሚጠብቀን በረከት ተስፋ ከምናደርጋቸው ትልልቅ በረከቶች እጅግ የሚልቅ እንደሆነ ቃሉ ያረጋግጥልናል፡፡ ወደፊት በምንመለከታቸው ትምህርቶች፣ የኢየሱስን የነቢይነት፣ የክህነትና የንግሥና አገልግሎት በጥልቀት እንመለከታለን፡፡ ግን በዚህም ደረጃ ቢሆን እንኳን፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ድንቅነትና ታላቅነት ለመዋጥና ሕይወታችንንም ለእርሱ ለመስጠት የሚያስችሉንን ከበቂ በላይ ምክንያቶች አይተናል፡፡